አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3574 | ቅዳሜ ግንቦት 15 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




# የከተማዋ ልማት አካታችነት እስከ ምን?

4



ፎቶ ከገጸ ድር

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ገብስ ተራ ቁጥር 3 የበጎነት መንደር የመኖርያ ቤት ከተሰጣቸው እናት ጋር

## የአረፋ እሴቶች ከመንፈሳዊ በረከት እስከ ብሔራዊ አንድነት

8



ፎቶ- ከፋይል

የታሪክ ተመራማሪ ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል

## የበዓላቱ ተጨማሪ ድምቀት

7



ፎቶ- ከገፀ ድር

በቴዎድሮስ አደባባይ አካባቢ የተከናወነው የኮሪደር ልማት ስራ ለአደባባይ በዓላት ተጨማሪ ድምቀት ይፈጥራል

## በፅናት የተገኘ ስኬት

23



ፎቶ- ከገፀ ድር

አርሴናል ከ22 የፅናት ዓመታት በኋላ የእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ ዋንጫ አሸናፊ ሆኗል

# በባዶ ምሳ ዕቃ ውስጥ የበቀለ ተስፋ

### የተማሪዎች ምገባ ፕሮግራም ከማህበራዊ ፍትሕ እስከ ትውልድ ግንባታ

**በቱም ቱም ሌንጮ**

ረፋድ አምስት ሰዓት፤ በአዲስ አበባ ከሚገኙ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች በአንዱ ክፍል ውስጥ የልጅ አንጀት የማይችለው ርሃብ፣ አዕምሮ ሊቀበለው የሚከብደው የመንፈስ ስብራት ነግሷል፡፡ ከክፍሉ በአንደኛው ጥግ ተማሪ ፈቃዱ የኔነህ የተማሪዎች ወንበር ላይ የተቀመጡ ደብተሮቹን ተደግፎ ተኝቷል። መምህሩ ጥያቄ ሲጠይቁ እጁን አውጥቶ የማይመልሰው፣ አይኖቹን ግን ግድግዳው ላይ የተሰቀለው ሰዓት ላይ የሚያንከራትተው ፈቃዱ፣ ሁል ጊዜ ጠዋት ትምህርት ቤት ሲመጣ በእጁ የላስቲክ ምሳ ዕቃ መያዝ አይረሳም።

ወደ ገጽ 9 ዞሯል



ፎቶ- ከገፀ ድር

የተማሪዎች ምገባ መርሃ ግብሩ ትውልድ ተሻጋሪ ውጤት እያመጣ ነው




# የአዲስ አበባ እህት ከተሞች፡- ከናይሮቢ እስከ ባኩ

- በአዲስ አበባ እና በባኩ መካከል የተደረገው የእህትማማችነት ከተማ ስምምነት አዲስ አበባ ለተያያዘችው የልማት ስራ ተጨማሪ አቅም እንደሚፈጥር ተመላክቷል

**በመለሰ ተሰጋ**

የብሪታንያ የታሪክ ጸሐፊ ፕሮፌሰር ሪቻርድ አቨርይ ስለ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት፣ ስለ ናዚ ጀርመን፣ ስለ ወታደራዊ ታሪክ እና በጦርነቱ ወቅት የወደሙ የአውሮፓ ከተሞችን አስመልክቶ ባደረጓቸው ጥናቶች ይታወቃሉ፡፡ በተለይ እ.ኤ.አ ጥር 1 ቀን 2013 “The bombing war: Europe From 1939 To 1945” በሚል ርዕስ ባሳተሙት

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

**አድራሻ** +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ



## የከተማዋ ልማት አካታችና የነዋሪዎችን ተጠቃሚነት ያረጋገጠ ነው!

አዲስ አበባ የኢትዮጵያ የልብ ምት፣ የአፍሪካ መዲና እና ዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲ ማዕከል ናት። ሆኖም፣ ለረጅም ዘመናት የከተማዋ ልማት፣ ከዚህ ግዙፍ ስምና ኃላፊነት ጋር ሲመዛዘን በብዙ ዘርፎች ዝቅተኛ ነበር። የከተማዋ መንደሮች ያረጁ፣ የኑሮ ሁኔታዋ ፈታኝ እና የነዋሪዎቿ ተጠቃሚነትም በዘላቂነት ያልተረጋገጠ ነበር። ይህን ክፍተት ለማስተካከል ባለፉት ጥቂት ዓመታት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተወሰዱት ብርቱ እና ዘርፈ-ብዙ የልማት እርምጃዎች፣ የከተማዋን የጉስቁልና ገጽታ በአዲስና ተስፋ ሰጪ ምዕራፍ እየተኩት ይገኛሉ።

የከተማ አስተዳደሩ ባለፉት ጥቂት ዓመታት የጀመረው የተቀናጀ የልማት ስትራቴጂ፣ የከተማዋን ገጽታ በአስደናቂ ሁኔታ ከመቀየሩም በላይ፣ የነዋሪዎችን የኑሮ ዘይቤ ወደ አዲስ ምዕራፍ አሸጋግሮታል። ይህ ለውጥ በአጋጣሚ የተፈጠረ ሳይሆን፣ በጥንቃቄ በተቀረጹ እቅዶች፣ በጠንካራ የክትትል ሥርዓት እና በአመራሩ የላቀ ቁርጠኝነት የመጣ ነው። ዛሬ አዲስ አበባን ሲመለከቱ፣ ከምንጊዜውም በላይ በንቃትና በልማት እንቅስቃሴ ውስጥ የምትገኝ ከተማ ሆና ትታያለች። ይህ ለውጥ ለከተማዋ እድገት ብቻ ሳይሆን፣ ለእያንዳንዱ ነዋሪ ክብርና ደህንነት ትኩረት የሰጠ መሆኑ፣ የለውጡን እሴት በእጅጉ ከፍ ያደርገዋል።

የዚህ ዘርፈ-ብዙ የልማት እንቅስቃሴ ዋናው ምስጢር አካታችነት ነው፤ እያንዳንዱ የልማት ፕሮጀክት የተነደፈው የህብረተሰቡን መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ነው። ያረጁና ለኑሮ አደገኛ የነበሩ ቤቶችን በዘመናዊና ለኑሮ ምቹ በሆኑ መኖሪያ ቤቶች መተካት፣ የብዙ ዜጎችን የቤት ባለቤትነት ህልም እውን እያደረገ ነው። በተለይም ህጻናት በአካልና በአዕምሮ ጎልብተው የሚያድጉባቸው የመጫወቻ ስፍራዎችና አረንጓዴ ፓርኮች መገንባት፣ ለከተማዋ የነገ ተስፋ ለሆኑት ወጣቶች የተሻለ የኑሮ መሰረት ጥሏል። የሴቶችና የወጣቶችን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ የሥራ ዕድል ፈጠራዎች የኢኮኖሚ አቅማቸውን በማሳደግ የከተማዋን ምርታማነት አጠናክረዋል።

የእግረኛና ብስክሌት መንገዶችን ያካተተው አዲሱ የትራንስፖርት ሥርዓት፣ ከተማዋን ለጤናማና ንቁ የአኗኗር ዘይቤ ተስማሚ አድርጓታል። የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎችና የመናፈሻ ስፍራዎች በየሰፈሩ መገንባት፣ የከተማዋን ድባብ ከማድመቅ ባለፈ ነዋሪው የሚዝናናበትና አብሮ የሚቀራረብበት ማህበራዊ መሰረት ፈጥሯል። እነዚህ ተግባራት አዲስ አበባን ከግዙፍ ግንባታዎች ባለፈ፣ ለነዋሪዎቿ እውነተኛ ቤትና ለመኖሪያ ምቹ ከተማ እያደረጓት ይገኛሉ። ይህ የከተማዋ ሁሉን አቀፍ ለውጥ፣ ለሌሎች የአፍሪካ ከተሞች ሊቀሰም የሚገባ ትልቅ የልማት ተሞክሮ ነው።

በእነዚህ ሰፊ የልማት ስራዎች የከተማዋ ገጽታ ከመቀየሩ ባለፈ፣ የነዋሪዎችን የኑሮ ደረጃ በማሻሻል ረገድ እየመጣ ያለው ለውጥ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ነው፡፡ አሁን አስፈላጊው ነገር አስተዳደሩ ይህንን የልማት ወኔና ፍጥነት በዘላቂነት ማስቀጠል ነው። የለውጡ ተጠቃሚ የሆነው የከተማዋ ነዋሪም፣ እነዚህን ልማቶች የራሱ አድርጎ የመጠበቅ፣ የመንከባከብና ለቀጣይ የልማት ፕሮጀክቶችም የተቻለውን ሁሉ ድጋፍ የማድረግ ታሪካዊ ኃላፊነት አለበት።

አዲስ አበባ የቆየውን የልማት ማነቆ በጣጥሳ ጥላ፣ ወደ ብልፅግናና ምቹ ከተማነት በፍጥነት እየተጓዘች ተጨባጭ ውጤት እያሳካች ትገኛለች። የከተማዋ አካታች እና የብዙሃኑን ነዋሪ ተጠቃሚነት ያረጋገጠ ነው። ይህንን ልማት በጋራ በመንከባከብና በማገዝ፣ አዲስ አበባ ለሁሉም የምትመች፣ የኩራት ምንጭና ለዓለም የብልፅግና ተምሳሌታዊት መዲና ሆና እንድትቀጥል ማድረግ የጋራ ግዴታችን ነው።

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## ችላ ሊባል የማይገባው ከታሪፍ በላይ የዋጋ ጭማሪ

**ኤፍራታ ከአስኮ**

የትራንስፖርት አገልግሎት የሰው ልጆችን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የሚያሳልጥ በመሆኑ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው እሙን ነው። የሰውን ልጅ ህይወት ከሚያቀልለው የትራንስፖርት አገልግሎት አማራጮች መካከል የአንበሳ የከተማ አውቶቡስ እና የሚድ ባስ ታክሲ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

እነዚህ የትራንስፖርት አማራጮች በሚሰጡት አገልግሎት የከተማውን ነዋሪ ህይወት አቅልለዋል፡፡ ነገር ግን አገልግሎት ሰጪዎቹ አገልግሎት አሰጣጣቸው ዛሬ የተሰማኝን አስተያየት ለመፃፍ አነሳስቶኛል፡፡

በታክሲዎችና ሚዲባሶች የሚታየው ዋነኛው ችግር "እንኳንስ ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ" እንደሚባለው አባባል የተከሰተውን የነዳጅ እጥረት ሰበብ አድርገው ከተቀመጠው ታሪፍ እጥፍ ማስከፈላቸው ነው፡፡ በተለይም ከሥራ መግቢያ፣ መውጫ እና የሳምንቱ መጨረሻ እንዲሁም የበዓል ቀናት ችግሩ የከፋ ነው፡፡ ከገጠመኝ የተወሰነ አስተያየት ብገልጽ ጥሩ ይመስለኛል፡፡ የተነሳሁት በተለምዶ አስኮ አዲስ ሰፈር ወደ ፒያሳ ለመሳፈር ነው፡፡ የታክሲ ረዳቱ ገንዘብ መሰብሰብ ሲጀምር የጠየቀን ከታሪፍ በላይ ነበር፡፡ "ለምን ትክክለኛው ታሪፉ አይደለም" ብለን እኔ እና ሌሎች ተሳፋሪዎች ለማስረዳት ስንሞክር "ካልፈለጋችሁ መውረድ ትችላላችሁ" የሚል መልስ ተሰጠን። የምንጓዘው ለመዝናናት አይደለምና እንዳልተገባ እያወቅን ከፍለን ያሰብንበት ደረስን፡፡ በነገራችን ላይ ሳልናገር ማለፍ የማልፈልገው የተሳፋሪም አንድ ሆኖ መብቱን አለማስከበሩ ሕገ ወጥነትን እንዲባባስ አድርጎታል፡፡

የታክሲዎች ያልተገባ ተግባርን ሸሽተን ወደ ሌላው አማራጭ አንበሳ የከተማ አውቶቡስ ለመሳፈር እንሞክራለን፡፡ በተለይም ምሳ ሰዓት አካባቢ፤ ትኬት የሚቆርጡት በተለምዶ ትኬተር የምንላቸው የሚቀያየሩበት ሰዓት "ትኬት ቆራጭ የለም" በማለት ፌርማታ ላይ ሳያቆሙ ዘግቶ የማለፍ ሌላ ችግር ይገጥማል፡፡ የአውቶቡስ ካፒቴኖቹ እንደማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ተቀጥረው ሳይሆን እንደ ግል ንብረታቸው እንደሚያዩትም ለተሳፋሪዎች ከሚመልሱት ተገቢ ያልሆነ መልስ የምረዳው ነው፡፡ ሌላው የሚገርመው ትኬት ቆራጭም ባይኖር የሚያውቁትን ተሳፋሪ በፊት በር ከፍተውለት ሲገባና ሌሎቻችን ቆመን ተሳፍሮ ሲሄድ ማየት ሌላኛው ትዝብቴ ነው፡፡

ከታሪፍ በላይ መጨመር ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ተሳፋሪዎች ላይ ከባድ ጫና ይፈጥራል ባይ ነኝ፡፡ "ትኬት ቆራጭ የለም" በማለት ተሳፋሪዎችን ሳይጭኑ ማለፍም እንዲሁ ለረጅም ጊዜ ትራንስፖርት በመጠበቅ ጊዜያቸውን እንዲያባክኑ ያደርጋል፤ ይህም ለስራ፣ ለትምህርት ወይም ለሌሎች ጉዳዮች መዘግየትን ያስከትላል። በአገልግሎቱ አሰጣጡም ላይ እምነትን ያሳጣል። የተገልጋዩን እምነት በመቀነስ "የትራንስፖርት ሥርዓቱ ፍትሐዊ አይደለም" የሚል ስሜትን ይፈጥራል። ይህ የግል አስተያየቴ ይሁን እንጂ ችግሩ አብዛኛው የከተማዋ ነዋሪ ላይ የደረሰና የሚስተዋል ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ችግሮች የተሳፋሪዎችን መብት፣ ደህንነት እና የዕለት ተዕለት ኑሮ በእጅጉ የሚጎዱ ናቸው፡፡ በመሆኑም ተገልጋይ አገልግሎቱን በአግባቡ የማይሰጥ የትራንስፖርት አማራጭን በማጋለጥ፤ የሚመለከተው የመንግሥት አካልም ተገቢውን ቁጥጥርና ህጋዊ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋቸዋል ባይ ነኝ።

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ**

**እየተዘጋጀች ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ ግንቦት 1985 ዓ.ም ተመሰረተች**

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ይግለጡ ጓዴ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
ለይላ መሀመድ
አብርሃም ገብሬ
ፋንታነሽ ተፈራ

**ዋና አዘጋጅ**
ተካልኝ አማረ
Tekalignteke123@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር B91/17

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# ለፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ቅስቀሳ የተዘጋጀ

## የብልፅግና መንገድ፡- የኢትዮጵያ ጂኦግራፊያዊ እስረኝነት ማብቂያ




የቀይ ባህር እና የዓባይ ውኃዎች የኢትዮጵያን ብሔራዊ ህልውና እና ጂኦ- ፖለቲካዊ ቁመና የሚወስኑ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ጸጋዎቻችን ናቸው። ይሁን እንጂ በታሪካዊና ፖለቲካዊ ስህተቶች ምክንያት ሀገራችን የአሰብ እና የምጽዋ ወደቦችን በማጣት "የመልክዓ- ምድር እስረኛ" ለመሆን ተገዳለች። ይህ ጥገኝነት ለከፍተኛ የወደብ ኪራይ ወጪ ከመዳረጉ ባለፈ፣ በብሔራዊ ደኅንነታችን ላይ ስጋት ደቅኗል። የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ የቅንጦት ሳይሆን የ130 ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ የህልውና፣ የፍትሕ እና የታሪክ ዕዳን የመክፈል ጉዳይ ነው።

ብልፅግና ፓርቲ ይህንን ለሶስት አስርት ዓመታት ተዳፍኖ የነበረውን አጀንዳ አቧራውን አራግፎ በይፋ በማንሳት የዜጎችን የሥነ- ልቦና ልዕልና መመለስ ችሏል። ጥረታችን የሌሎችን ሉዓላዊነት በመንካት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን፣ በአለም ዓቀፍ ሕግ መሠረት "የሰጥቶ መቀበል" መርሕን የተከተለ ሰላማዊና ዲፕሎማሲያዊ መንገድ ነው። ባለፉት ዓመታት የአንድ ወደብ ጥገኝነትን ለመቀነስ ከጎረቤት ሀገራት ጋር የስትራቴጂክ ትሥሥር የመፍጠር እና የባህር ኃይልን የመገንባት ተጨባጭ ሥራዎች ተጀምረዋል። ይህም ለአምራች ኢንዱስትሪዎች እና ለኢንቨስትመንት መረጋጋትን ከመፍጠሩም በላይ ለወጣቱ ትውልድ አዲስ የኢኮኖሚ ተስፋን አሳይቷል።

በቀጣይም የሕዝብ ድምጽ አግኝተን መንግሥት ስንመሰርት፣ ይህንን የባህር በር ጥያቄ ከታላቁ የሕዳሴ ግድብ ስኬት ጋር በማስተሳሰር የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ብልፅግና እናረጋግጣለን። ሰላማዊና ሕጋዊ ድርድሮችን ወደተጨባጭና ሉዓላዊ የባህር በር ስምምነት በማሸጋገር ሀገራችንን የቀጠናዊ የንግድና የደኅንነት ትሥሥር ማዕከል እናደርጋታለን። ኢትዮጵያ ወደባህሯ ስትመለስ ትጠነክራለች፡፡ እኛ የመረጥነው መመለስንና መጠከርን በመሆኑ፣ ለነገው ትውልድ ቁጭትን ሳይሆን ሉዓላዊና የበለጸገች ሀገርን እናወርሳለን።

ብልፅግናን በመምረጥ ኢትዮጵያን የባህር በር ባለቤት ያድርጉ!!!

**ብልፅግናን ይምረጡ**

**ምልክታችን የስንዴ ነዶ ነው።**

**የስንዴ ነዶ የመደመር፣ የትብብር እና የአንድነት ተምሳሌት ነው።**

**ኢትዮጵያን ወደ ተምሳሌት ሀገር!!!**

**ይህ ቦታ ለኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ህብረት፣ ለነፃነት እና እኩልነት ፓርቲ፣ ለባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ፣ ለሕብር ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ እና ለኢትዮጵያ ዜጎች ለማሕበራዊ ፍትሕ ፓርቲ ምርጫ ቅስቀሳ የተሰጠ ቢሆንም ፓርቲዎቹ የቅስቀሳ ጽሑፍ ባለማምጣታቸው ጋዜጣው ከዚህ በታች ያለውን የራሱን ጽሑፍ አስተናግዶበታል።**



## የምርጫ ፋይዳ ሲቃኝ

**በስንታየሁ ምትኩ**

ምርጫ የዴሞክራሲ የማዕዘን ድንጋይ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ሥርዓት ዜጎች ሀሳባቸውን በነጻ የሚገልጹበት እና ሀገር የሚያስተዳድሩ ብቁ ዕጩዎችን ለሥልጣን የሚያበቁበት አንዱ መንገድ ድምፅ መስጠት ወይም መምረጥ ነው፡፡ በመሆኑም የዜጎች መምረጥ በርካታ ጥቅሞችን ያስገኛል፡፡

ምርጫ የዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ቁልፍ ጽንሰ ሃሳብ የሚረጋገጥበትም ነው፡፡ ዴሞክራሲ ሲባል በአጭሩ የሕዝብ አስተዳደር ማለት ሲሆን፤ ሕዝቡ ሀገርን ማን እንደሚመራ ይወስናል፡፡ በዴሞክራሲ ምርጫ ሕዝብ የሀገርን አቅጣጫ የማመላከት እና በውሳኔዎች ላይ የመሳተፍ መብት አለው፡፡ ሕዝቡ ይህንን ፍላጎቱን በምርጫ ድምፅ በመስጠት ይገልጻል።

ሌላው ምርጫ በሕዝብ የተወከለና ቅቡልነት ያለው መንግሥት ለማቋቋም ያስችላል፡፡ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ መንግሥት ሕጋዊነቱን የሚያገኘው ከሕዝብ ፈቃድ ሲሆን፤ ይህም በነፃና ፍትሐዊ ምርጫ አማካኝነት ይረጋገጣል፡፡

በኢፌዴሪ ህገ መንግሥት አንቀጽ 38 መሠረት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በቀለም፣ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በኃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግበት በየጊዜው በሚደረግ ምርጫ የመምረጥና የመመረጥ መብት አለው፡፡ ምርጫው ሁሉን አቀፍ፣ በሁሉም እኩልነት ላይ የተመሰረተና በሚስጢር ድምፅ አሰጣጥ መራጩ ፈቃዱን በነጻነት የሚገልጽበት፣ ዋስትና የሚሰጥበት መሆን አለበት፡፡ ይህም በምርጫ መሳተፍ ሕገ መንግሥታዊ የዜግነት መብት መሆኑን ያሳያል፡፡ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓትም ዜጎች በሀገራቸው በሚኖር የፖለቲካ እንቅስቃሴ ቢያንስ በምርጫ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ይላል፡፡

ምርጫ ዜጎች እኩልነታቸውን የሚያረጋግጡበት መብት ነው፡፡ በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ 1162/2011 እና በተሻሻለው አዋጅ መሠረት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ፣ በድምፅ መስጫው ዕለት ዕድሜው 18 ዓመት የሚሞላውና ከዚያ በላይ የሆነ በመራጭነት መመዝገብ ይችላል፡፡ በአዕምሮ ህመም ምክንያት የመወሰን አቅም የሌለው መሆኑ ሥልጣን ባለው አካል ወይም በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠበት፣ የመምረጥ መብት በሕግ ወይም አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በፍርድ ቤት ውሳኔ ከተገደበበት ውጪ ማንም መምረጥ ይችላል፡፡

ምርጫ ዜጎች የሀገር ፍቅርን የሚገልጹበት እና ዘመናዊነትን የሚለማመዱበት ሂደት ነው፡፡ ሀገርን መውደድ በቃላት ብቻ የሚገለፅ አይደለም በተግባርም እንጂ፡፡ ከዚህ አኳያ በምርጫ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ለሀገር መጻኢ እድል ማሰብ ነው፡፡

ምርጫ ዜጎች የመረጧቸው ተወካዮችን ተጠያቂነትን የሚያረጋግጡበት ሂደትም ነው፡፡ ምርጫ ኃላፊዎች ወይም ተመራጮች ለሚሰሩት ሥራ ተጠያቂ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያገለግል መሠረታዊ መሣሪያ ነው። የተመረጡ ተወካዮች የመራጩን ፍላጎት ማንፀባረቅ የሚገባቸው ሲሆን፤ ተወካዮች ይህን ማድረግ የማይችሉ ከሆነ ከሥልጣን እንዲወርዱ ማድረግ ይቻላል፡፡ ምርጫዎች መራጮች ተወካዮቻቸው ግዴታቸውን እየተወጡ ወይም በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት የገቡትን ቃል እየጠበቁ እንደሆነ ከተሰማቸው እንዲቀጥሉ አሊያም ኃላፊነታቸውን እንዳልተወጡ ከተሰማቸው አዳዲስ መሪዎችን የመምረጥ ዕድል ይሰጣቸዋል።

ምርጫ ዜጎች በተለያዩ ሀገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ መድረኮች የሚወክላቸውን አስተዳደራዊ አካል የሚመርጡበት፣ መንግሥት ለዜጎቹ የሚጠቅም ፓሊሲዎች እንዲያዘጋጅና እንዲተገብር የሚያደርጉበት፣ ሐሳብን የመግለጽ እድልን የሚያረጋግጡበት፣ የመልካም አስተዳደር መስፈንን የሚከታተሉበት ዓይነተኛ መሳሪያ ነው፡፡

በሌላ በኩል በምርጫ አለመሳተፍ ወይም አለመምረጥ ዜጎች ሊወክላቸው በማይችል ወኪል መተዳደርና ባልመረጧቸው እና ባልደገፏቸው የአስተዳደር አካላት ውሳኔ እንዲሁም አስተዳደራዊ ሥርዓት ስር ተገዢ መሆን ግዴታ አለባቸው፡፡ ከዚህ አኳያ ዜጎች አለመምረጥ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተጽዕኖዎች ለመከላከል የዜግነት መብታቸውን በመጠቀም ድምፅ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

**ምንጭ፡-** የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ገፀ ድር፣ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ 1162/2011

# የከተማዋ ልማት አካታችነት እስከ ምን?

**በአብርሃም ገብሬ**



ፎቶ ከገጸ ድር
ከንቲባ አዳነች አቤቤ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ገብስ ተራ ቁጥር 3 የበጎነት መንደር የመኖርያ ቤት ከተሰጣቸው እናት ጋር

አዲስ አበባ በፈጣንና ዘመናዊ የለውጥ ጉዞ ውስጥ ትገኛለች። ለረጅም ዓመታት በትራፊክ መጨናነቅና ክፍት በሆኑ አረንጓዴ ስፍራዎች እጥረት ስትታማ የኖረችው መዲናዋ፣ ዛሬ ግን በታላላቅ የኮሪደር ልማቶችና የወንዝ ዳርቻ ፕሮጀክቶች አማካኝነት ገጽታዋን እየቀየረች ነው። እነዚህ ልማቶች ለከተማዋ አዲስ የህይወት ዘይቤ ከማላመዳቸውም በላይ፣ ነዋሪዎቿ ለዓመታት አጥተውት የነበረውን አረንጓዴ ስፍራና አማራጭ የመዝናኛ ስፍራዎች እንዲያገኙ አዲስ በር መክፈት ችለዋል፡፡

ይህ ሰፊና አካታች የመሰረተ ልማት ግንባታ ከተማዋን ወደ ላቀ የውበትና የፅዳት ደረጃ ከማሸጋገሩም ባሻገር፣ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሥነ-ልቦናዊ ዘርፎች ላይ የራሱን ትልቅ አሻራ ማሳረፍ ጀምሯል። በተለይ ለዘመናት የቆየውን የመዝናኛ ስፍራዎች እጥረት በከፍተኛ ደረጃ በመቅረፍ ረገድ የፈጠረው መነቃቃት በቀላሉ የሚገመት አይደለም። አዲስ ልሳን ጋዜጣም ባሳለፍነው ሐሙስ የተመረቀውን የኢኮ-ፓርክን ጨምሮ ሌሎች በከተማዋ የተሰሩት ታላላቅ የመዝናኛ ሥፍራዎች የነዋሪውን የአኗኗር ዘይቤ በመቀየር፣ የከተማዋን መልካም ገጽታ በመገንባትና የቱሪዝም ዘርፉን በማነቃቃት ረገድ ያላቸውን ሁለንተናዊ ፋይዳ በተመለከተ አጭር ዳሰሳ አድርጓል፡፡

## አዲሶቹ የህዝብ መዝናኛ ፓርኮች ለመዲናዋ ምን አዲስ ነገር ይዘው መጡ?

የአዲስ አበባን የከተማነት ታሪክ በአዲስ ምዕራፍ እየጻፉ ያሉት መጠነ-ሰፊ የኮሪደር ልማቶችና ዘመናዊ ሜጋ ፕሮጀክቶች፣ መዲናዋን ወደ ላቀ የውበትና የኑሮ ምቹነት ደረጃ እያሸጋገሯት ይገኛሉ። ይህ ከተማዋን አረንጓዴ፣ ውብና ለነዋሪዎቿ ተስማሚ ለማድረግ የተወጠነው ዕቅድ፣ በአሁኑ ወቅት ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ በርካታ ታላላቅ ፓርኮችን ለህዝብ ማበርከት ችሏል። ይህ ግዙፍ እንቅስቃሴ የከተማዋን ገጽታ ከመቀየር ባለፈ፣ ነዋሪው ከቤት ውጭ የሚያሳልፈውን የመዝናኛ ባህል በማነቃቃትና አዲስ አበባን በአፍሪካ ቀዳሚ የከተማ ቱሪዝም መዳረሻ በማድረግ ረገድ የላቀ ሚና እየተጫወተ ይገኛል።

በመዲናዋ እየተመዘገበ ላለው አረንጓዴና ዘመናዊ የከተማ ዕድገት በተጨባጭ ማሳያ የሚሆነውና ባሳለፍነው ሳምንት ሐሙስ ዕለት በአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በይፋ የተመረቀው አዲሱ የኢኮ ፓርክ አንዱ ነው፡፡ ፓርኩ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ልዩ ስሙ አስኮ አዲስ ሰፈር አካባቢ የተሰራ ሁለገብ የሕዝብ መዝናኛ ፓርክ ነው። ከንቲባ አዳነች አቤቤ በማህበራዊ የትስስር ገጻቸው የፓርኩን መመረቅ አስመልክተው ባጋሩት ጽሑፍ "ቦታው ከዚህ በፊት የቆሻሻ መጣያ የነበረ፣ ሕገ-ወጦችም ያለአግባብ ይጠቀሙበት የነበረ ሲሆን፣ ዛሬ በርካታ እሴቶች ተጨምረውበት መንፈስን የሚያድስ፣ ሕዝብ በጋራ የሚጠቀምበት ንፁህ አካባቢን ፈጥሯል" ብለዋል።

ይህ በላቀ ጥራትና ውበት የተገነባው የኢኮ ፓርክ በ30 ሺህ ካሬ ሜትር ሰፊ መሬት ላይ ያረፈ ሲሆን፣ ለአካባቢው ነዋሪዎችና ለከተማዋ ተለዋጭ የመዝናኛ አማራጮችን በስፋት የያዘ ነው። ፓርኩ ዘመናዊ ምህንድስናን ከተፈጥሮ ውበት ጋር አጣምሮ በውስጡ ማራኪ የውሃ ምንጭ (ፋውንቴን)፣ ደረጃውን የጠበቀ የእግር ኳስ ሜዳ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ የህጻናት መጫወቻ ስፍራ፣ የባህልና ሥነ-ጥበብ ስራዎች ማቅረቢያ አምፊ-ቴአትር፣ እንዲሁም ዘመናዊ ካፌቴሪያ፣ ሱቆችና የጁስ ባርን አካቶ ይዟል። ከዚህ በተጨማሪ ለጎብኚዎች ምቾት ሲባል ሰፊ የመኪና ማቆሚያ (ፓርኪንግ)፣ ዘመናዊ የሻወርና የመፀዳጃ ክፍሎች እንዲሁም ረጃጅም የሰውነት ማጎልመሻና የእግር ጉዞ መሄጃ መንገዶች በጥራት ተሟልተውለታል።

ይህ ግዙፍና አካታች የኢኮ-ፓርክ ማህበራዊ ደረጃና የኑሮ ልዩነት ሳይገድበው ህጻናት፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን እና አጠቃላይ የህብረተሰብ ክፍሎች ድሃ ሃብታም ሳይሉ በጋራ የሚገለገሉበት ጠንካራ የማህበራዊ ትስስር መድረክ ሆኖ የተሰራ ፕሮጀክት ነው። ከዚህ ፓርክ በተጨማሪ ከሳምንት በፊት የተመረቀው የአራዳ ፓርክም ብዙዎችን ያስደነቀ ሌላኛው ፕሮጀክት ሆኗል፡፡

የአራዳ ፓርክ በውስጡ የከተማዋን የስፖርትና የመንገድ መሰረተ ልማት ለማሳደግ እያንዳንዳቸው 5 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያላቸው የአስፓልት መንገድ፣ የብስክሌት መስመርና የመሮጫ መም እንዲሁም 6 ኪሎ ሜትር የሚረዝም ምቹ የእግረኛ መንገድ አካትቶ ይዟል። የአካባቢውን ጥንታዊ ለውጥ ይበልጥ ለማድመቅም በዙሪያው የነበሩ ከ700 በላይ ቤቶችና ሕንፃዎች ታሪካዊ ይዘታቸውን ሳይለቁ በጥንቃቄ እንዲታደሱ ተደርጓል።

ይህ ዘመናዊ ማዕከል ለንግድና ለፋይናንስ አገልግሎቶች ልዩ ትኩረት የሰጠ ሲሆን፣ ከፒያሳ ለተነሱ ነጋዴዎች ቅድሚያ የተሰጠባቸው 131 ዘመናዊ ሱቆች፣ 7 ካፌዎችና ሬስቶራንቶች፣ 1 ትልቅ ሱፐርማርኬት እና 1 የባንክ ቅርንጫፍ በውስጡ ይዟል። ከዚህ ባሻገርም ለአካል ብቃት እንቅስቃሴ የሚሆን 1 ዘመናዊ ጅምናዚየም፣ 7 አዳራሾች፣ ለተለያዩ ኩነቶች ማዘጋጃ የሚውሉ 8 ፕላዛዎች እና 3 አምፊ-ቲያትሮች የተገነቡለት ሲሆን፣ በሀገራችን ረጅሙ የሆነው ባለ 100 ሜትር የብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ መስቀያ እና በአይነቱ ልዩ የሆነው "ዳንሲንግ ፋውንቴን" ለፓርኩ ልዩ ብሔራዊ ግርማ ሞገስ አላብሰውታል። ለቤተሰብና ለህጻናት ምቾት ሲባልም 4 ዘመናዊ የመጫወቻ ስፍራዎች፣ ህፃናት ስለ ሀገራቸው እውቀት የሚቀስሙበት "ትንሿ ከተማ"፣ 15 ሄክታር አረንጓዴ ተክሎች፣ 22 የሕዝብ መጸዳጃ ቤቶች የተገነቡ ሲሆን፣ በአንድ ጊዜ 131 መኪናዎችን መያዝ የሚችል የመኪና ማቆሚያም አለው፡፡ የአራዳ ፓርክ የታሪክ መመልከቻ ጋለሪን፣ ሆቴሎችን፣ የውበት ሳሎኖችን እና የግብይት ማዕከላትን በአንድ ጥላ ስር በማቀፍ የአዲስ አበባ አዲሱ የቱሪስት መዳረሻና መለያ ምልክት መሆን ችሏል።

ከዚህ በተጨማሪ በከተማዋ እምብርት ላይ የተሰሩት የአንድነት ፓርክ፣ የወዳጅነት አደባባይ እንዲሁም ተፈጥሮን ከዘመናዊነት ጋር ያቀላቀለው የእንጦጦ ተፈጥሮ ፓርክ በአሁኑ ወቅት የመዲናዋ አዳዲስ የኩራት መለያና ህያው ምስክሮች ሆነዋል። ከእነዚህ ታላላቅ ስራዎች ጎን ለጎን፣ በቅርቡ በተከናወኑ የኮሪደር ልማቶች አማካኝነት በታሪካዊቷ ፒያሳ፣ በፍልውሃ እና በአዋሬ ወንዝ ዳርቻዎች ላይ የተገነቡት አዳዲስ ክፍት የህዝብ መዝናኛዎች ለከተማዋ ተጨማሪ ማራኪ ውበትና የንጹህ አየር መተንፈሻ መሆን ችለዋል። እነዚህ አዳዲስ ስፍራዎች ከተማዋ ለዘመናት ተጭኗት ከነበረው የህንጻ ብዛት ውጥረት አውጥተው ወደ አረንጓዴ ስፍራነት ቀይረዋታል።

ወደ ገጽ 20 ዞሯል

# የአዲስ ... ከገጽ 1 የዞረ

መፅሐፋቸው እንደ ሃምቡርግ፣ ድሬስደን፣ በርሊን፣ ዋርሶ፣ ሮተርዳም እና ለንደን ያሉ ታላላቅ ከተሞች ላይ የደረሰውን ጉዳት ያብራራሉ።

በከተሞች ላይ የሚደርሰውን እንዲህ አይነቱን ጉዳት ለማካካስም ሆነ ፈጣን ልማት ለማረጋገጥ የእህትማማች ከተሞች ግንኙነት መመስረት አስፈላጊ ነው፤ የእህትማማች ከተሞች ግንኙነት መመስረት የጀመረው ከዚሁ አስከፊ ጦርነት በኋላ መሆኑንም ታሪክ ይነግረናል፡፡ በተለይም በግጭቱ በተጎዱ ሀገራት መካከል እርቅ ለመፍጠር እና ሰላምን እንደገና ለመገንባት የእህትማማች ከተሞች ግንኙነትን በመመስረት የሰላምና የዕድገት መንገዶችን ቀይሰዋል፡፡

እስከዛሬም ከ20 እስከ 30 ሺህ የሚደርሱ የዓለማችን ከተሞች የእህትማማችነት ስምምነትን በመመስረት ችግሮቻቸውን የሚፈቱበትን እና እድገቶቻቸውንም የሚያስቀጥሉባቸውን የጋራ ብልሃቶች በመዘየድ በንቃት እየተንቀሳቀሱ መሆኑን የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ድዋይት ዲ. አይዘንሃወር ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ “የዜጎች ዲፕሎማሲ”ን ከፍ ለማድረግ በሚል እ.ኤ.አ 1956 የመሰረቱት ‘ሲስተር ሲቲስ ኢንተርናሽናል’ የተሰኘው ድርጅት ይፋ ያደረጋቸው የቅርብ ጊዜ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

አዲስ አበባም የአፍሪካ የዲፕሎማሲ ዋና ከተማ እንደመሆኗ መጠን ቤጂንግ፣ ዋሽንግተን ዲሲ፣ ኪጋሊ እና አሁን ባኩን ጨምሮ ከበርካታ ከተሞች ጋር የእህትማማች ግንኙነትን መስርታለች፡፡ የመጀመሪያዋ አዲስ አበባ እህት ከተማ ናይሮቢ ስትሆን ስምምነቱም የተፈፀመው እ.ኤ.አ በ1960ዎቹ መጀመሪያ ነበር። በአሁኑ ወቅት ከተማዋ ከ30 በላይ የዓለማችን ከተሞች ጋር የእህትማማችነት ስምምነቶችን አድርጋለች፡፡

ከእነዚህም ውስጥ የደቡብ ኮሪያ ቹንቼዮን፣ የእስራኤል ቤርሳቤህ፣ የሩሲያ ሴንት ፒተርስበርግ፣ የደቡብ አፍሪካ ጆሃንስበርግ፣ የሱዳን ካርቱም፣ የዛምቢያ ሉሳካ፣ የቻይና ቤጂንግ እና ቾንግኪንግ፣ የፈረንሳይ ግራንድ ሊዮን፣ የጀርመን ላይፐዚግ፣ የቱርክ አንካራ፣ ዋሽንግተን ዲሲ እና ከአሜሪካ ሎስ አንጀለስ ይገኙበታል።

ለአብነት ከቻይና ከተሞች ቤጂንግ እና ቾንግቺንግ ጋር የተደረገው ስምምነትም በዘመናዊ የከተማ መሪ ዕቅድ፣ በትራንስፖርት አስተዳደር እና በደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ዙሪያ ከፍተኛ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የስልጠና እድሎችን አስገኝቶላታል፡፡ የቱርክዬ አንካራ ከተማም በአስተዳደር ሰራተኞች አቅም ግንባታ ላይ ስትሰራ፣ ሌይፐዚግ ደግሞ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በምርምርና በትምህርት ዘርፉ ላይ የበኩሏን ትብብር ታደርጋለች፡፡

እንደ ኢስታንቡል ካሉ ከተሞች ጋር የተደረጉ ስምምነቶችም ለቱርክዬ ባለሀብቶች መምጣት ትልቅ በር በመክፈት በሀገራችን የጨርቃ ጨርቅ እና የኢንዱስትሪ ፓርኮች ግንባታ ላይ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል።


ፎቶ- ከገፀ ድር
ከንቲባ አዳነች አቤቤ እና ከንቲባ ኤልዳር አዚዞቭ በአዲስ አበባ እና በባኩ ከተሞች መካከል የእህትማማችነት ስምምነት ተፈራርመዋል

እንደ ቤጂንግ፣ ሼንዘን እና ሻንጋይ ያሉ የቻይና ከተሞች ደግሞ ለአዲስ አበባ የኢንዱስትሪ ዞኖች መስፋፋትና ለታላላቅ መሰረተ ልማቶች እንደ ቀላል ባቡር የፋይናንስ እና ቴክኒክ ድጋፍ መገኛ እንደሆኑም መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

አዲስ አበባ ሰሞኑን ከአዘርባጃን ዋና ከተማ ባኩ ጋር በከተማ ልማት፣ በአገልግሎት ዲጂታላይዜሽን፣ በቤት ልማት፣ በቱሪዝም፣ በስፖርት እና በሁለቱ ህዝቦች መካከል የባህልና የታሪክ ልውውጥን የሚያጠናክር የእህትማማች ከተማ ስምምነት አድርጋለች፡፡

ከተማዋ፣ የዓለም አቀፍ “የእህት ከተሞች” ትስስርን እንደ ቴክኖሎጂ ሽግግር ድልድይ በመጠቀም፣ የወረቀት ላይ ስምምነቶችን ወደ ተግባር እየለወጠች ነው፡፡ ከተማዋ ከአውሮፓዋ ሊዮን ከተማ ጋር ካላት በርካታ ዓመታትን ያስቆጠረ ትስስር በተገኘ ልምድ እና ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ መንግስት በወሰደው ቆራጥ እርምጃ በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ሰፊ የኮሪደር እና የወንዞች ዳርቻ ልማት እየተተገበረ እና ሰውን ማዕከል ያደረገ ለውጥ እየተመዘገበ ይገኛል።

የአዲስ አበባ እህት ከተማ የሆነችው ኪጋሊ አገልግሎቶችን መቶ በመቶ ዲጂታላይዝ በማድረግ ቀዳሚ ከተማ መሆኗ ይታወቃል። አዲስ አበባም ይህንን ተሞክሮ በመውሰድ ወረቀት አልባ አሰራርን፣ ዲጂታል መታወቂያን እና የተሳሰረ የህክምና መዝገብን ተግባራዊ እያደረገች እና ፅዱ፣ ውብና ለኑሮ ተስማሚ ከተማነቷን እያረጋገጠች ነው፡፡

ከዲጂታላይዜሽን አንፃርም የወሳኝ ኩነት፣ የንግድ ፈቃድ እና የቤት ግብር ክፍያዎች በኦንላይን እንዲከናወኑ ተደርጓል። የመንገድ ደህንነትን በቴክኖሎጂ ለመቆጣጠር እና የካርቦን ልቀትን ለመቀነስ በተደረገው ትብብር አዲስ አበባ የብሉምበርግ ዓለም አቀፍ ሽልማት ባለቤት መሆኗም የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት፣ ከአዘርባጃን ዋና ከተማ ባኩ ጋር የተፈረመው ስምምነት በከተማ ልማት፣ በአገልግሎት ዲጂታላይዜሽን፣ በቤት ልማት፣ በቱሪዝም (ስፖርት ቱሪዝምን) ጨምሮ በሁለቱ ህዝቦች መካከል የባህልና የታሪክ ልውውጥን የሚያጠናክር መሆኑን አመልክተዋል።

ባኩ በካስፒያን ባህር ምዕራባዊ የባህር ዳርቻ ላይ የምትገኘው የአዘርባጃን ዋና ከተማ ናት። በካውካሰስ ክልል ውስጥ ካሉት እጅግ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ካላቸው ከተሞች አንዷ ስትሆን የአዘርባጃን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ እና የባህል ማዕከል ሆና ታገለግላለች። ባኩ በዓለም አቀፍ ደረጃ በዘመናዊና ሰማይ ጠቀስ ሕንፃዎቿ፣ በኃይል ኢንዱስትሪ፣ በተራቀቁ መሠረተ ልማቶቿ እና በታላላቅ የከተማ ትራንስፎርሜሽን ፕሮጀክቶቿ ትታወቃለች።

በቅርብ አሥርት ዓመታት ውስጥም ከተማዋ በትራንስፖርት፣ በአረንጓዴ ቦታዎች፣ በዲጂታል መሠረተ ልማቶች፣ በቱሪዝም እና በሥነ ሕንፃ ላይ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት በማድረግ ራሷን ወደ ዘመናዊ የከተማ ማዕከልነት ቀይራለች። ባኩ በቅርብ ዓመታት ውስጥ ያስተናገደቻቸው እንደ ዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ኮንፈረንሶች እና የከተማ ልማት መድረኮችን የመሳሰሉ ዓለም አቀፍ ዝግጅቶችም ተፈላጊነቷን የበለጠ ጨምረውላታል ይላል የአዘርባጃን ብሔራዊ የከተማ ፎረም እ.ኤ.አ ጥቅምት 2025 ይፋ ባደረገው መረጃ፡፡

ባኩ ከሂዩስተን፣ ኔፕልስ፣ ሳራጄቮ፣ ኢዝሚር፣ ሞስኮ እና ሌሎችም ከተሞች ጋር ሰፊ ዓለም አቀፍ እህትማማችነትን መስርታለች፡፡ በአዲስ አበባ እና በባኩ መካከል የተደረገው የእህትማማች ስምምነትም የሁለቱን ከተሞች ከፍታ የሚያሳይ መሆኑን የከተማ ልማት ባለሙያና አማካሪ ኢንጂነር በሱፈቃድ አየለ ይናገራሉ፡፡

አዲስ አበባ ልክ እንደ ባኩ ሁሉ፣ ግዙፍ የኮሪደር ልማት ፕሮጀክቶች፣ የከተማ እድሳት ፕሮግራሞች፣ የዲጂታል አገልግሎት ማሻሻያዎች፣ ዘመናዊ የትራንስፖርት፣ የወንዝ ዳርቻ ልማት እና ለቱሪዝም ትልቅ ቦታ በመስጠት ለምታከናውነው ልማት ስምምነቱ ተጨማሪ አቅም እንደሚኖረው ኢንጂነር በሱፈቃድ አብራርተዋል። ቀደም ሲል በ2026፣ አዘርባጃን ኢትዮጵያ በ2027 እንድታስተናግድ የሚጠበቀውን የCOP32 ዝግጅት ለመደገፍ ቃል መግባቷንም አስታውሰዋል፡፡

አዲስ አበባ የኮሪደር ልማት እና የዲጂታል አስተዳደር ፕሮጀክቶችን እያሰፋች ስትሄድ ተፈላጊነቷ እየጨመረ መጥቷል የሚሉት ኢንጂነሩ፣ በዚህም ዓለም አቀፍ ታላላቅ ጉባኤዎችን በማስተናገድ፣ በቅርስ ቱሪዝም እና ኢንቨስትመንት ዘርፎች መዳረሻነቷ ከፍ እያለም መጥቷል፡፡ ለአብነትም አዲስ አበባ በ2017 ዓ.ም ብቻ 150 ያህል ታላላቅ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን በስኬት በማከናወን ተመራጭ የኮንፍረስ ቱሪዝም መዳረሻ መሆኗን አረጋግጣለች፡፡

ሰሞኑን በከንቲባ አዳነች አቤቤ የተመራው የልዑካን ቡድን በአዘርባጃን የካስፒያን የባህር ዳር የተቀናጀ የከተማ ልማት ፕሮጀክት (Sea Breeze Project) መጎብኘቱን አስመልክቶ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ፅሕፈት ቤት ይፋ ባደረገው መረጃ መሰረት አዘርባጃን በአሁኑ ወቅት ካስመዘገበችው ከፍተኛ ዕድገት ጎን ለጎን የከተማ መልሶ ማልማት ሥራዎችን አጠናክራ ቀጥላለች፡፡ አሮጌ መንደሮችን በማንሳት አድሳለች፡፡ ከዚህ ቀደም ጥቅም ላይ ያልዋሉ ቦታዎችንም ለይቶ የማልማት ስትራቴጂ እየተከተለች ነው፡፡

በ16 ዓመታት ጊዜ ውስጥም የሚጠናቀቁ 50 ሺህ መኖሪያ ቤቶች፣ ሆቴሎችና ተያያዥ የልማት ሥራዎች በ‘Sea Breeze ፕሮጀክት’ ሥር በስፋት እየተገነቡ እንደሚገኙና የግሉ ዘርፍም ከመንግሥት ጋር በመቀናጀት በከፍተኛ ደረጃ እየተሳተፈ ይገኛል። አዲስ አበባም፣ በየዓመቱ 100 ሺህ ቤቶችን እና ተያያዥ ልማቶችን ለመገንባት ርብርብ እያደረገች ነው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ያረጁና የተጎሳቀሉ አካባቢዎችን የማደስ ሥራዎችን እያከናወነ ሲሆን፣ ቀደም ሲል በአግባቡ ጥቅም ላይ ያልዋሉ እንደ የጫካ ፕሮጀክት፣ ገላን-ጉራ እና አዲስ ቱሞሮ ያሉ አካባቢዎችን በመጠቀም አዲስ ከተማ የመገንባት ያህል ምቹ የልማትና የመኖሪያ ስፍራዎችን ለመፍጠር እየተሠራ ነው።

ይህ መጠነ-ሰፊ የቤት ልማትና የከተማ ማደስ እንቅስቃሴ በዋናነት የመኖሪያ ቤት ችግርን ለማቃለልና መዲናዋን የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ የታለመ ነው፡፡ በቀጣይነትም በላቀ ጥረትና በልማት ልኅቀት አዲስ አበባን እንደ ስሟ አበባ በማድረግ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነቷን ግንባር-ቀደም የማድረጉ ተግባር ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም በመረጃው ተመላክቷል፡፡

# “ካለብኝ የጤና ችግር አንጻር ማዕከሉ ትልቅ እረፍት ሰጥቶኛል”

### የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከል ተጠቃሚ

**በሳህሉ ብርሃኑ**



ፎቶ- ከገፀ ድር
የአራዳ ክፍለ ከተማ ቁጥር አንድ የተስፋ ብርሃን ምገባ ማዕከል ተመጋቢዎች በከፊል

አንዳንድ በጎ ተግባር አለ፤ ከብዙ መልካም ስራዎች መካከል ለብቻው ሰንደቅ ሆኖ የሚውለበለብ፤ ሰጪና ተቀባይን በፍቅር አገናኝቶ ተስፋን የሚያለመልም። አንዳንድ ማዕድም አለ፤ በችግረኞች ላይ ተስፋን ዘርቶ፣ የተራቡትን መግቦ የክፉ ጊዜ ጨለማን የሚገፍፍ። አንዳንድ የርኅራኄ እጅም አለ፤ ለራሱ ሳይሆን ለተቸገሩት እያደለ፣ ሰብዓዊነትንና ፍቅርን አስተሳስሮ በሰዎች ፈገግታ ውስጥ ለዘመናት የሚያበራ። በሰዎች ልብ ውስጥ ለዘመናት የሚኖረው ይህ ድንቅ ተግባር ዛሬ ላይ በአዲስ አበባ ከተማ እውን ሆኗል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከበጎ አድራጊ ባለሀብቶች ጋር በመተባበር የገነባቸውና በአሁኑ ወቅት 29 የደረሱት ተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከላት የዚህ አብነት ናቸው። እነዚህ ማዕከላት መደበኛ የመመገቢያ ስፍራዎች ብቻ ሳይሆኑ፤ ለአረጋውያን፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ቋሚ ገቢ ለሌላቸው እና እጅግ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ነዋሪዎች የህልውና ጋሻና የደግነት መገለጫዎች ናቸው። በተለይም ለሀገርና ለወገን ውለታ የዋሉ ውድ የሀገር ባለውለታዎችንና ራሳቸውን መመገብ የማይችሉ ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን በክብር ለመደገፍ ታልመው የተቋቋሙ ስለመሆናቸውም የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ይገልጻሉ።

አነስተኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች በስፋት በሚኖሩባቸው እና ምቹ በሆኑ ቦታዎች ላይ የተገነቡት እነዚህ የምገባ ማዕከላት በከተማዋ ውስጥ የሚራብ ሰው እንዳይኖር ያግዛሉ። የከተማዋን ውበት በሕንፃዎችና በኮሪደር ልማት ብቻ ሳይሆን፣ በእንዲህ ዓይነት የደግነት ማዕቀፎች የዜጎችን የዕለት ጉርስ በማቅረብና እንባቸውን በማበስ ጭምር መሆኑን እነዚህ ማዕከላት በየቀኑ ምስክርነታቸውን እየሰጡ ይገኛሉ።

የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል በአራዳ ክፍለ ከተማ በሚገኘው በቁጥር አንድ ተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከል ተገኝቶ ያረጋገጠው ሀቅ ይህንኑ ነው። ማዕከሉ ከዕለት ጉርስ በላይ ሰብዓዊ ፍቅርና ተስፋ የሚታደልበት እውነተኛ የሕዝብ ማረፊያ መሆኑን ለመታዘብም ችለናል። ወደዚህ ማዕከል ደጃፍ የዕለት ጉርስ ፍላጋ የሚመጣ ማንኛውም የተቸገረ ሰው በአክብሮት መስተንግዶ ሲያገኝ ተመልክተናል፡፡ ከማዕከሉ ባገኘነው መረጃ መሰረት በበዓላት ወቅት እስከ አንድ ሺህ የሚደርሱ ወገኖች ምገባ የሚያገኙ ሲሆን፣ በመደበኛነት ደግሞ በየቀኑ ከ300 በላይ ወገኖች በምገባ ማዕከሉ ይጠቀማሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት በርካታ አቅመ ደካሞችን፣ አረጋውያንንና ሕፃናትን ያለመታከት እያገለገለ የሚገኘው ይህ ማዕከል፣ ከሚያስተናግዳቸው ወገኖች መካከል አብዛኞቹ በአንድ ወቅት ወጣትነታቸውን፣ ዕውቀታቸውንና ጉልበታቸውን ለሀገራቸው ልማትና ዕድገት የገበሩ ባለውለታዎች መሆናቸው ደግሞ የአገልግሎቱን ክቡርነትና ማዕከሉ የሚወጣውን ታሪካዊ ኃላፊነት ይበልጥ ጎልቶ እንዲታይ ያደርገዋል። ከእነዚህም መካከል የሶስት ልጆች አባት የሆኑት አምሳ አለቃ ማቴዎስ ሶካ ይገኙበታል፡፡ ማዕከሉ ውስጥ በተገኘንበት ወቅት፣ ምሳ ሲበሉ ያገኘናቸውና በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ አንድ ነዋሪው አምሳ አለቃ ማቴዎስ ሀገራቸውን በውትድርና ለ34 ዓመታት አገልግለዋል፡፡ በእርሳቸው ፊት ላይ የሚነበበው እውነተኛ ገጽታም የተረጂነት ሳይሆን ተስፋን ማሳያ ነበር።

በአንድ ወቅት በኑሮ ጫና እና በህመም ምክንያት ተስፋ የመቁረጥ ጥላ አጥልቶባቸው የነበሩት እንደ አምሳ አለቃ ማቴዎስ ያሉ አባቶች ዓይኖች፣ ዛሬ በደስታና በሰላም ብርሃን ተሞልተው አስተውለናል። ከማዕዱ ባሻገር፣ በመንግሥትና በማህበረሰቡ ዘንድ “አለንላችሁ፤ ብቻችሁን አይደላችሁም!” የሚል አጋዥና ደጋፊ ከጎናቸው መኖሩን ሲረዱ የፈጠረባቸው የስነ-ልቦና መረጋጋትና የእርካታ ስሜት በየፊታቸው ላይ ባለ ጥልቅ ፈገግታ በጉልህ ይነበባል። ይህ የምገባ ማዕከል ለነዋሪዎቹ የዕለት ጉርስ ማድረሻ ብቻ ሳይሆን፣ የተረሱ መስሏቸው ለነበሩ ወገኖች ሰብዓዊ ክብራቸው የታደሰበት፣ የተስፋ ስንቅ የተሰነቀበት የፍቅር አጸድ መሆኑን ከተመጋቢዎቹ ገጽታ ላይ በግልጽ ለመታዘብ ችለናል።

ከምገባ ማዕከሉ ተጠቃሚዎች መካከል አንዱ የሆኑት በዕድሜ ጠና ያሉና ለእግሮቻቸው ድጋፍ ክራንች የሚጠቀሙት አቶ ጋሹ ደሴ የሚናገሩት ታሪክም የዚሁ እውነታ ማሳያ ነው። ቀደም ሲል በገጠር አካባቢ በእርሻ ስራ ይተዳደሩ የነበሩት እኚህ አባት፣ በድንገተኛ ህመም ምክንያት እግራቸው በመጎዳቱና የመንቀሳቀስ አቅማቸውን በማጣታቸው ሕይወታቸው ፈታኝ ወደሆነ አቅጣጫ ተቀይሮ ነበር። አሁን ግን አዲስ አበባ ውስጥ እየኖሩ፣ የእለት ጉርሳቸውን ለማግኘት ከባድ በሆነበት ወቅት ላይ ይህ የምገባ ማዕከል መከፈቱ ታላቅ የብርሃን ጭላንጭል ሆኖላቸዋል። "ካለብኝ የጤና ችግር አንጻር ማዕከሉ ትልቅ እረፍት ሰጥቶኛል" ብለዋል።

ማዕከሉ ለእሳቸውና መሰል ችግር ላይ ላሉ ወገኖች ያበረከተውና ወደፊትም የሚያበረክተው ጥቅም በቀላሉ የሚገመት እንዳልሆነ ይናገራሉ። “እኔ ዛሬ እዚህ መጥቼ ተጠቅሜያለሁ፤ ወደፊትም እጠቀማለሁ ነገም ተመግቤ እንደማድር እርግጠኛ ነኝ” በሚል ስሜት፣ ማዕከሉ የዕለት ምግብ ከማቅረብ ባለፈ በውስጣቸው የተስፋ ስሜት እንደዘራባቸው ይመሰክራሉ። ባገኙት መስተንግዶ ሙሉ በሙሉ መርካታቸውን የገለጹት እኚህ አባት፣ በከተማዋ መሰል ማዕከላት መኖራቸው አቅመ-ደካሞችንና ጧሪ ደጋፊ የሌላቸውን ዜጎች ለመደገፍ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በአንደበታቸው መስክረዋል።

የአራዳ ክፍለ ከተማ ነዋሪዋ ወይዘሮ አይሻ ሺፋ በበኩላቸው፣ ከዓመታት በፊት በነበራቸው የስራ ፍላጎትና ተነሳሽነት፣ በመጀመሪያው የወረዳ አንድ የሴፍቲኔት ምዝገባ ወቅት ተመዝግበው በሻይ ንግድና በተለያዩ የጉልበት ስራዎች ይረዱ እንደነበር ያስታውሳሉ። ነገር ግን፣ ጊዜ እያለፈ ሲሄድ ያጋጠማቸው የጤና መታወክ፣ የልብ ሕመም እና ተያያዥነት ያለው የጀርባ ህመም ከባድ ስራዎችን እንዳይሰሩ አግዷቸዋል። የገቢ ምንጫቸውም ተቋረጠ፤ ለራሳቸውም ሆነ ለቤተሰባቸው መትረፍ አቅቷቸው በነበሩበት የጭንቀት ወቅት፣ ይህ የምገባ ማዕከል ደርሶላቸው የሕይወት ዋስትና እንደሆናቸው ተናግረዋል።

“በጣም በቸገረኝ ጊዜ ነው ይሄንን ዕድል ያገኘሁት” የሚሉት ወይዘሮ አይሻ፣ በአሁኑ ወቅት ምንም ዓይነት ቋሚ የገቢ ምንጭ ባይኖራቸውም፣ በማዕከሉ የሚቀርበው ምግብ ካለባቸው የጤና እክልና የኑሮ ጫና አንጻር ትልቅ እረፍትና መረጋጋትን እንደሰጣቸው ነግረውናል።

ያነጋገርናቸው የማዕከሉ ተጠቃሚዎች ለከተማዋ ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ ያላቸውን አክብሮትና ምስጋና ሲገልጹ፣ ከንቲባችንን በጣም ነው የምናመሰግነው፤ እርሳቸው ይህንን ባያደርጉልን ኖሮ እኛ የት እንወድቅ ነበር? በማለት በምገባ መርሃ-ግብሩ ሕይወታቸው ለተቀየረ በርካታ ደካማ እናቶችና አረጋውያን ድምፅ ሆነዋል። የቁጥር አንድ የተስፋ ብርሃን ምገባ ማዕከል የምግብ ጥራት ቁጥጥር ባለሙያ ራሄል ይግለጡ እንደገለጹት፣ የአገልግሎቱ ዋነኛ ዓላማ ደካማ እናቶችንና፣ አረጋውያን በአግባቡ ማስተናገድ ነው፡፡ በማዕከሉ የሚሰጠው ምላሽና የእለት ከእለት እንክብካቤ ሰብዓዊ ክብርን በጠበቀ መልኩ የሚከናወን በመሆኑ፣ ህብረተሰቡ ለአገልግሎቱ ያለው አመለካከትና ምስጋና እጅግ ከፍተኛ መሆኑን ያስረዳሉ። በማዕከሉ የሚዘጋጀው ምግብ ጥራቱንና ንጽህናውን የጠበቀ እንዲሆን ከፍተኛ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል ያሉት ባለሙያዋ፣ በአሁኑ ወቅት በአግባቡና ያለመጉላላት ለማስተናገድ ሠራተኞቹ በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜትና በትጋት እንደሚሰሩም ገልጸዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ 29ኛውን የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከል መርቀው ለአገልግሎት ክፍት ባደረጉበት ወቅት ባስተላለፉት መልዕክት፣ መዲናዋን ውብ ገፅታ ከሚያላብሱ ግዙፍ የልማት ውጤቶች ባሻገር፣ የዜጎችን ህይወት በዘላቂነት የሚቀይሩ ስኬታማ ሰው ተኮር ስራዎች በትኩረት እየተሰሩ መሆኑን ገልጸዋል። የምገባ ማዕከላትም የአገልግሎት አቅምና ተደራሽነትን በከፍተኛ ደረጃ በማስፋት፣ በተለይም ጧሪና ደጋፊ የሌላቸውን ውድ የሀገር ባለውለታዎችና አቅመ-ደካሞችን በክብር ለመንከባከብ ትልቅ አቅም እንደሚሆን አስገንዝበዋል።

የማዕከላቱ በተለይ ቋሚ ገቢ የሌላቸውን፣ የጎዳና ተዳዳሪዎችንና ዝቅተኛ የዕለት ገቢ ሰራተኞችን ከከፋ ርሃብና ከምግብ እጥረት መታደጋቸውንና ለከተማ ነዋሪው መሰረታዊ የህልውና ዋስትና መሆናቸውን የምርምር ውጤቶች ያረጋግጣሉ። የከተማ ነዋሪዎች የምገባ ማዕከላት ከምግብ አቅርቦት ባለፈ ማህበራዊ ፋይዳቸው የጎላ መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ። ማዕከላቱ አቅመ-ደካማ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች እርስ በርስ የሚገናኙበት፣ የሚወያዩበትና የብቸኝነት ስሜትን የሚያስወግዱበት መድረክ ሆነው ያገለግላሉ።

# የበዓላቱ ተጨማሪ ድምቀት

**• የኮሪደር ልማቱ የፈጠረው ውብና ምቹ ገፅታ በከተማዋ የሚከናወኑ ኃይማኖታዊ እና ህዝባዊ በዓላትን አይረሴ ትዝታ እንደሚያጎላ ተገልጿል**

**በመለሰ ተሰጋ**

አሁን አዲስ አበባ እንደ ፅጌሬዳ ፈክታለች፤ አዲስ ውበትን፣ ማራኪ ገፅታን ተላብሳለች፡፡ ከስሟና ከታሪኳም ጋር ታርቃለች፡፡ ለበርካቶችም የዐይን ማረፊያ ሆናለች፡፡ አህጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ ሁነቶችን በብቃት ማስተናገድም ጀምራለች፡፡

በዚህ ላይ ደግሞ ኃይማኖታዊ እና የህዝብ በዓላትን ከአዲስ አበባ ውብ ጎዳናዎች ጋር መመልከት ልብን ያሞቃል። አዲስ አበባን እንደ አዲስ በወለደው ፅዱ የህዝብ መዝናኛ ቦታዎች፣ የህፃናት መጫወቻዎች፣ ምቹና ሰፋፊ የእግረኛና የተሽከርካሪ መንገዶች ከሰማይ ጠቀስ ሕንፃዎቿ ጋር ተዳምረው ከተማዋን እንደ ሙሽራ አስውበዋታል፡፡

በከተማዋ የተገነቡት የአውቶብስና የታክሲ ተርሚናሎች፣ የምድር ውስጥ ፓርኪንግ፣ የታክሲ ማውረጃና መጫኛ ቦታዎች፣ የመሮጫ ትራኮች፣ የእግረኛ እና የሳይክል መንገዶች እንዲሁም ዘመናዊ የእግረኛ መሸጋገሪያ ድልድዮች የትራፊክ ፍሰቱን ጤናማ ያደረጉና የትራንስፖርት አገልግሎትን ያሻሻሉ ናቸው፡፡ በኮሪደር ልማቱ የተሰሩት መሰረተ ልማቶች ለከተማዋ ነዋሪዎች ለበዓላቸው ድምቀት፣ ለድካማቸው እረፍት እና ለገቢያቸውም ምክንያት ሆነዋል፡፡

በእርግጥም “ስለ አዲስ አበባ አስገራሚ ለውጥ ለመናገር ምስክር አያሻም፤ ምክንያቱም ከተማዋ እንደስሟ አበባ እየሆነች ስለመምጣቷ የተመለከታት ሁሉ ምስክር ነው” ይላሉ የመዲናዋ ነዋሪ አቶ አህመድ ከማል፡፡ በመዲናዋ ከ35 ዓመታት በላይ እንደኖሩ የነገሩን አቶ አህመድ እንደሚሉት ከተማዋ ቀደም ባሉት ዘመናት ነግዶ ለማትረፊያ እንጂ ያን ያህል ለመኖሪያ ምቹ አልነበረችም፡፡

ምክንያቱም ንፅህናቸውን ያልጠበቁ መንገዶች እና መንደሮች በብዛት ከመኖራቸውም በላይ በአንዳንድ አካባቢዎች ክረምት በመጣ ቁጥር አሊያም ሙቀቱ በሚያይልባቸው ወቅቶች ወረርሽኞች ጭምር ይከሰቱ እንደነበር አስታውሰው፣ አሁን በከተማዋ እየተከናወነ ባለው ልማት እነዚህ ችግሮች እየተፈቱ መሆናቸውን ያስታውሳሉ፡፡

አሁን ከተማዋ ለንግድ ብቻ ሳይሆን ለመኖሪያም የምትመረጥ፣ ጎዳናዎቿ የሚያምሩ ውብ ከተማ ሆናለች፡፡ በዚህ ላይ እንደ አረፋን የመሳሰሉ በዓላትን ህዝቡ በነቂስ ወጥቶ ሲያከብር ከህብረ ቀለማቱ ውበት ጋር የተዳመረ ገፅታዋ ጎልቶ ሲወጣ እጅጉን ታምራለች ይላሉ አቶ አህመድ፡፡

ወይዘሮ ፎዚያ አሕመድ በበኩላቸው፣ የአዲስ አበባ ውበት ነግቶ በጠባ ቁጥር አዲስ እየሆነ ነው፡፡ ከመዋባቸው የተነሳ አንዳንድ የማውቃቸው ስፍራዎች ጭምር ግር እያሉኝ መጥተዋል ይላሉ፡፡ ይህን መሰል ለውጥ ከእኛ ባሻገር ለልጆቻችን እና ለልጅ ልጆቻችን ትልቅ ሀብት እንደማስቀመጥ ነው፡፡ በተለይም እንደ አረፋን እና ኢድ አል ፈጥርን የመሳሰሉ ኃይማኖታዊም የሆኑ ሌሎች በዓላትን በአደባባይ ወጥተው ሲያከብሩ የከተማዋ አሁናዊ ገፅታ ደስታቸውን አይረሴ



ፎቶ- ከገፀ ድር

በቴዎድሮስ አደባባይ አካባቢ የተከናወነው የኮሪደር ልማት ስራ ለአደባባይ በዓላት ተጨማሪ ድምቀት ይፈጥራል

እንደሚያደርገውም አጫውተውናል፡፡

የፎክሎር ባለሙያው አቶ ግዛው ማሞ እንደሚሉት፣ በኢትዮጵያ የሚከበሩ የአደባባይ በዓላት በዛ ያሉ ቢሆኑም በተለይ እንደ አረፋ፣ ኢድ አል ፈጥር፣ ጥምቀት፣ መስቀል፣ ኢሬቻ እና ሌሎቹም ኃይማኖታዊና ባህላዊ በዓላት በበርካታ የሀገሪቱ ክፍሎች በድምቀት የሚከበሩና የማህበረሰቡን እሴት በጉልህ የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡

በእነዚህ በዓላት የሚታደሙ ኢትዮጵያውያን በተለይ በአዲስ አበባ ጎዳናዎች እና አደባባዮች ሲታዩ ህብረ ብሔራዊነት ነፍስ ዘርቶ የሚደምቅበት፣ የማህበረሰቡ የተለያዩ ውብ ኃይማኖታዊ ስርዓቶች፣ ባህላዊ አልባሳት እና ቀልብን በሚገዙ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች በኮሪደር ልማቱ ውብ ገፅታን በተላበሱት የመዲናዋ አደባባዮች የኢትዮጵያውያንን መልክና ልክ አጉልተው ሲያሳዩ በርካታ ጎብኚዎችን ቀልብ ይስባሉ፡፡

አዲስ አበባ እንደ አዲስ ውበቷ እየፈካ፣ ጎዳናዎቿ እንደ ፅጌሬዳ አበባ የሚያሳሱ እየሆኑ መጥተዋል፡፡ ታዲያ በእነዚህ ውብ ጎዳናዎችና አደባባዮች ላይ እንደ አረፋ እና ኢድ አል ፈጥርን የመሳሰሉ ኃይማኖታዊና የህዝብ በዓላት ሲከበሩ ለከተማዋ ተጨማሪ ውበትን ለበዓላቱ ደግሞ ድርብ ድምቀትን ይሰጣሉ፡፡

ኃይማኖታዊም ሆነ የህዝብ በዓላት ህዝቡ በክት ልብሱ ደምቆ፣ መልካም መንፈስን ታጥቆ እና ከቤቱ ወጥቶ የሚያከብራቸው በዓላት በመሆናቸው በህብረ ቀለማት ያሸበረቁ ናቸው፡፡ ታዲያ የበዓላቱና የአደባባዮቹ ድምቀት አብሮ ሲደመር ለከተማዋ ትልቅ ፍካትን ይፈጥራሉ፡፡ የማህበረሰቡም መልካም እሴቶች እንዲጎለብቱም ዕድል ይሆናሉ ይላሉ፣ የፎክሎር ባለሙያው አቶ ግዛው ማሞ፡፡

የኢትዮጵያውያን ውብ ባህላዊ እሴቶች እንዲህ ደምቀው በአደባባይ ሲታዩ፣ ለሌላው ዓለም የህዝቡን መልካም ገፅታ እንዲሁም የሀገርን ሁለንተናዊ ከፍታ ያሳያሉ፡፡ እየለማ ያለው ግዑዝ የሆነው ቦታ ብቻ ሳይሆን የማህበረሰቡም ነባር እሴት በመሆኑ በማህበረሰባዊ፣ በኢኮኖሚያዊም ሆነ በሌሎች ዘርፎች ያለው ፋይዳ ከፍ ያለ ስለመሆኑም ጠቅሰዋል፡፡

ኃይማኖታዊና ባህላዊ በዓላት ሰዎች ልባቸውንም፣ ልብሳቸውንም አፅድተው በህብረት የሚያከብሯቸው በመሆኑ ንፁህ ስፍራዎችም ያስፈልጓቸዋል፡፡ የኮሪደር ልማቱ ያስገኘው አንዱ በረከትም ለእነዚህ በዓላት ምቹ ማክበሪያ ቦታዎችን ነው፡፡ በመሆኑም የማህበረሰቡን ስጋና ነፍስ ለማስደሰት ትልቅ አቅምን ፈጥሯል። ይህም ለከተማዋ ተጨማሪ ውበት ለበዓላቱም አይረሴ ድምቀት ነውም ብለዋል፡

አክለውም፣ ማህበረሰቡ በእነዚህ ስፍራዎች የአደባባይ በዓላትን ያለምንም መጨናነቅ በፍፁም ደስታና ውበት ሲያከብር ሀገራዊ ኩራት እንዲሰማው ይሆናል፡፡ የተሰራው ልማት ለእርሱ እንደሆነም በሚገባ እንዲረዳው፣ ልማቱንም እሴቱንም እንዲጠብቅና እንዲያከብር ያነሳሱታል፡፡

በርካታ ሀገራት ጎዳናዎችን፣ አደባባዮችን እና መናፈሻዎችን ወደ ደማቅ የበዓል ማክበሪያ ማዕከልነት በመቀየር ባህሎቻቸውን እያሳደጉ እና እያበለጸጉ ነው ይላል የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ተቋም (ዩኔስኮ) The Impact of Heritage Conservation on Cultural Development በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ መስከረም 26 2025 ይፋ ያደረገው መረጃ፡፡

ለአብነትም ጃፓን፣ ስፔን እና ዩናይትድ ስቴትስ፣ ህዝባዊ በዓላቶቻቸው ከፍ ብለው እና ደምቀው እንዲታዩ ጎዳናዎቻቸውን እና አደባባዮቻቸውን በማስዋብ ዓለም አቀፍ ትኩረትን መሳብ ችለዋል፡፡

ጃፓን ቶኪዮን በመሳሰሉ ከተሞቿ በየዓመቱ የሚከበሩት በዓላቶቿን በሰፋፊ አደባባዮች፣ መንገዶችና ፓርኮች ላይ የበዓሉ ታዳሚዎች በአበቦች፣ በዛፎች እና በውብ ፏፏቶዎች ደስ ብሏቸው እንዲያሳልፉ ታደርጋለች፡፡ ይህም በመላው ዓለም በዓላቱ ትኩረት እንዲስቡ ምክንያት እንደሆነም በመረጃው ተመላክቷል፡፡

በዓለም ዙሪያ የባህል እና የፈጠራ ኢንዱስትሪዎች በየዓመቱ ከ2 ነጥብ 25 ትሪሊዮን ዶላር በላይ ያመነጫሉ። ይህም ወደ 30 ሚሊዮን ለሚሆኑ ዜጎች የስራ ዕድልም ይፈጥራል፡፡ እንደ መረጃው ከሆነ የባህል ቱሪዝም ከዓለም ጉዞዎች ውስጥ 40 በመቶውን ይሸፍናል፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ የኮሪደር ልማቱ የፈጠረው ውብና ምቹ ገፅታ በየዓመቱ ለሚከናወኑ ኃይማኖታዊ እና ህዝባዊ በዓላት አይረሴ ትዝታን እና ተናፋቂ ድባብን ከመፍጠራቸው ባሻገር ከተማዋ በባህል ቱሪዝም ዘርፍም የበለጠ ተጠቃሚ የምትሆንበትን ዕድልም የሚፈጥር ነው፡፡

የከተማ ልማት ባለሙያው እና አማካሪ ኢንጂነየር በሱፈቃድ አየለ እንደሚሉት ስለ ዘመናዊ ከተማ ልማት ስናስብ ስለ መሠረተ ልማት ብቻ ሳይሆን ስለ የማህበረሰቡን እሴት፣ ወግና ልማድ ታሳቢ ማድረግን፣ ማህበራዊ ግንኙነትን ማጠናከርና የመሳሰሉትንም ትኩረት ሰጥቶ መስራት ምን ያህል ፋይዳ እንዳለው የአዲስ አበባ አሁናዊ ልማት ምስክር ነው፡፡

ለአብነትም ለተሽከርካሪ ብቻ ሳይሆን ለእግረኞችም ተስማሚ የሆኑ መንገዶችን፣ መብራቶችን እና አረንጓዴ ቦታዎችን ከሌሎች መሰረተ ልማቶች ጋር አዋህዶ መስራት ከዘመናዊ የከተሜነት እሳቤ ባሻገርም ምን ያህል በማህበረሰቡ ዘንድ እርካታን እንደሚፈጥር እና ማህበራዊ ትስስርን እንደሚያጎለብት በኮሪደር ልማቱ መመልከት ችለናል፡፡

በከተማዋ የተሰሩ መናፈሻዎች፣ ፋውንቴኖች፣ ፕላዛዎች፣ የእግረኛ መንገዶች ከመዝናኛነት ባለፈ ለነዋሪዎቹ የገቢ ምንጭ እያስገኙ ነው፡፡ ለአብነትም በፎቶ ማንሳት ሙያ የተሰማሩ ወጣቶችን መጥቀስ እንችላለን፡፡

በ4 ኪሎ ፕላዛ ላይ ፎቶ ግራፍ በማንሳት የሚተዳደረው ወጣት መኮንን ሲሳይ የኮሪደር ልማቱ ለእሱና ለጓደኞቹ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ይዞለት የመጣ መሆኑን ይገልጻል፡፡ በ500 ብር ወርሃዊ ደመወዝ ተቀጥሮ ፎቶ ግራፍ የማንሳት ስራውን የጀመረው ወጣት መኮንን አሁን በ100 ሺህ ብር ዘመናዊ ካሜራ በመግዛት በ4 ኪሎ ፕላዛ አካባቢ ፎቶ ግራፍ በማንሳት ህይወቱን እየመራ ይገኛል፡፡

ከዓመት በፊት ሸራተን ሆቴል አካባቢ ፎቶ ሲያነሳ እንደነበር ያጫወተን ወጣት መኮንን ኮሪደር ልማቱ በፈጠረለት ተጨማሪ አቅም አሁን ከ4 ኪሎ ፕላዛ እስከ ፒያሳ ድረስ ባለው መንገድ ነዋሪዎችን ፎቶ በማንሳት ገቢ እያገኘ ነው፡፡

እሱ እና ጓደኞቹ በአዲስ አበባ ፓርኮች አስተዳደር ስምንት ወጣቶች በመሆን በ“ሙሴ እና አሊያድ ጓደኞቻቸው ፎቶ አንሺ ማህበር” ተደራጅተው ፎቶ ግራፍ እያነሱ ሕይወታቸውን በተሻለ መልኩ እየመሩ ስለመሆኑም አጫውተውናል፡፡

በእርግጥም የኮሪደር ልማቱ ያስገኛቸው በረከቶች ነዋሪዎች ደስታቸውን የሚያጣጥሙባቸው፣ ማህበራዊ ሕይወታቸውን የሚያጎለብቱባቸው እና ኢኮኖሚያቸውን ከፍ የሚያደርጉባቸው የለውጥ መስኮት መሆናቸውን በርካቶች በመመስከር ላይ ናቸው፡፡

# የአረፋ እሴቶች ከመንፈሳዊ በረከት እስከ ብሔራዊ አንድነት

**በአብርሃም ገብሬ**

የዒድ አል አድሃ- አረፋ በዓል በታላቅ መስዋዕትነት፣ በጽናት እና በተግባራዊ እኩልነት ላይ የተመሰረተ ጥልቅ መንፈሳዊና ማህበራዊ አንድምታ ያለው በዓል ነው። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የእስልምና እምነት ተከታዮች ሳይለያዩ በአንድነት የሚያከብሩት ይህ በዓል፣ የሰው ልጅ የእርስ በእርስ መደጋገፍና መደማመጥ በተግባር የሚታይበት ታላቅ ዕለት ነው። በዓሉ በውስጡ የያዛቸው የመስዋዕትነት፣ የመተሳሰብ፣ የይቅርታ እና የርህራሄ እሴቶች የሰው ልጆችን ትስስር የሚያጠናክሩ ከመሆናቸውም በላይ፣ ካለፈ ቁርሾ ይልቅ ለወደፊት ዕርቅና ሰላም ቅድሚያ መስጠት እንደሚገባ የሚጠቁሙ ህያው አስተምህሮዎች ናቸው። የአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍልም የአረፋ በዓል አንኳር እሴቶችን መነሻ በማድረግ የታሪክ ተመራማሪ የሆኑትን ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚልን በማነጋገር አጭር ዳሰሳ አድርጓል፡፡

ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል በታሪክ ምርምር ረገድ ካላቸው ሰፊ እውቀትና ልምድ በመነሳት፣ የአረፋ በዓልን ኃይማኖታዊ ፋይዳ ብቻ ሳይሆን ማህበራዊና ታሪካዊ አንድምታውን ለዝግጅት ክፍላችን በዝርዝር አብራርተዋል፡፡ በተለይም የግል ትውስታቸውን ከበዓሉ መንፈሳዊ እሴቶች ጋር በማቆራኘት፣ በዓሉ የግል በረከት ብቻ ሳይሆን ለህዝቦች ትስስርና ለአብሮነት ያለውን ሚና በአጽንዖት ገልጸዋል፡፡ እሳቸው የአረፋ በዓል የሚያስተምረን የመስዋዕትነት እና የታማኝነት እሴት እንደ ሀገር በጋራ ለምንቆምላቸው ጉዳዮች ትልቅ ስንቅ የሚሆን ነው፡፡ በተለይም እንደ ቀይ ባህር ባሉ ስትራቴጂካዊና ብሔራዊ ፋይዳ ባላቸው የጋራ አጀንዳዎች ላይ ብሔራዊ መግባባትን መፍጠር ለኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምና እድገት ወሳኝ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡ የታሪክ ምሁሩ እንደነዚህ ያሉ በዓላት ልዩነትን ለማጥበብና የጋራ ጥቅምን ለማስከበር እንደ ትልቅ አጋጣሚ ልንጠቀምባቸው እንደሚገባ በማሳሰብ፣ ወቅታዊና ታሪካዊ ክስተቶችን ከሀገር ግንባታ ሂደት ጋር አዛምደው በዝርዝር አጫውተውናል፡፡

## የአረፋ በዓል አንኳር እሴቶችና ሀገራዊ ፋይዳቸው

ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል የዒድ አል አድሃ- አረፋ በዓል በታሪክ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው የመስዋዕትነት እና የታዛዥነት ተምሳሌት ነው ይላሉ። ይህ በዓል በውስጡ የያዛቸው እሴቶች ከአንድ እምነት ተከታዮች አልፈው፣ እንደ ሀገር በጋራ የሚያስተሳስሩንን አንኳር እሴቶች በውስጡ በመያዙ ፋይዳው መልከ ብዙ ነው፡፡ በበዓሉ የሚታየው የመረዳዳት እና የርህራሄ መንፈስ፣ ዜጎች በልዩነቶቻቸው ውስጥ ሆነው ለጋራ ዓላማ እንዲሰለፉ የሚያስችላቸው አቅም አለው ብለዋል።



ፎቶ- ከፋይል

የታሪክ ተመራማሪ ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል

የታሪክ ተመራማሪው አደም እንደተናገሩት፣ በዓሉ ከታላቁ የሐጅ ሥነ-ሥርዓት ጋር የተሳሰረ መሆኑንና ይህም የሰው ልጆች ሁሉ የእኩልነት መድረክ መሆኑን ያመለክታል። በዓረፋ ተራራ ላይ የሚደረገው ስብስብ የንጉሥ፣ የፕሬዝዳንት፣ የጄነራልም ሆነ የሰፊው ህዝብ ልዩነት የማይታይበት መሆኑን ያወሱት ምሁሩ፣ "ንጉሡም ይሁን ፕሬዝዳንት፣ ጄነራልም ይሁን መኮንን ሁሉም በእኩልነት አንዲት ሸርጥና አንዲት ልብስ ለብሰው የሚውሉበት እለት ነው" በማለት የሰው ልጅ በመሰረታዊነት አንድ መሆኑን አስረድተዋል።

የዒድ አል አድሃ- አረፋ በዓልን መነሻ በማድረግ የሚከወነው የሐጅ ሥነ-ሥርዓት ሌላው መገለጫ የሰው ልጅ ለፈጣሪው ያለውን ፍጹም ታዛዥነትና ሥነ-ምግባር ማሳየቱ ነው። ረዳት ፕሮፌሰሩ አያይዘው፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ካሉበት ርቀው፣ ስራቸውንና ቤተሰባቸውን ትተው በአንድ ቦታ መሰብሰባቸው ከፍተኛ የዲሲፕሊን ውጤት ነው። "ንብረቱን እና ስራውን ትቶ፣ ከቤተሰቦቹ ርቆና በአንድነት ተሰባስቦ በዕለቱ 'አቤት' ብለው ጌታቸውን ይጠይቃሉ" በማለት፣ ለትልቅ ግብ ሲባል ጊዜያዊ የግል ጥቅሞችንና ምቾቶችን የመተው (የመስዋዕትነት) አስፈላጊነትን አብራርተዋል፡፡

> **"በኃይማኖታዊ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ የሚታየው የአንድነትና የጋራ መደማመጥ፣ ወደ ሀገራዊ ስትራቴጂካዊ ጥያቄዎች ሲመጣም የማይታለፉ የሚመስሉ መሰናክሎችን ለማለፍና የሀገርን ጥቅም ለማስከበር ትልቁ መሣሪያ ነው"**

ምሁሩ የአረፋን ተራራ ታሪካዊ አመጣጥ ከአደምና ሐዋ ዳግም መገናኘት ጋር በማያያዝ በዓሉን የዕርቅና የይቅርታ ተምሳሌት አድርገው ያቀርቡታል። አደምና ሐዋ ከገነት ከወጡና ከተለያዩ በኋላ በምድር ላይ የተገናኙበትና የፈጣሪን ምሕረት የተቀበሉበት መሆኑን ሲያብራሩ፣ "አረፋ ከስያሜው አደምና ሐዋን… አወቅሽኝ ወይ? አወቅከኝ ወይ? ተባብለው የተገናኙበት ቦታ ነው" በማለት፤ የጥል መጨረሻና የፍቅር መጀመሪያ መሆኑን ገልጸውልናል። ይህ የይቅርታ እሴት ለሀገራዊ መግባባትና ለዘላቂ ሰላም ግንባታ እንደ መሰረት ሊያገለግል የሚችል ሲሆን፣ ቂምን ሽሮ ለመደማመጥ ምቹ መንገድ ይከፍታል በማለት ተናግረዋል።

በተጨማሪም ምሁሩ የዒድ አል አድሃ- አረፋ በዓል አላህ ለሰው ልጆች ምህረቱን የሚቸርበት ልዩ ቀን መሆኑን ያሰምሩበታል። በዕለቱ አማኞች ንብረታቸውንና ቤታቸውን ትተው በአንድ ሜዳ ላይ ተሰብስበው አምላካቸውን ይለምናሉ። ረዳት ፕሮፌሰሩ ይህንን መንፈሳዊ ድባብ ሲገልጹ "አላህ 'እነዚህን ባሮቼን እዩአቸው፤ በምድር ላይ ተሰብስበው ንብረታቸውን፣ ስራቸውን፣ ቤታቸውን ትተው እኔን ምህረት እየጠየቁ ስለሆነ ዛሬ ምህረት አድርጌላቸዋለሁ' ብሎ የሚመሰክርበት እለት ነው" ይላሉ።

ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል አክለውም፤ በዓሉ ከኃይማኖታዊ ይዘቱ ባለፈ የሰው ልጆች ሁሉ የእኩልነትና የአንድነት መድረክ መሆኑን አብራርተዋል። የዒድ አል አድሃ- አረፋ በዓል ለሰው ልጆች ሁሉ የሚያስተላልፈውን የእኩልነትና የአንድነት መልዕክት ያጎላሉ። በበዓሉ የሚደረገው ሥነ ስርዓት የሰው ልጅን መዳረሻና ከሞት በኋላ ያለውን ሁኔታ የሚያስታውስ መሆኑን ይገልጻሉ። ይህንንም ሲያጠቃልሉ "ይህ ጸሎት አንድነትን፣ ህብረትን ነው የሚያሳየው… ሀብት ጥቅም የለውም፣ ዝና የለውም፤ በመሆኑም ሰው ሁሉ እኩል መሆኑን የሚያስተምር ነው" በማለት፤ በዓሉ ከመንፈሳዊነቱ ባለፈ ማህበራዊና ሰብዓዊ ፋይዳው የላቀ መሆኑን ተናግረዋል።

የታሪክ ምሁሩ አጽንኦት የሰጡት አንዱ ጉዳይ፣ የሰው ልጅ በሙሉ ከአንድ ምንጭ የተገኘ መሆኑንና ልዩነቶች ለውበትና ለዕውቀት እንጂ ለጠብ ሊሆኑ እንደማይገባ ነው። ፈጣሪ ሰውን ሁሉ እኩል አድርጎ መፍጠሩን፣ እንዲሁም ለሰው ልጅ አስፈላጊውን ሁሉ መለገሱን በመጥቀስ፣ ይህንን ፀጋ ለበጎ ተግባር ማዋል እንደሚገባ የበዓሉን አንኳር እሴቶች መነሻ በማድረግ ይመክራሉ። ምሁሩ አክለውም "ሰው ማለት የፈጣሪ ተወካይ ነው፤ በመሆኑም በመሬት ላይ፤ ትልቅ አደራ የተረከበ ነው"። በመሆኑም የዒድ አል አድሃ- አረፋ በዓል ትርጉም የሚኖረው እነዚህን የመከባበር፣ የመረዳዳትና የእኩልነት እሴቶችን በተግባር ስንተረጉማቸው መሆኑን ምሁሩ በአጽንኦት ገልጸዋል።

ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል በሀገር ውስጥና በተለያዩ የዓለም ሀገራት ያሳለፏቸውን የዓመታት ተሞክሮዎች መነሻ በማድረግ፣ የዓረፋ በዓል በየትኛውም አውድ ቢከበር መሰረታዊ ይዘቱ አንድ መሆኑን ያስረዳሉ። በዓሉ ለዘመናት የዘለቁ ትውስታዎችን የሚያጭር ከመሆኑም በላይ፣ አማኞች "እኔ እበልጥ" የሚል የፉክክር መንፈስን አስወግደው በፈጣሪ ፊት በእኩልነት የሚቆሙበትና ምህረትን የሚማጸኑበት ቅዱስ ዕለት ነው። እንደ ምሁሩ ገለጻ፣ ይህ ዕለት የግል መንፈሳዊ እርካታ የሚገኝበት ብቻ ሳይሆን፣ የመስዋዕትነትን ትርጉም በተግባር በመተርጎም ለሌሎች ርህራሄ የሚታይበትና የእርስ በእርስ መደማመጥ ባህል የሚጎለብትበት ልዩ አጋጣሚ ነው።

ይህንን መንፈሳዊ እሴት ከኢትዮጵያዊያን ማህበራዊ ህይወት ጋር በማቆራኘት፣ የመረዳዳት ባህል በውስጣችን ያለ እሴት መሆኑን የታሪክ ተመራማሪው ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል ያነሳሉ። ሆኖም እንደ ዓረፋ ባሉ ታላላቅ በዓላት ወቅት ለተቸገሩ ወገኖች

ወደ ገጽ 20 ዞሯል

# በባዶ . . .ከገፅ 1 የዞረ



ፎቶ- ከፋይል
የተማሪዎች ምገባ መርሃ ግብሩ ትውልድ ተሻጋሪ ውጤት እያመጣ ነው



ፎቶ- ከፋይል
ከንቲባ አዳነች አቤቤ በተማሪዎች ምገባ መርሃ ግብር ላስመዘገቡት ስኬት እ.ኤ.አ በ2022 የሚላን የከተማ ምግብ ፖሊሲ ስምምነት ሽልማትን ሲቀበሉ

ይሁን እንጂ የትምህርት ክፍለ ጊዜው መጠናቀቁንና የምሳ ሰዓት መድረሱን የሚያስታውሰው የደወል ድምፅ ሲሰማ ፈቃዱ ጓደኞቹ ዘወትር ምሳቸውን ወደሚመገቡበት ስፍራ አይሄድም። ይልቁንም የምሳ ሳህኑን እንደያዘ በግቢው ጥግ ወዳለችው ዛፍ ጥላ ስር ብቻውን ያመራል። ይህን ከሌሎች ተማሪዎች የተለየ የዘወትር ተግባር በተደጋጋሚ ይመለከቱ የነበሩት መምህሩ፣ ተማሪ ፈቃዱ ወዳረፈባት ዛፍ ስር አቀኑ፤ ብቻውን የተቀመጠውን አዳጊ ተጠግተው የምሳ ዕቃውን ሲከፍቱት ግን ውስጡ ምንም ምግብ አልነበረም፤ ባዶ ነበር! ፈቃዱ ጓደኞቹ "ምሳ ዕቃ አልያዝክም" ብለው እንዳያገልሉትና እንዳያፍር ብቻ ነበር ባዶ ምሳ ዕቃ ተሸክሞ ወደ ትምህርት ቤት የሚያቀናው። ከሰዓት በኋላ ባለው ክፍለ-ጊዜ፣ የርሃብና የድካም ስሜት የሚጠናበት ፈቃዱ በክፍል ውስጥ ተዝለፍልፎ መውደቅ በተደጋጋሚ የሚያጋጥመው ክስተት ነበር።

ይህ ታሪክ የፈቃዱ ብቻ አልነበረም፤ የትምህርት ቤት ምገባ ከመጀመሩ በፊት በከተማችን ትምህርት ቤቶች ውስጥ የነበረው የችግር ጥልቀት ማሳያ እንጂ። ተማሪዎች ምግብ ባለመመገባቸው ምክንያት በክፍል ውስጥ ተዝለፍልፈው መውደቅ፣ ለትምህርታቸው ትኩረት ማጣት፣ በዚህም ሳቢያ የውጤት መቀነስ፣ መጠነ-መድገም፣ መጠነ-ማቋረጥና መጠነ-ማርፈድ በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መሄዱ የከተማ አስተዳደሩን አስገዳጅና አስቸኳይ ምላሽ እንዲሰጥ ያስገደደው መነሻ ነበር።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተጀመረው የተማሪዎች ምገባ ፕሮግራም በከተማዋ ትምህርት ቤቶች መጀመር እንደ ፈቃዱ ያሉ አዳጊዎችን የየዕለት ጭንቀት አቅልሏል፤ የእናቶችን እምባ አብሷል። ይህ ተግባር ተማሪዎችን የመመገብ ተራ የበጎ አድራጎት ስራ አይደለም፤ ይህ የከተማዋን የትምህርት ጥራት የሚቀይር፣ ማህበራዊ ፍትሕን የሚያሰፍን እና የነገዋን ጠንካራ አገር የሚቀርጽ ግዙፍ የትውልድ ግንባታ ፕሮጀክት ነው።

## የማህበራዊ ፍትህ ማረጋገጫ ድልድይ

ማህበራዊ ፍትሕ (Social Justice) ማለት ሁሉም ዜጋ እኩል የመደመጥ፣ የመማር እና የመልማት እድል ሲያገኝ ነው። በአንድ ክፍል ውስጥ ምሳ ይዞ የሚመጣ ተማሪ እና እንደ ፈቃዱ ባዶ ምሳ ዕቃ ይዞ የሚቀመጥ ተማሪ እያለ ስለ "እኩልነት" እና ስለ "ትምህርት ጥራት" ማውራት አይቻልም። ርሃብ ባለበት ክፍል ውስጥ ዴሞክራሲም ሆነ ፍትሕ ቦታ የላቸውም።

ባለፉት የለውጥ ዓመታት የከተማ አስተዳደሩ ይህንን ክፍተት ለመድፈን የተማሪዎችን የምገባ ፕሮግራም እንደ ዋና የማህበራዊ ፍትሕ ማስፈኛ መሳሪያ አድርጎ ሰርቷል። መርሃ ግብሩ ሲጀምር 300 ሺህ ተማሪዎችን ብቻ ያቀፈ የነበረ ቢሆንም፣ በአሁኑ ወቅት ከ1 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎችን በቀን 2 ጊዜ ጥራቱ የተጠበቀና ጤናማነቱ የተረጋገጠ ምግብ መመገብ ተችሏል፤ በተጨማሪም ዩኒፎርም፣ ጫማ እና የመማሪያ ቁሳቁስ ጭምር ለተማሪዎቹ ያቀርባል።

ይህን ያህል ቁጥር ያለውን ተማሪ በየቀኑ የተመጣጠነ ይዘት ያለው ቁርስና ምሳ መመገብ ማለት ትርጉሙ ብዙ ነው፡፡ በቀላሉ ለመመልከት ይህ አሃዝ ከሲሼልስ የሕዝብ ብዛት ስምንት እጥፍ በላይ እንደማለት ነው፡፡ ይህ ማለት አዲስ አበባ የሲሼልስን ያህል ቁጥር ያላቸው ስምንት ሀገራትን በየቀኑ ቁርስና ምሳ ትመግባለች፤ በየዓመቱ የትምህርት ቤት ደንብ ልብስ፣ ጫማ፣ ደብተርና ሌሎች የትምህርት ቁሳቁስ ታሟላለች እንደማለት ነው፡፡ በእርግጥ ጉዳዩን በጥልቀት ካየነው ከዚህም በላይ ትርጉም የሚሰጥ ነው፡፡

ይህ እርምጃ በከተማዋ ሰፊ ማህበራዊ ፍትሕን አስፍኗል፤ በኢኮኖሚ አቅም ማነስ ምክንያት ልጆቻቸውን መመገብ የማይችሉ ወላጆችን ትልቅ ሸክም አቅልሷል። ከ16 ሺህ በላይ አቅመ ደካማ መጋቢ እናቶችን በቅንጅት በማደራጀትና የስራ እድል በመፍጠር፣ የኢኮኖሚ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን አረጋግጧል፤ ቋሚ የስራ እድልም ፈጥሯል። አሁን በአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሁሉም ተማሪዎች እኩል ይመገባሉ፣ እውቀት ይገበያሉ፤ እናም የነገ ተስፋቸውን በብሩህ ተስፋ አሻግረው ይመለከታሉ።

## በትምህርት ቆይታ ላይ የመጣ ለውጥ

ይህ ማህበራዊ ፍትሕን የማስፈን ስራ ዝም ብሎ በበጎ ምኞት የተገለጸ ሳይሆን በተጨባጭ ቁጥሮች የተደገፈ ስኬት ያመጣ ነው። በተለይም ተማሪዎች በምግብ እጥረት ምክንያት ትምህርታቸውን የሚያቋርጡበት ሁኔታ ግርምትን በሚፈጥር መልኩ ቀንሷል፡፡

ይህ መሻሻል በተማሪዎች አጠቃላይ የክፍል ውስጥ ውጤት፣ በተለይም በ6ኛ እና 8ኛ ክፍል ክልል አቀፍ ፈተናዎች የማለፍ ምጣኔ ላይ ተጨባጭና አስደናቂ ለውጥ እንዲመዘገብ አድርጓል።

**የምገባ ፕሮግራሙ በትምህርት ዘርፍ ላይ ያመጣው ለውጥ**

| የትኩረት መስኮች | ከፕሮግራሙ በፊት | ከፕሮግራሙ በኋላ | የተገኘው ለውጥ |
|---|---|---|---|
| የተማሪዎች ቁጥር | 300,000 | 1,000,000+ | ከሶስት እጥፍ በላይ አድጓል |
| የትምህርት ማቋረጥ ምጣኔ | ከፍተኛ | በከፍተኛ ሁኔታ የቀነሰ | በምግብ እጥረት ትምህርት አይቋረጥም |
| የትምህርት ማርፈድና መቅረት | ከፍተኛ | በከፍተኛ ሁኔታ የቀነሰ | የተማሪዎች በክፍል ውስጥ መገኘት ጨምሯል |
| የክልል አቀፍ ፈተናዎች (6ኛ እና 8ኛ ክፍል) | ዝቅተኛ የማለፍ ምጣኔ | ከፍተኛ የማለፍ ምጣኔ | በከፍተኛ ሁኔታ ውጤታቸው ጨምሯል |

"ሀገር የሚገነባው በዜጎች ሁለንተናዊ ለውጥና በትውልድ ግንባታ ቀጣይነት ነው!"

የፕሮግራሙ ትልቁ ስኬት እንደ ተራ ምጽዋት ሳይሆን እንደ ትልቅ "የትውልድ ግንባታ" ፕሮጀክት መታሰቡ ነው። ዛሬ በትምህርት ገበታ ላይ እያለ አእምሮው በዕውቀት፣ አካሉ ደግሞ በተመጣጣኝ ምግብ ያልተገነባ አዳጊ፣ ነገ አገር የመረከብ ተስፋው የመነመነ ነው።

ይህ ፕሮግራም ለወደፊቱ ብቁ፣ አገር ወዳድ፣ ጤናማ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ መሆን የሚችል ትውልድ ለመፍጠር ትልቁን ሚና ይጫወታል። ዛሬ በትምህርት ቤቶች እየተተገበረ ያለው የምገባ ፕሮግራም ነገ ለአገሪቱ የሳይንስ ሊቃውንትን፣ መሀንዲሶችን፣ መሪዎችን እና የኢኮኖሚ ባለሙያዎችን የሚያፈራበት የትውልድ ማሳደጊያ ስልት ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይህንን ፕሮግራም በዘላቂነት ለማስቀጠልና ስኬታማ ለማድረግ ልዩ የፖለቲካ ቁርጠኝነት አሳይቷል። ለዚህም ማሳያ የሚሆነው ስራውን በዘመናዊ መዋቅር ተቋማዊ አድርጎ ለመምራት ራሱን የቻለ "የተማሪዎች ምገባ ኤጀንሲ" ማቋቋሙ ነው። ከዚህም ባሻገር በጥራት ረገድ ጉድለት እንዳይኖር በሁሉም ትምህርት ቤት ሁለት ሁለት የስነ-ምግብ ባለሙያዎችን በመቅጠር ጠንካራ የክትትል ስርዓት ዘርግቷል።

ይህ የአዲስ አበባ ከተማ ተሞክሮ ዛሬ የሀገር ውስጥ ስኬት ብቻ አይደለም፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ እውቅናን ያገኘ፣ ለኢትዮጵያ መልካም ገፅታ ግንባታ ትልቅ ፋይዳ ያበረከተና ሌሎች አዳጊ አገሮችም ሊቀስሙት የሚገባ ትልቅ ሞዴል ሆኗል።


ዛሬ እንደ ፈቃዱ ያሉ የከተማችን ልጆች ምሳቃቸው ባዶ አይደለም፤ የቀደመ ታሪካቸውም ላይመለስ ትዝታ ሆኖ አልፏል፡፡ ባዶ ምሳ እቃ ይዞ በመመላለስ ምክንያት ይደርስባቸው የነበረው የመንፈስ ስብራት ተጠገኖ ልባቸው በፍቅር፣ በእኩልነት እና በተቃና የነገ ተስፋ ተሞልቷል።

ቸር እንሰንብት!

# ለትውልድ የሚተርፍ መስዋዕትነት

**በደረጀ ታደሰ**

“ጊዜ ወርቅ ነው” የሚለው አባባል የተለመደ ነው:: አባባሉ የጊዜን ውድነት እና ከፍ ያለ ዋጋውን ያሳያል:: ይህ ውድ፣ ከውድም በጣም ውድ የሆነው ጊዜ፤ ለሁሉም ሰው በፍትሐዊነት የተሰጠው ልዩ ተፈጥሯዊ ስጦታ መሆኑ፤ በጊዜ የመጠቀምም ሆነ ያለመጠቀም ውሳኔ በእያንዳንዱ ሰው ላይ እንዲወድቅ አድርጎታል:: ለዚህም ነው፤ በምድር ላይ ከልደት እስከ ሞት ድረስ ውስን የሆነ ዕድሜን የሚኖረው የሰው ልጅ ከጊዜ ጋር ባለው ቁርኝትና አጠቃቀም፣ የሕይወት ዘመኑን ስኬት እና ውድቀት የሚወስነው።



ፎቶ- ከገፀ ድር
ቀን ከሌሊት እየተገነባች ያለችው አዲስ አበባ ከፊል ገፅታ

የጊዜን ወርቅነት ያለመረዳት፣ በጊዜም በአግባቡ ያለመጠቀም ችግር በኢትዮጵያዊያን ዘንድ በስፋት የሚስተዋል ችግር ሆኖ ቆይቷል። “የሐበሻ ቀጠሮ” የሚል ስያሜ እስከመሰጠት ያደረሰን፣ ለጊዜ ያለን ዋጋ ቀላልና ርካሽ መሆኑ ነው:: ጊዜን ማባከን ለውድቀትና ለኋላቀርነት ራስን በጓደኝነት አሳልፎ እንደመስጠት ይቆጠራል:: የጊዜ አባካኝነት በዓለማዊው አስተምህሮ ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊው አስተምህሮም የተወገዘ ነው:: ምክንያቱም፤ በሰከንድ፣ በደቂቃ፣ በሰዓት፣ በቀን፣ በሳምንት፣ በወር፣ በዓመት ... ተለክቶ በተሰጠ ጊዜ ውስጥ በታቀደና ውጤታማ በሆነ መልኩ አለመንቀሳቀስ በስጋም ሆነ በነፍስ ጉድለት የሚያስከትል እንደሆነ ይታመናል::

ውድ አንባቢያን፤ ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ምን ያክል ውጤት እንደሚያመጣ የሁላችን መዲና የሆነችውን አዲስ አበባን በማሳያነት እንመልከት:: ምልከታችንን በጊዜ እንወስነው:: ከ2010 ዓ.ም በመነሳት አሁን እስካለንበት (ግንቦት አጋማሽ 2018 ዓ.ም.) ድረስ ባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንመላለስ:: የእያንዳንዱን የአዲስ አበባ ከተማ አካባቢዎች የቀደመ ገፅታ እና አሁናዊ መልክ እናስታውስ:: በኮሪደር ልማት፣ በወንዝ ዳርቻ ልማት፣ በተለያዩ እና ዘርፈ ብዙ አገልግሎት ሰጪ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ... የተሠሩ እና ለውጤት የበቁ ትሩፋቶችን እስከምንችለው ድረስ እንቁጠር:: የከተማዋን እየተጋጋለ የመጣውን የእንቅልፍ አልባ እንቅስቃሴዎችም በትውስታችን ላይ እናክልበት:: በጥቂት ዓመታት ውስጥ በአዲስ አበባ ለታየውና እየታየ ላለው ሁሉን አቀፍ አስደናቂ ስኬት እንዲመዘገብ ካስቻሉ ቁልፍ አቅሞች መካከል፡- ጊዜን በአግባቡ የመጠቀም ባህልና ልምድ መዳበሩ በቀዳሚነት ይጠቀሳል::

ከቀናት በኋላ፤ የዒድ አል-አድሃ (አረፋ) በዓል በመላው የሀገራችን የእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ በታላቅ ድምቀትና በመንፈሳዊ ሥነ-ስርዓት ይከበራል። እንደ እምነቱ አስተምህሮ በዓሉ የሚከበረው፤ የታላቁን ነቢይ ኢብራሂምና የልጃቸውን የኢስማኤልን ፍጹም ታዛዥነት፣ ታማኝነትና ለመስዋዕትነት የመዘጋጀት ጥግን ለማስታወስ ነው። በዚህ የበዓሉ መሰረታዊ መነሻዎች ውስጥ “መስዋዕትነት” አንዱ ሆኖ እንመለከታለን። ይህም በዓሉ፣ ራስን ለአምላክ ትዕዛዝ ፍጹም አሳልፎ ከመስጠት መንፈሳዊ እውነት በዘለለ፣ “መስዋዕትነት” የተሰኘውን ታላቅ ሰብዓዊ፣ ማኅበራዊና ሀገራዊ እሴት በሰፊው የሚሰላሰልበት ነው::

መስዋዕትነት በብዙ የሕይወት ዘርፎችና በተለያዩ ተግባራዊ መልኮች ሊገለጽ የሚችል ሰፊ ጽንሰ-ሀሳብ ነው። ከእነዚህ ዘርፈ-ብዙ የመስዋዕትነት መገለጫዎች መካከል ደግሞ የሰው ልጅ ሊተካውና ሊመልሰው የማይችለው እጅግ ውድና ታላቁ ሀብት “ጊዜ” እንደሆነ ይታመናል። አዎ፤ ይህንን ለመረዳት ሩቅ ሳንሄድ አዲስ አበባን መመልከት ይበቃል። ዛሬ በአይናችን የምናያት፣ በየቀኑ አዳዲስ ገጽታዎችን የምትላበሰውንና በግዙፍ ሜጋ ፕሮጀክቶች አሸብርቃ የነገ እጣ ፈንታዋን በደመቀ ሁኔታ እየቀየረች ያለችውን የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባን ስንመለከት፣ ይህንን እውነት በተግባር እንረዳዋለን። መዲናዋ አሁን ያለችበትን አንጸባራቂ የለውጥ ምዕራፍ ልታስመዘግብ የቻለችው፣ ይህንኑ የመስዋዕትነት ፍልስፍና ወደ ተግባር በመተርጎም፣ የጊዜን ዋጋ ተረድታ ሳምንቱን ሙሉ በቀን 24 ሰዓት ያለማቋረጥ መሥራት በመቻሏ እንደሆነ ግልጽ ነው።

ጊዜ በመስዋዕትነት የሚቀርብ ውድ ስጦታ ስለመሆኑ ከእስልምና ኃይማኖት አስተምህሮ ጋር በማያያዝ የሚያስረዱት አየር ጤና የሚገኘው አንሷር መስጂድ ኃይማኖታዊ መምህር የሆኑት ዑስታዝ ሙሐመድ ፈረጅ ናቸው። እሳቸው እንደሚገልጹት፤ በእስልምና አስተምህሮት፣ ጊዜ ከምንም በላይ ውድ ነው:: ጊዜ ትልቅ ዋጋ አለው:: ጊዜ እንደ

> “24 ሰዓት መሥራት ማለት የከተማዋን ምርታማነት በሦስት እጥፍ ማሳደግ ማለት ነው። ይህ ደግሞ በባዶ ሜዳ የመጣ ሳይሆን፣ የሠራተኛው፣ የአመራሩና የባለሙያው ‘የጊዜና የጉልበት’ መስዋዕትነት ውጤት ነው::”

ተጠቃሚው ብቃት ውጤት የሚሰጥ ነው:: ጊዜን ካልቆረጥከው ይቆርጥሃል። በቅዱስ ቁርዓን ውስጥ ስለጊዜ በብዙ ቦታዎች ላይ ተጠቅሷል:: ‘ጊዜውን የተጠቀመ ዳነ፣ ተረፈ፣ የሚፈልገውን አገኘ:: ጊዜውን ያልተጠቀመ ደግሞ ከሰረ፣ ተዋረደ፣ የሚፈልገውን አጣ፣ ወደቀ’ የሚል መልዕክት በተለያዩ የቅዱስ መጽሐፍቱ ላይ ተጠቅሶ እናገኛለን። ስለዚህ ጊዜውን በአግባቡ የተጠቀመ ይድናል፣ የተሻለ ሕይወትን ይኖራል:: በተቃራኒው ጊዜውን ያባከነ ይዋረዳል፣ ለጉዳትም ይዳረጋል::

ዑስታዝ ሙሐመድ አክለው እንዳስረዱት፤ ጊዜን ሳይባክን በአግባቡ መጠቀም ይገባል:: ከዚህ ጋር በተያያዘ ነብዩ መሐመድ፤ “ሁለት ጸጋዎች አሉ። አንደኛው ጤንነት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ጊዜ ነው:: በእነዚህ ጸጋዎች ላይ አብዛኛው ሰው ተሞኝቶባቸዋል።” በማለት ማስተማራቸውን በምሳሌነት ጠቅሰዋል:: ይህም፤ የሰው ልጅ በቀላሉ በእጁ ያሉትን ሀብቶች (ጊዜና ጤናን) ሳያባክን መጠቀም እንዳለበት የእምነቱ አስተምህሮ ደጋግሞ እንደሚገልጽ አንስተዋል::

“በኢድ አል-አድሃ (አረፋ) በዓል ላይ በግን በማረድ ብቻ መስዋዕትን መግለፅ በቂ አይደለም:: ይልቁንም ጊዜያችንን ሰውተን ወዳጅ ዘመዶችን፣ ጎረቤቶችን፣ አቅመ ደካሞችን፣ የተቸገሩትን መጠየቅና ካለን ማካፈል ይጠበቅብናል::” ያሉት ዑስታዝ ሙሐመድ፤ ጊዜን ለልማት ማዋል፣ የሰው ልጅ ለተሻለ ሥራ እንዲነሳሳ፣ ሞራሉ እንዲገነባ፣ አንድነት እንዲፈጠር፣ ሠላም እንዲሰፍን ... ማዋል የሚያስገኘው ስጋዊና መንፈሳዊ ውጤት ከፍተኛ መሆኑን አስረድተዋል::

በተለይ ጊዜን ለልማት ማዋል እጅግ ወሳኝ መሆኑን ነብዩ መሐመድ በተለያዩ ምሳሌዎች ካስተማሯቸው ትምህርቶች መካከል አንዷን በመጥቀስ አብራርተዋል፤ “ከሃያ ወይም ከረጅም ዓመት በኋላ ፍሬ የምታፈራን ተክል፣ ‘ነገ ትሞታላችሁ፣ ነገ የዓለም ፍጻሜዋ ነው’ ብትባሉ እንኳን፤ ተክሏን ባላችሁ ጊዜ ወይም አሁኑኑ ትከሏት’ ይላሉ። ምክንያቱም፣ ዛሬ ላይ ያለው ሰው ተክሏን ካልተከላት፣ ከሃያ ዓመት በኋላ የሚመጣው ትውልድ ከፍሬዋ ሊመገብ አይችልምና:: ከዚህ የምንረዳው፤ ልማት ፈፅሞ መቆም እንደሌለበት ነው:: በችግር ውስጥም ሆኖ ማልማት፣ በሕመም ውስጥም ሆኖ መሥራት፣ በምሽትም ሆነ በሌሊት የልማት ሥራዎችን ማስቀጠል ይገባል:: አስቸጋሪ ሁኔታዎች ቢከሰቱ እንኳን ለእነሱ መፍትሄ እየሰጡ ልማትን ያለማቋረጥ ማስቀጠል ያስፈልጋል:: የልማት ቀጣይነት ሲረጋገጥ ነው አገር እና ትውልድ ሊቀጥል የሚችለው:: ‘እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል’ የሚለው አባባል፤ በእስልምና አስተምህሮ ውስጥ ቦታ የለውም::”

አሁን ባለንበት ዘመን፣ በአገራችን በተለይም በአዲስ አበባ የኛ ትውልድ አካል የሆኑ “የልማት አርበኞች” ጊዜያቸውን በመስዋዕትነት በማቅረብ ትውልድ ተሻጋሪ የልማት ጡቦችን እየገነቡ መሆኑን እንመለከታለን:: ባለፉት ጥቂት ዓመታት በመዲናዋ ያስተዋልነው እውነታ ቢኖር “ሌሊት” የሚለው ጽንሰ-ሀሳብ መለወጡ ነው። ከተማዋ እንቅልፍ አታውቅም። እየተከናወኑ ያሉ የኮሪደር ልማቶች፣ የፓርኮች ግንባታ እና የሕዝብ

ወደ ገጽ 20 ዞሯል

**ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ**

# ስለ ምሽት ንግድና ትራንስፖርት አገልግሎት ደንቡ ምን ይላል?


**(ክፍል ሁለት)**

**አብርሃም ንጉሴ (ዐቃቤ ህግ)**

ውድ አንባቢዎቻችን፤ ባለፈው ዕትማችን በዋና ርዕሰ ጉዳይ መነሻነት፤ የንግድ እና የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ደንብ ቁጥር 185/2017 አዋጅ በተመለከተ እና ተያያዥ ጉዳዮችን በክፍል አንድ አስነብበናችኋል። ክፍል ሁለትን ደግሞ እንደሚከተለው አዘጋጅተናል። መልካም ንባብ!

**በአዋጁ አስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ ምን ይመስላል?**

የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ደንብ ቁጥር 185/2017 አዋጅ አሰጣጥ መሰረት ማንኛውም የንግድ ተቋም ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም በዚህ ደንብ የተደነገጉትን ክልከላዎች ተላልፎ ሲገኝ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ እንዲያስተካክል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል። ማስተካከል ካልቻለ ቢሮው የቅጣት ሰንጠረዥ መሰረት 10 ሺ ብር አስተዳደራዊ ቅጣቱን እንዲከፍል ማስታወቂያ ይሰጠዋል።



የንግድ ተቋሙ በአስተዳደራዊ ቅጣቱ መታረም ሳይችል ቀርቶ በተደጋጋሚ ጥፋቶችን የሚፈጽም ከሆነ 10 ሺ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል። ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ከተፈጸመ ከተቀመጠው ቅጣት 1/3 (አንድ ሦስተኛ) ተጨምሮ እንዲቀጣ ይደረጋል፤ ለሦስተኛ ጊዜ ካጠፋ የተሰጠው ቅጣት 1/3(አንድ ሦስተኛ) ተጨምሮ እንዲቀጣ ይደረጋል፤ ለአራተኛ ጊዜ ካጠፋ የተሰጠው ቅጣት 1/3(አንድ ሦስተኛ) ተጨምሮ እንዲቀጣ ይደረጋል፤ ለአምስተኛ ጊዜ ካጠፋ የተሰጠው ቅጣት 1/3 (አንድ ሦስተኛ) ተጨምሮ እንዲቀጣ ይደረጋል። በተደነገገው መሠረት የገንዘብ ቅጣት ተቀጥቶ ማረም ካልቻለ ቢሮው የንግድ ሥራ ፈቃዱን ያግዳል። በእግዱ መሠረት ችግሩ ካልታረመ ደግሞ የንግድ ፈቃዱን እንደሚሰርዝ ተቀምጧል። የንግድ ፈቃዱ የተሰረዘበት ሰው የንግድ ተቋሙ የንግድ ሥራ እያከናወነ የሚገኘው በመንግስት ቤት ውስጥ ከሆነ ቢሮው ቤቱን ለሚያስተዳድረው አካል የንግድ ሥራ ፈቃዱ የተሰረዘ መሆኑን መረጃውን ያስተላልፋል።

በዚህ መሰረት መረጃው የደረሰው አስፈጻሚ አካል ቤቱን ከተከራየው ሰው ጋር ያደረገውን ውል ያቋርጣል፤ ውሉ የተቋረጠ መሆኑንም ለተዋዋዩ ያሳውቃል፤ ቤቱንም ይረከባል። ይህ እንዳለ ሆኖ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ በዚህ ደንብ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገጉትን ክልከላዎች ተላልፎ ሲገኝ በዚህ ደንብ አባሪ በተደረገው ሰንጠረዥ መሠረት አስተዳደራዊ ቅጣቱን እንዲከፍል ማስታወቂያ ይሰጠዋል። የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ በአስተዳደራዊ ቅጣቱ መታረም ሳይችል ቀርቶ በተደጋጋሚ ጥፋቶችን የሚፈጽም ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ተፈጻሚ ይደረጋል።

**በተመሳሳይ መልኩ አስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰዱ ምን ይመስላል?**

በዚህ ደንብ መሠረት አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም ሰው የተሰጠውን አስተዳደራዊ ቅጣት ማስታወቂያ ወረቀት በመያዝ ወዲያውኑ ጥፋቱ በተፈፀመበት አካባቢ በሚገኘው የወረዳ ንግድ ጽህፈት ቤት ወይም ትራንስፖርት ቢሮ ቀርቦ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መክፈያ ዘዴ በሦስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ገንዘቡን ገቢ በማድረግ ቅጣቱን መፈጸም አለበት። በዚህ መሠረት አስተዳደራዊ መቀጫውን ገቢ ያላደረገ ሰው የተጣለበትን የቅጣት ገንዘብ መጠን እጥፍ እንዲከፍል ይደረጋል። የቅጣት ማስታወቂያ ለመቀበል ፍቃደኛ ካልሆነ እንደተቀበለ ተቆጥሮ ተፈጻሚ ይሆናል። ቢሮው ወይም የትራንስፖርት ቢሮ በዚህ መሠረት መቀጫውን ገቢ ያላደረገ ማንኛውም ሰው ላይ ክስ እንዲቀርብ ለከተማው አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ማስረጃውን አደራጅቶ ይልካል።

የቅሬታና አቤቱታ አቀራረብን በተመለከተ ቢሮው ወይም የትራንስፖርት ቢሮ በሚሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ውሳኔው በተሰጠው በሦስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ውሳኔውን ለሰጠው አስፈጻሚ አካል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ እንደሚችል በዚህ ደንብ አንቀጽ 11 ላይ ተደንግጓል። ቅሬታውን የተቀበለው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በሚኖሩት 5 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን መርምሮ የውሳኔ ሀሳቡን ለቢሮው ወይም ለትራንስፖርት ቢሮ የበላይ ኃላፊ ማቅረብ አለበት። የውሳኔ ሀሳብ የቀረበለት የበላይ ኃላፊ በ5 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

የበላይ ኃላፊው የሰጠው ውሳኔ ደግሞ የመጨረሻ ይሆናል። ቅሬታ አቅራቢው ላቀረበው ቅሬታ ውሳኔ እስከተሰጠ ድረስ ቅጣቱ ከመፈጸም ታግዶ ይቆያል። የአስፈጻሚ አካሉ የበላይ ኃላፊ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታ ለማቅረብ ይችላል፡፡

በአጠቃላይ ማንኛውም ሰው ይህንን ደንብ ለማስፈጸም ሲጠየቅ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡ ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም የከተማ ካቢኔ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡ ስለሆነም ይህ ደንብ ከየካቲት 29 ቀን 2018 ዓ.ም ጀምሮ ተግባር ላይ የዋለ መሆኑን ሁሉም ሰው ማወቅ ይኖርበታል።

# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን
Addis Ababa city Government Tax Appeal Commission

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ለመላው የእስልምና እምነት ተከታዮች እንኳን ለ1447ኛ ጊዜ ለሚከበረው የኢድ አል አድሃ አረፋ በዓል እንኳን በሰላም አደረሳችሁ እያለ መልካም ምኞቱን ሲገልፅ በደስታ ነው።**

ኮሚሽኑ ፍትሃዊ ታክስ አስተዳደር ስርዓት የሰፈነባት እና የህግ የበላይነት የተረጋገጠባት ከተማ ከማድረግ አንፃር ተገልጋዩ ህብረተሰብ ይግባኝ አቀራረብ ስርዓት በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 88 መሰረት መሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ማለትም የተወሰነበትን ግብር ወይም ታክስ 50 በመቶ የተከፈለበት ደረሰኝ በመያዝ የውሳኔ ማስታወቂያ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ተከታታይ ቀናት የይግባኝ አቤቱታቸውን ከነማስረጃዎቹ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ስለሆነም ተገልጋይ ህብረተሰብ በአገልግሎት አሰጣጣችን እንዲረካና ያለምንም ውጣ ውረድ ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኝ ቅልጥፍና፣ ጥራትና ምርታማነት የላቀ በማድረግ ረገድ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የችሎት ቀጠሮ ቀንና የተቀጠረበትን ምክንያት በየትኛውም ቦታ ሆኖ ማወቅ እንዲችል እንዲሁም የውሳኔ ይግባኙን በQR code በመጠቀም ባሉበት ቦታ ሆኖ ማወቅና መውሰድ እንዲችሉና፣ አጠቃላይ የፋይል አከፋፈትና አደረጃጀት ወረቀት አልባ ኢፋይልን ሲስተም /E-filing system/ በመጠቀም በቴክኖሎጂ የተደገፈ የላቀ አገልግሎት በመስጠት ላይ እንገኛለን፡፡

ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን በከተማ አስተዳደሩ ግብር ከፋዮች የሚያቀርቡት ይግባኝ አቤቱታዎችን መርምሮ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን በኮሚሽኑ እንደገና መቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 105/2011 የተደነገገ ሲሆን፣ የሚከተሉት ስልጠንና ተግባር ተሰጥቷል፡፡

- በግብር እና ማዘጋጃ ቤታዊ ታክስና ቀረጦች ጋር በተገናኘ ይግባኝ የቀረበበትን ጉዳይ መርምሮ ውሳኔውን ያሻሽላል፣ ያፀናል፣ ወይም ይሽራል፣ እንዲሁም አስፈላጊ የሆነውን ተጨማሪ ትዕዛዝ ይሰጣል፣ የሰጠውን ውሳኔና ትዕዛዝ ያስፈፅማል፣
- ባለሥልጣኑ የሰጠውን የታክስ ውሳኔ በመቃወም የሚቀርብለትን ይግባኝ በመስማት በፍሬ ነገር ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፣
- በሕግ ይግባኝ በተፈቀደባቸው የማዘጋጃ ቤት ታክስና ቀረጥ ላይ የሚቀርብለትን ይግባኝ መርምሮ ይወስናል፣
- በቀረበለት ጉዳይ ላይ መርምሮ ውሳኔ ለመስጠት አግባብነት ያለው ማናቸውም መፅሐፍ፣ መዝገብ ሌላ ፅሁፍም ሆነ ማንኛውም ዓይነት ሌላ ማስረጃ (የኤሌክትሮኒክስ መረጃን ጨምሮ) እንዲቀርብለት ትዕዛዝ ይሰጣል
- በቂ ባልሆነ ምክንያት የችሎቱን ዕዛዝ ያልፈጸመ ተከራካሪ ወገን ለሌላ ተከራካሪ ወገን ተመጣጣኝ ኪሳራ እንዲከፍል ይወስናል፣
- አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የሰጠውን ውሳኔና ትዕዛዝ የፖሊስ ኃይል በማዘዝ ያስፈፅማል፡፡

**ፈጣሪ ኢትዮጵያችንን በሰላም፣ በበረከትና በአንድነት ይጠብቅልን።**

- ስልክ ቁጥር፡0115502038/011 ወይም 0115502104
- ኢሜይል፡aataxappeal4@gmail.com
- ዌብሳይት፡https://www.aataxappeal.gov.et/
- ቴለግራም፡https://t.me/AddisTaxAnnouncements
- ፌስቡክ፡https://www.facebook.com/share/r/18norsFF65/

**መልካም በዓል**

**‹‹ፍትሃዊ የታክስ አስተዳደር ስርዓት ለመገንባት›› በጋራ እንስራ!!**




ኮሜርሻል ኖሚኒስ ኃ.የተ.የግ.ማ
Commercial Nominees P.L.C

60th YEARS OF TRUST

**60 አመታትን በታማኝነት**

6630 +251111564350
www.commercialnominees.com,
marketing@commercialnominees.com

# ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች

**በጊዜው አማረ**

በመዲናችን አዲስ አበባ ባሳለፍነው ሳምንት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች እና አዳዲስ ጥበባዊ ስራዎች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል፡፡ ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም የተለያዩ ጥበባዊ መሰናዶዎች ይደረጋሉ፡፡ ከተሰናዱ ዋና ዋና ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች መካከል፣ የመጽሐፍት እና ሃሳብ ውይይት፣ የሥነ-ጥበብ አውደ ርዕይ፣ የሙዚቃ አልበም ምርቃት፣ የቴአትር መርሃ ግብር እና ሌሎች መሰናዶዎች ይገኙበታል። ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር
በከተማችን ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

## መጽሐፍት

"ምስጉን ሰው"መጽሐፍ በነገው ዕለት ተመርቆ ለንባብ ይበቃል፡፡ የህይወት ታሪክ ዘውግ የሆነው ይህ መጽሐፍ ነገ ግንቦት 16 ቀን 2018 ዓ.ም ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ጀምሮ ባምቢስ ሱፐር ማርኬት አጠገብ በሚገኘው ዲ ሊዮፖል ሆቴል ይመረቃል፡፡

በሌላ መረጃ "ዝሃ" መጽሐፍ በትናንትናው ዕለት በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ልዑል ራስ መኮንን አዳራሽ ተመርቆ ለንባብ በቅቷል፡፡ የመጽሐፉ ደራሲ አንጋፋው ጸሐፊ ተውኔትና አዘጋጅ ዳግማዊ አመለወርቅ ፈይሳ ነው፡፡

እንዲሁም በዛሬው ዕለት የመጽሐፍ ፊርማ ሥነ ስርዓት እና ውይይት ይካሄዳል፡፡ ውይይቱ የሚደረገው ከወጣቱ ደራሲ አህመድ ሁስ ጋር ሲሆን የቫዮሊን መርሃ ግብርም መዘጋጀቱ ተገልጿል፡፡ መርሃ ግብሩ የሚካሄደው ለገሃር ተወልደ ሕንጻ ስር በሚገኘው ጃዕፈር መጻሕፍት መደብር ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ጀምሮ ነው፡፡ ደራሲ አህመድ ሁስ "ጥሪ ወደ ሞት" እና "የሎሚ ጭማቂ ትዝታ" በተሰኙት ስራዎቹ ይታወቃል፡፡

## የስዕል ዐውደ ርዕይ

"የዝምታ ወጎች" የስዕል አውደ ርዕይ በመጪው ረቡዕ ለእይታ ሊበቃ ነው። ሰዓሊው ታሪኩ አስራት ሲሆን አውደ ርዕይው የሚከፈተው ሀያት ሪጀንሲ ሆቴል በሚገኘው በፈንድቃ የባህል ማዕከል ነው፡፡

በተጨማሪም "ውብ አዲስ" የተሰኘው የስዕል አውደ ርዕይ በእይታ ላይ ይገኛል። የሰዓሊ ሀሮን ሱሌይማን ስራ የሆነው "ውብ አዲስ" የተሰኘ የሥዕል ዐውደ ርዕይ እየታየ የሚገኘው በጣይቱ የባሕልና ትምህርት ነው፡፡ ዐውደ ርዕይው የሚጠናቀቀው ግንቦት 23 ቀን 2018 ዓ.ም ነው።

በሌላ መረጃ "ትስስር" የተሰኘው የስዕል ዐውደ ርዕይው በመጪው ማክሰኞ ይጠናቀቃል፡፡ የአብዱልቃድር መሐመድ፣ ኢሳ ታደለ እና ምስለኬ እሸቱ ስራዎች የቀረቡበት ይህ የቡድን የግራፊክስ የስዕል አውደ ርዕይ እየታየ የሚገኘው በፈንድቃ የባህል ማዕከል ነው፡፡

## ሙዚቃ

"ጎምጃ" የተሰኘ አዲስ የሙዚቃ አልበም በዛሬው ዕለት ተመርቆ ለአድማጭ ተመልካች ይደርሳል፡፡ የድምፃዊ ግርማይ በላይ (ግርማይ ራያ) ስራ የሆነው ይህ አልበም ዛሬ ከቀኑ 8:00 ሰዓት መገናኛ አካባቢ 24 በሚገኘው ኮከብ ህንፃ ይመረቃል፡፡ ከምርቃቱ በኋላ የሙዚቃ ስራው በድምጻዊው የዩቱብ ገጽ ለአድማጭ ተመልካች እንደሚደርስ ተገልጿል፡፡

## የቴአትር መርሃ-ግብር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ። ቅዳሜ 7፡30 ሲሆን "12ቱ እንግዶች" ቴአትር እንዲሁም 11፡30 ደግሞ "ሽምጋይ" ቴአትር ይታያል፡፡ እሁድ በ7፡30 "ንጉሥ አርማህ" ቴአትር፣ እንዲሁም "እምዬ ብረቷ" የተሰኘው ቴአትር በ11፡30 ላይ ይታያሉ፡፡ በብሔራዊ ቴአትር ለሚታዩ ቴአትሮች ተመልካቾች ጊዜያቸውን ለመቆጠብ በ"ሁሉ በጀ" መተግበሪያ በመጠቀም ትኬቶችን አስቀድመው መግዛት እንደሚችሉ ተገልጿል።

በተጨማሪም "ባልቻ አባነፍሶ" ቴአትር እሁድ በ8:00 ሰዓት በአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ የሚታይ ሲሆን ትኬት በኦን ላይን የክፍያ ስርዓት መቁረጥ እንደሚቻል ተገልጿል፡፡ በሀገር ፍቅር ቴአትር ደግሞ ነገሩ አይቆምም ሐሙስ 11፡30 ሳደታ (በአፋን ኦሮሞ ) እሑድ 8፡00 ሰዓት እንዲሁም የመጨረሻው ፍርድ እሑድ 12፡00 ሰዓት ለቴያትር አፍቃሪያን ይታያል፡፡

በተጨማሪም "አዮ ቦራ" የተሰኘው የአፋን ኦሮሞ የህፃናት ቴአትር ቅዳሜ ጠዋት 4፡00 ሰዓት በህፃናትና ወጣቶች ቴአትር ቤት ለእይታ ይቀርባል፡፡ በተመሳሳይ "የሰማይ ልጆች" የተሰኘው ቴአትር እሁድ ጠዋት 4፡00 ሰዓት ጀምሮ ፍላሚንጎ በሚገኘው በህፃናትና ወጣቶች ቴአትር ቤት ይታያል፡፡

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት ሳምንታዊ የፓዝል ጥያቄ እና መልስ ባለማቅረባችን ይቅርታ እንጠይቃለን፡፡

አንባቢዎቻችን ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ የመጀመሪያው ረድፍ ላይ (3×4)+3=15 ይሆናል፡፡ በሁለተኛው ረድፍ ላይ (7×5)+3=38 ነው፡፡ በዚህ መሰረት በሦስተኛው ረድፍ ላይ (3×5)+3=18 ነው፡፡ ስለዚህ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛ ቁጥር 18 ይሆናል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 3 | 15 | 4 |
| 7 | 38 | 5 |
| 3 | 18 | 5 |

## የዛሬው የቁጥር ጨዋታ

ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት ዕትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# ነብዩ መሐመድ የሚወዷቸው ቀለማት

**በጊዜው አማረ**

ጠዋት ከእንቅልፋችን ስንነቃ መጀመሪያ የምናስተውለው ምንድን ነው? የሰማዩን ሰማያዊነት፣ የቅጠላ ቅጠሎችን አረንጓዴነት ወይንስ የፀሐይዋን ወርቃማ ብርሃን? በዕለት ተዕለት ህይወታችን ውስጥ ቀለማትን እንደ ተራ የተፈጥሮ ክስተት ብቻ ልናያቸው እንችላለን። ነገር ግን፣ ቀለማት ለአይን የሚታዩ ውበቶች ብቻ አይደሉም፤ እነሱ ከሰው ልጅ ሥነ-ልቦና፣ ታሪክ፣ ባህል እና መንፈሳዊነት ጋር በጥብቅ የተሳሰሩ የዓለማችን ህያው ቋንቋዎች ናቸው።

የሰው ልጅ በምድር ላይ መኖር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ቀለማትን እንደ መገናኛ፣ መግለጫ እና መለያ መሳሪያ ሲጠቀምባቸው ኖሯል። ምክንያቱም ቃላት ሊገልጹት የማይችሉትን ጥልቅ ስሜት፣ ረቂቅ እምነት እና የጋራ ማንነት በአንድ ቀለም ውስጥ አምቆ ማሳየት ይቻላልና። ቀለማት የድንበር አጥርን ጥሰው፣ የቋንቋ ልዩነትን አሸንፈው በቀጥታ ከሰው ልጅ ንቃተ-ህሊና ጋር ይነጋገራሉ። የሰው ልጅም ከፈጣሪው እና ከማይታየው መንፈሳዊ ዓለም ጋር ያለውን ግንኙነት ለመግለጽ ቀለማትን እንደ ትልቅ ድልድይ ይጠቀማል። በእምነት ተቋማት ውስጥ እያንዳንዱ ቀለም ዝም ብሎ የሚመረጥ ሳይሆን፣ ጥልቅ መለኮታዊ እና ምስጢራዊ ትርጉም ያዘለ ነው። ይህ ጽሑፍ የአረፋ በዓልን ምክንያት በማድረግ ነብዩ መሐመድ የሚወዷቸው ቀለማት እና ትርጓሜያቸውን እንዲሁም በእስልምና እምነት ውስጥ ያላቸውን ስፍራ ይተነትናል።


ፎቶ- ከገፀ ድር
በእስልምና እምነት ከፍተኛ ቦታ የሚሰጣቸው ቀለማት በመስጂዶች ላይ ጎልተው ይታያሉ

## ቀለማት እና እስልምና

ቀለማት በሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ስሜትን የመግለጽ፣ ውበትን የመፍጠርና መልዕክትን የማስተላለፍ ትልቅ አቅም አላቸው። በእስልምና አስተምህሮ እና ታሪክ ውስጥ ደግሞ ቀለማት ከተራ ውበት ማድመቂያነት አልፈው ጥልቅ መንፈሳዊ፣ ባህላዊና ሥነ-ልቦናዊ ትርጉም ይይዛሉ። በቅዱስ ቁርዓን እና በነቢዩ መሐመድ ሐዲሶች (ትምህርቶች) ውስጥ ለተለያዩ ቀለማት የተሰጡት ቦታዎች፣ በእስልምና ጥበብ (Art)፣ ሥነ-ህንጻ (Architecture) እና አልባሳት ላይ የጎላ አሻራ አሳርፈዋል።

ሁሉንም ቀለማት አቅፎ የያዘውና የብርሃን ነጸብራቅ የሆነው ነጭ ቀለም እና ሁሉንም ቀለማት በውስጡ የሚሰበስበው ጥቁር ቀለም በእስልምና እምነት ውስጥ ልዩ ቦታ አላቸው። አረንጓዴ ቀለም በእስልምና እምነት ውስጥ እጅግ የላቀና የተቀደሰ ቦታ ይሰጠዋል፡፡ በተጨማሪም ሰማያዊ ቀለም በሙስሊሙ ማህበረሰብ ታሪክና ስልጣኔ ውስጥ የሰላም፣ የጸጥታ፣ የጥልቅ እውቀትና የመለኮታዊ ውበት መገለጫ፣ የሰማይን ስፋትና ጥልቀት የሚያስታውስ፣ አማኞች ወደ ላይ ሲመለከቱ የፈጣሪን ስፋትና ወሰን የለሽ ኃይል እንዲያስቡ የሚያደርግ መንፈሳዊ ድልድይ ተደርጎ ይታያል።

## ነጭ

በእስልምና አስተምህሮ ነጭ ቀለም እጅግ የላቀ፣ ንጹህ እና የተከበረ ቦታ አለው። በዚህም ነብዩ መሐመድ በንግግራቸውም ሆነ በተግባራቸው ለነጭ ቀለም ከፍተኛ ትኩረትና ምርጫ ሰጥተዋል።

ኡስታዝ ፉአድ አብዱ የእስልምና ኃይማኖት መምህር ናቸው፡፡ በእስላማዊ ትምህርት ጥናት በዲግሪ ተመርቀዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ትምህርታቸውን እየተማሩና ሌሎችንም እያስተማሩ ነው፡፡ "ነብዩ መሐመድ ቀለምን በተመለከተ በግልጽ ያስቀመጧቸው ነገሮች አሉ" ይላሉ። ከእነዚህ ውስጥ "ከልብሶቻችሁ ነጭ ልብሶችን አብዝታችሁ ልበሱ፤ እሱ ከልብሶቻችሁ ሁሉ በላጭ (ጥሩ) ነውና" የሚለው ዋነኛው ነው የሚለውን ይጠቅሳሉ፡፡

ነብዩ መሐመድ ነጭ ልብስን የመረጡበትን ምክንያት ሲያስረዱ "እሱ ይበልጥ ንጹህና ያማረ ነው" ብለዋል። ነጭ ልብስ ላይ ጥቃቅን ቆሻሻዎች እንኳን ወዲያው ስለሚታዩ፣ ሰውየው ልብሱን ቶሎ እንዲያጥብና ሁልጊዜም ንጹህ ሆኖ እንዲቆይ ያደርገዋል። ይህ ውጫዊ ንጽህና ደግሞ የውስጥ (የልብ) ንጽህና ማሳያና መዳረሻ ተደርጎ ስለሚወሰድ ነው ይላሉ፡፡

ነጭ ቀለም ያለው ልብስ ዋነኛ ትኩረቱ ንጽህና ነው፡፡ የአካል ንጽህና ነጸብራቁ የልብ ንጽህና መገለጫ ሆኖ ይታያል። በእርግጥ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ልብሳቸው ነጽቶ ውስጣቸው ሊቆሸሽ ይችላል። ነገር ግን ሰው ላዩን ንጹህ ባደረገ ልክ ደግሞ ልቡን ንጹህ የማድረግ ሁኔታው ይጨምራል፡፡ እና በዋናነት የሚፈለገው እና ዓላማው ውስጥን እንደ ነጭ ቀለም ንጹህ ማድረግ ነው በማለት ኡስታዝ ፉአድ ያብራራሉ፡፡

በእስልምና ትልቁ የአምልኮ ሥነ-ስርዓት በሆነው በሐጅ (የመንፈሳዊ ጉዞ) ወቅት፣ ከዓለም ዙሪያ የሚሰበሰቡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሙስሊሞች ያሉበትን የሀብት፣ የስልጣን፣ የዘር እና የባህል ልዩነት በሙሉ ትተው ተመሳሳይ ነጭ ልብስ ይለብሳሉ። ይህም በፈጣሪ ፊት ሁሉም ሰው እኩል መሆኑን፣ ንጉስም ሆነ ምስኪን፣ ነጭም ሆነ ጥቁር ልዩነት የሌላቸው አንድ መሆናቸውን የሚያሳይ ታላቅ የተምሳሌት ቀለም ነው።

እንዲሁም የአርብ ቀን (ጁሙዓ) ለሙስሊሞች የሳምንቱ ታላቅ የጋራ የአምልኮ ቀን ነው። በዚህ ቀን ወደ መስጂድ ከመሄድ በፊት ገላን መታጠብ፣ ሽቶ መቀባት እና ንጹህ ነጭ ልብስ መልበስ እጅግ የተወደደ ነው። ይህም ለዕለቱ የሚሰጠውን ክብርና መንፈሳዊ ዝግጅት ያሳያል።

የአል ኢምራን ቁራን አካዳሚ መስራች ወጣት ኑራዲስ ሰኢድ በበኩሉ፤ ነጭ ቀለምና ልብስ በእስልምና አስተምህሮ በህይወት ብቻም ሳይሆን እስከ ሞት ድረስ የተመረጠ ቀለም ነው በማለት ያስረዳል፡፡ ወጣቱ "ሙታኖቻችሁንም በነጭ ልብስ ከፍኑ" የሚለውን የነብዩ መሐመድ ቃል ነጭ ቀለም በእስልምና ኃይማኖት ውስጥ ያለውን ትልቅ ስፍራ የሚያሳይ መሆኑን ጠቅሷል።

በእርግጥም የነጭ ቀለም ክብርና አገልግሎት በሰው ልጅ ህይወት ብቻ የሚያበቃ አይደለም። አንድ ሙስሊም ከዚህ ዓለም በሞት በሚለይበት ጊዜ፣ አስከሬኑ (ጀናዛው) ታጥቦ ወደ ቀብር ከመወሰዱ በፊት የሚከፈነው በነጭ ጨርቅ ነው። ይህም ሰውየው ወደ አኺራ (ወደሚቀጥለው ዓለም) ሲሄድ ንጹህ ሆኖ እንዲሄድ ካለው ምኞትና አስተምህሮ ጋር የተያያዘ ነው። ስለዚህ ነጭ ቀለም በእስልምና ኃይማኖት ውስጥ የንጽህና፣ የሰላም፣ የመረጋጋት፣ የእኩልነት እና የመንፈሳዊ ከፍታ ትልቅ መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል።

## አረንጓዴ

በእስልምና አስተምህሮ እና ባህል ውስጥ አረንጓዴ ቀለም እጅግ የላቀ፣ የተከበረና ልዩ ቦታ ያለው ሌላኛው ቀለም ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት በቀጥታ ከቅዱስ ቁርዓን አንቀጾች፣ ከነብዩ አስተምህሮና ተግባር እንዲሁም ከጀነት መገለጫዎች ጋር የተያያዘ ስለሆነ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ነብዩ መሐመድም በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ አረንጓዴ ልብስ ለብሰው ታይተዋል ይላሉ ኡስታዝ ፉአድ።

ከነብዩ መሐመድ ልብሶች መካከል አረንጓዴ ቀለም ያላቸው ልብሶች ነበሩ። እነዚህን ልብሶች ይወዱና ይለብሱ እንደነበር በሀዲሶች ተዘግቧል። ሰሃባዎችም ውብ አረንጓዴ ልብስ ለብሰው እንዳዩአቸው መስክረዋል። ስለዚህ ሙስሊሞች ይህንን ቀለም መልበስ የነብዩን ሱና እንደመከተል አድርገው ይቆጥሩታል።

ኡስታዝ ፉአድ እና ወጣት ኑራዲስ ለአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍል እንደተናገሩት የጀነት ሰዎች ከሐር የተሰሩ አረንጓዴ ልብሶችን እንደሚለብሱ እና አረንጓዴ መደገፊያዎችን እንደሚደገፉ እንዲሁም ውብ በሆኑ ምንጣፎች ላይ እንደሚቀመጡ ተናግረዋል።

ከዚህ ባለፈም በተፈጥሮም አረንጓዴ ቀለም ተፈጥሮን፣ ልምላሜን፣ ህይወትን፣ እድገትን እና የተፈጥሮን ውበት (ለምሳሌ ዝናብ ሲዘንብ መሬት በአረንጓዴ ዕፅዋት መሸፈኗን) ያሳያል። እስልምና ደግሞ የህይወትና የሰላም ኃይማኖት በመሆኑ፣ ቀለሙ ከእምነቱ መንፈሳዊ እሴቶች ጋር ይጣጣማል።

እንዲሁም በታሪክም ሆነ በአሁኑ ዘመን በርካታ የሙስሊም አገሮችና ተቋማት በሰንደቅ ዓላማዎቻቸው፣ በባህላዊ አልባሳቶቻቸው፣ በመንፈሳዊ ሥነ ስርዓቶች እና በመንዙማና ነሺዳ ሥነ ሥርዓቶች ላይ አረንጓዴ ቀለምን በስፋት ይጠቀማሉ።

በአጠቃላይ፣ አረንጓዴ ቀለም በእስልምና ውስጥ የንጽህና፣ የሰላም፣ የህይወት እና የጀነት ተስፋ መገለጫ ተደርጎ የሚወሰድ በመሆኑ በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ ልዩ ውበትና ክብር አለው፡፡

## ጥቁር ቀለም

በእስልምና ኃይማኖት ውስጥ ቀለማት የላቀ ቦታና የየራሳቸው የሆነ መንፈሳዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ ትርጉም አላቸው።

ወደ ገጽ 20 ዞሯል

ከዳግማዊ ምኒልክ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ጋር በመተባበር በየአስራ አምስት ቀኑ የሚቀርብ

# ጥናቱ ያመጣው ብሩህ ተስፋ

- **በጥናቱ ከተካተቱ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ካለባቸው 545 አዳጊዎችና ወጣቶች መካከል 87 ነጥብ 3 በመቶ የሚሆኑት በስድስት ወራት ውስጥ የቫይረስ መጠናቸው መቀነሱ ተመላክቷል**

**በሸዋርካብሽ ቦጋለ**

በዓለም አቀፍ ደረጃ የኤች.አይ.ቪ ፀረ-ቫይረስ መድኃኒት ተደራሽነት ካለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ወዲህ ከፍተኛ መሻሻል አሳይቷል። በአሁኑ ወቅት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች መድኃኒቱን በማግኘታቸው የቫይረሱን ስርጭት ለመግታትና ሞትን ለመቀነስ ተችሏል። ይሁን እንጂ የቫይረስ መጠንን በደም ውስጥ በማሳነስ ረገድ የሚፈለገውን ግብ ለመምታት አሁንም ግለሰቦች መድኃኒታቸውን በአግባቡ መውሰድና ጤናማ የአኗኗር ዘይቤን መከተል ይኖርባቸዋል። የቫይረስ መጠንን መቆጣጠር ለታካሚው ጤና መጠበቅ ብቻ ሳይሆን፣ ቫይረሱ ወደ ሌላ ሰው የመተላለፍ እድሉን ወደ ዜሮ በማውረድ ረገድ የሚጫወተው ሚና የላቀ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው።



ፎቶ- ከገፀ ድር
የጸረ ኤች.አይ.ቪ መድሐኒት በአግባቡ መውሰድ በደም ውስጥ ያለን የቫይረስ መጠን መቀነስ ይረዳል

የመድኃኒት አቅርቦት መቆራረጥ፣ የቫይረስ መጠን ምርመራ በየጊዜው አለመደረግና የታካሚዎች የክትትል ማነስ አሁንም ለችግር የሚያጋልጡ ክፍተቶች ናቸው። እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት የጤና ተቋማት የምርመራ መሣሪያዎችን ማዘመን፣ የመድኃኒት ክምችትን በአግባቡ ማስተዳደርና ታካሚዎችን የሚያበረታቱ የምክር አገልግሎቶችን ማስፋፋት ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም በሕብረተሰቡ ዘንድ ያለውን መገለል በማስቀረትና ግንዛቤን በማሳደግ፣ ሁሉም ታካሚዎች ያለምንም ፍርሃት የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ለነገ የማይባል መፍትሔ ነው።

በኤች.አይ.ቪ ፀረ-ቫይረስ ህክምና ላይ ላሉ ታካሚዎች የቫይረስ መጠን መቀነስ ማለት በጣም ጠቃሚ እና የህክምናው ዋነኛ ግብ የሆነ ደረጃ ላይ መድረስ እንደሆነ የህክምና ባለሙያዎች ያስረዳሉ። እንደ ባለሙያዎች ማብራሪያ፣ በደም ውስጥ የሚገኘው የቫይረስ መጠን በምርመራ ማሽን ሊታወቅ ከሚችልበት ደረጃ በታች ዝቅ ሲል የቫይረስ መጠን መቀነስ የሚባል ሲሆን፣ ብዙውን ጊዜ በአንድ ሚሊ ሊትር ደም ውስጥ ያለው የቫይረስ ቅጂ ከ50 በታች ሲሆን የቀነሰ ይባላል።

ይህ ትልቅ ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚገባ ነጥብ እንደሆነ የሚያስቀምጡት ባለሙያዎቹ ይህም ቫይረሱ ከደም ውስጥ ጠፍቷል ወይም ታማሚው ድኗል ማለት ሳይሆን ቫይረሱ በጣም ደካማ ከመሆኑ የተነሳ በምርመራ ማሽን ሊታይ ወይም ማሽኑ ሊያገኘው አለመቻሉን የሚያሳይ ነው፡፡ በእንደዚህ ሁኔታም ቫይረሱ በተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ውስጥ ተደብቆ ሊቆይ እንደሚችልም ነው ከዳግማዊ ምኒሊክ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ያገኘነው መረጃ የሚያመላክተው።

በኮሌጁ በህብረተሰብ ጤና ትምህርት ክፍል ውስጥ መምህር በሆኑት ረዳት ፕሮፌሰር ደሳለኝ አጀማ ዋና የጥናት ተመራማሪነት እና ሌሎች የዘርፉ ባለሙያዎች በአዲስ አበባ የመንግሰት ሆስፒታሎች ውስጥ በኤች.አይ.ቪ ፀረ-ቫይረስ ህክምና ላይ ባሉ አዳጊዎችና ወጣቶች የቫይረስ መጠን መቀነስን በተመለከተ በ2017 ዓ.ም ጥናት አካሂደዋል፡፡ በጥናቱ የተካተቱ ወጣቶች የቫይረስ መጠናቸው ከ50 በታች የሚሆነው በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ነው የሚለውን ከማመላከታቸውም ሌላ የመቀነሱ ዋና ዋና ምክንያቶችንም አስቀምጠዋል፡፡

ጥናቱ በከተማ አስተዳደሩ ስር ባሉ አራት ሆስፒታሎች የኤች.አይ.ቪ ፀረ-ቫይረስ ህክምና የሚያደርጉ 545 አዳጊዎች እና ወጣቶችን ያሳተፈ ነው፤ በተለይም እ.ኤ.አ ከ2019 እስከ 2024 ባላቸው የህክምና መዝገብ ላይ ተመስርቶ እንዲሁም ከአራቱም ሆስፒታሎች አራት ወንድና አራት ሴት ኤች.አይ.ቪ ኤድስ በደማቸው ያለባቸው ወጣቶችና በጉዳዩ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ ያላቸው የጤና ባለሙያዎችና ባለድርሻ አካላት ተመርጠው የቫይረስ መጠን እንዳይቀንስ የሚያደርጉ ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው? የሚለውን ቃለመጠይቅ በማድረግ መሰራቱን ጠቅሰዋል፡፡

በጥናቱ ከተካተቱ 545 አዳጊዎችና ወጣቶች መካከልም 87 ነጥብ 3 በመቶ የሚሆኑት በስድስት ወራት ውስጥ የቫይረስ መጠናቸው መቀነሱ ተመላክቷል፡፡ ይህ ጥናት በ2030 ዓ.ም ኤች.አይ.ቪ ኤድስ የህብረትሰብ ጤና ችግር መሆኑ እንዲያበቃ ከሚለው ግብ አኳያ ጥሩ አፈፃፀም መኖሩን የሚያመላክትና ከተለያዩ ጥናቶች ጋርም የሚስማማ አይነት ግኝት ቢሆንም መዘናጋት እንደማያስፈልግ የሚጠቁምም ነው፡፡

ቀደም ባሉት ጊዜያት ሰፊ የግንዛቤ ስራ ሲሰራበት የነበረው ኤች.አይ.ቪ ኤድስ አሁንም የዓለም ህብረተሰብ የጤና ችግር ሆኖ መቀጠሉን አስታውሰው፣ በተወሰነ ጊዜ ሰፊ የግንዛቤ ስራ ቢሰራበትም በሌሎች የጤና ችግሮች ምክንያት እየተረሳ አሁን ላይ እንደ አዲስ እየተስፋፋ መሆኑን አንስተዋል፡፡ የጥናቱ ትኩረት ከ10 እስከ 24 ዓመት እድሜ ላይ ያሉ ወጣቶች ላይ ነው፡፡ በዚህ እድሜ ላይ ያሉ ወጣቶች አካላዊ እድገት፣ ከህፃንነት ወደ ጉርምስና የሚሸጋገሩበት ጊዜ መሆኑ፣ የሰነ ልቦና ጫናዎችን ጨምሮ ለተለያዩ ፈተናዎች ተጋላጭ የሚሆኑ ናቸው፡፡

በእነዚህ የእድሜ ክልሎች ውስጥ የቫይረስ መቀነስ ማለት ቫይረሱ ወደ ሌሎች እንዳይተላለፍ የሚሆንበት የቫይረስ መጠን ነው፡፡ የቫይረስ መጠን መተላለፍ ወደማይችልበት ቁጥር ላይ ደርሷል ለማለት የተለያዩ መለኪያዎች ሲኖሩ የዓለም ጤና ድርጅት (WHO) የቫይረስ መጠን መቀነስ በፕሮግራም ደረጃ ከ1000 copies/mL በታች አድርጎ ይተረጉመዋል፤ ይህም በዋነኝነት አነስተኛ ግብዓት ባለባቸው አካባቢዎች ተግባራዊ ለማድረግ እንዲያመች ታስቦ ነው። ይሁን እንጂ ከ50 RNA/mL በታች መሆኑ ይበልጥ ጥብቅ እና በህክምናው ዘርፍ ተመራጭ የሆነ ግብ ሲሆን፣ ይህ ጥናት የተጠቀመውም ከ50 RNA/mL በታች ያለውን መለኪያ ነው።

50 RNA/mL የቫይረስ መጠን መቀነስ የሚለው አገላለጽ የኤች.አይ.ቪ መራባት በከፍተኛ ደረጃ በቁጥጥር ስር የዋለበትን ሁኔታ የሚያመለክት ሲሆን፣ ይህም ውጤታማ የሆነ የመድኃኒት አወሳሰድ እና የተሻለ የህክምና ምላሽ መኖሩን ያሳያል ብለው፣ ለጥናቱ ጥቅም ላይ የዋለውም ከ50 RNA/mL በታች ያለው መለኪያ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የኤች.አይ.ቪ የቫይረስ መጠን እንዳይቀንስ በዋናነት በግለሰብ ደረጃ ያሉ ተፅዕኖዎች ተብለው የተለዩት መድኃኒት መርሳትና አብዛኛዎቹ ልጆች ከእናት ወደ ልጅ የተላለፈባቸው በመሆኑ ከህፃንነታቸው ጀምሮ መድኃኒት ሲወስዱ የቆዩ በመሆናቸው በመሰላቸት መድኃኒታቸውን በአግባቡ የማይወስዱ መሆኑ ተጠቃሽ ናቸው። በተጨማሪም ከጤና ባለሙያዎችና ከራሳቸው ከወጣቶቹ በተገኘው መረጃ መሰረት የተለየው ዋነኛ ችግር የስነ ልቦና ጫና ነው፡፡ ከኤች.አይ.ቪ ጋር የሚኖሩ ወጣቶች ለተለያዩ የስነ ልቦና ጫናዎች የተጋለጡ ናቸው፡፡ በዚህም ተስፋ በመቁረጥ መድኃኒታቸውን በትክክል አይወስዱም፡፡

በጤና ተቋም ደረጃ ከሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች ደግሞ የአገልግሎት መዘግየት፣ የላብራቶሪ ማሽኖች ብልሽት፣ በተለይ ወጣቶች ሚስጥራቸው እንዲጠበቅ የሚፈልጉ ቢሆኑም ከኤች.አይ.ቪ ጋር ለሚኖሩ ወጣቶች ለብቻቸው የተዘጋጀ የህክምና ማዕከል በበቂ ደረጃ አለመኖር፡፡ የህክምና ክፍሎቹ ከአዋቂዎች ጋር አብሮ መሆኑ እንደ እንቅፋት ተቀምጧል፡፡

ከዚህም ሌላ አንዳንድ ታካሚዎች ከኢኮኖሚ ችግር አኳያ ምግብ በአግባቡ አለመመገብ ብቻ ሳይሆን፣ የሚመገቡት ምግብ ከመድኃኒቱ ጋር አለመሄድ ያጋጥማል፡፡ በደንብ ካልተመገቡ መድኃኒቱ እንደሚከብዳቸው እንዲሁም በአንዳንድ የኃይማኖት ተቋማት ውስጥ ኤች.አይ.ቪን እንደማንኛውም ህመም ያለማየት ችግር መድኃኒት ከመውሰድ ይልቅ በተለያዩ ቤተ እምነቶች የሚደረጉ ነገሮች ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ መገፋፋት ያሉ የኃይማኖት ተፅዕኖዎች በመኖራቸው ለህክምና መቋረጥ ምክንያት እንደሚሆን ነው፡፡

በማህበረሰብ ደረጃ እንቅፋት ተብለው የተለዩት እስከ አሁን ድረስ በትምህርት ቤት፣ በመኖሪያና በስራ አከባቢዎች መገለል አለ፡፡ እነዚህ አዳጊዎችና ወጣቶችም መገለልን በመፍራት መድኃኒታቸውን ተደብቀው ለመውሰድ ይገደዳሉ፡፡ ማህበረሰቡ ስለ ኤች.አይ.ቪ ያለው ግንዛቤ አሁንም አናሳ መሆን፣ የድጋፍ ማጣት ችግር በተለይም ወላጅ የሌላቸው አዳጊዎች መድኃኒቱን እንዲወስዱ የሚያስታውሳቸው፣ የሚያግዛቸውና የሚንከባከባቸው ሰው ማጣት እንደ ትልቅ ችግር ተለይቷል፡፡

በጤና ባለሙያዎች እና ተቋማት ረገድም የቫይረስ መጠን እንዲቀንስ ወይም መድኃኒታቸውን በአግባቡ እንዳይወስዱ የሚያደርጓቸው ምቹ ሁኔታዎችም አሉ፡፡ ደግና የማይፈርጁ የጤና ባለሙያዎች መኖራቸው ብቻ ሳይሆን ያልተቋረጠ የመድኃኒት አቅርቦት በጤና ተቋማት መኖሩ በበጎ ጎን የሚጠቀስ ነው፡፡ የቫይረስ መጠኑ መቀነስ ወይም መጨመር በላብራቶሪ የደም ምርመራ የሚታወቅበት አሰራር መኖሩን የጠቀሱት ረዳት ፕሮፌሰር ደሳለኝ የቫይረስ መጠን መጨመር (ወይም የህክምና መስተጓጎል ሲኖር) በሰውነት ላይ የሚታዩ ምልክቶች ቢኖሩም ብዙውን ጊዜ የቫይረስ መጠን መጨመር በምልክት ሳይሆን በምርመራ ቀድሞ ማወቅ ተገቢ እንደሆነ ነው የገለፁት።

አንድ የታመመ ሰው መድኃኒት መውሰድ ሲጀምር ጥሩ የሆነ የጤና መሻሻሎችን እንደሚያሳይ ሁሉ የቫይረስ መጠን ቀነሰ ሲባልም በተዘዋዋሪ በጥሩ ሁኔታ ክትትል እየተደረገ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ የቫይረስ መጠን በሰውነት ውስጥ መጨመር ደግሞ በአግባቡ ክትተል አለመደረጉን ይህም የሰውነት በሽታ መከላከል አቅምን እያዳከመ ስለሚሄድ በቂ እረፍት ቢደረግም የማይለቅ የሰውነት መዛል እና ድካም፣ የሰውነት ክብደት መቀነስ፣ ተደጋጋሚ ትኩሳት እና ላብን ጨምሮ አጠቃላይ የጤና መጓደል ወይም የኤድስ ምልክቶች ይታያሉ፡፡

# ልጆች፣ ሰለመታዘዝ ጥቅም ምን ያህል ታውቃላችሁ?

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ልጆች እንኳን ለ1447 ዓመተ ሂጅራ ዒድ አል አድሃ- አረፋ በዓል በሰላም አደረሳችሁ! በዛሬው ጽሑፋችን ከአረፋ በዓል ስለምንማረው ታላቅ ቁም ነገር መታዘዝ ነው።

ዒድ አልአድሃ- አረፋ በዓል ነብዩ ኢብራሂም ለፈጣሪያቸው እንዲሁም ኢስማኤል ለአባቱ ለነብዩ ኢብራሂም፤ እንዴት እንደታዘዙ እና በመታዘዝ የሚገኙ ጥቅሞችን ነው፡፡ ለዚህም ማብራሪያ የሰጡን በቡራዩ ሸክላ መስጂድ የኃይማኖት አስተማሪ ዑስታዝ ከሚል ኸይሩ ናቸው፡፡

ኡስታዝ ካሚል ኸይሩ እባላለሁ። በቡራዩ ሸክላ መስጂድ የኃይማኖት አስተማሪ ነኝ፡፡ ልጆች በእስልምና እምነት አስተምህሮት መታዘዝ ማለት የተሰጠንን መመሪያ ወይም ትዕዛዝ ተቀብለን መፈጸም ወይም ማከናወን ማለት ነው። ትዕዛዙም ለምናውቀው ሰው፣ ለእናትና አባታችን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ማክበር አለብን፡፡


ፎቶ- ከገፀ ድር
የፈጣሪ እዝነት፣ የነብዩ ኢብራሂም እምነትና የልጃቸው ኢስማኤል ታዛዥነት የተገለፀበት የአረፋት ተራራ

ልጆች ዒድ አል አድሃ- አረፋ በዓል ነብዩ ኢብራሂም ለፈጣሪያቸው፤ ልጃቸው ኢስማኤል ደግሞ ለአባታቸው ያሳዩት ፍጹም ታዛዥነት የታየበት ነው። የነብዩ ኢብራሂም ልጅ ኢስማኤል ካደገ በኋላ አላህ "ልጅህን እንድትሰዋ ታዝዘሃል" የሚል ትእዛዝ ለኢብራሂም በህልማቸው አሳያቸው፡፡ ነብዩ ኢብራሂምም በህልማቸው ያዩትን በዝምታ አላለፉትም። ምንም እንኳን ነብዩ ኢብራሂም የፈጣሪያቸውን ትዕዛዝ ለመፈጸም ዝግጁ ቢሆኑም የልጃቸውንም ታዛዥነት ለመረዳት አነጋግረውታል። "ልጄ ሆይ እኔ በህልሜ አንተን እንድሰዋህ አይቻለሁ፤ እስቲ አንተም ነገሩን ተመልከት ምን ይታይሃል" አሉት፡፡ ልጁም "አባቴ ሆይ የታዘዝከውን ፈፅም፤ የአላህን ፈቃድ በእኔ ላይ ለመፈፀም ዝግጁ ነኝ፡፡ የአላህ ትዕዛዝ ነው ከእኔ የሚበልጠው" አላቸው፡፡

ነብዩ ኢብራሂም ልጃቸው ኢስማኤልን ለመስዋት ወደ አረፋት ተራራ ወጡ። ነብዩ ኢብራሂም ከቦታው ደርሰው ልጃቸውን ሊሰዉ ሲሞክሩ "ኢብራሂም ታላቅነትህን አስመስክረሃል እና እርዱን አቆየው" የሚል የአላህ መልዕክተኛ (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) ድምፅ ተሰማ። በእስማኤል ምትክም በጉ ታርዶ ኢብራሂም እና ኢስማኤል ወደ መካ ተመለሱ፤ ይህም ቀን የዒድ አል አድሃ አረፋ በዓል ሆነ።

አያችሁ ልጆች ነቢዩ ኢብራሂምም ለፈጣሪያቸው፣ ልጃቸው ኢስማኤልም ለአባታቸውና ለፈጣሪያቸው ምን ያህል ታዛዥ እንደሆኑ! መታዘዝ ምን ያህል ጥቅም ወይም ትርፍ እንደሚያስገኝ ተረዳችሁ?

አዎ እንግዲህ ልጆች ከዚህ ታሪክ የምንማረው በየትኛውም መልኩ ከሁሉም በላይ ፈጣሪን እንዲሁም ታላላቆችን በተለይም ወላጆችን ማክበርና መታዘዝ እንደሚገባንና ታዛዥነት እንደ ኢስማኤል ከመታረድ እንደሚያድን ነው፡፡

ልጆች ስለመታዘዝ በታላቁ መጽሐፍ ቁርዓን ምዕራፍ 31 ሉቁማን የሚባል በጣም ትልቅ ምሁር ነበረ፡፡ ጥበበኛም ነበር፡፡ ልጁንም ከጌታህ ጋር ያለህ ግንኙነት እንዳይበላሽ ልንገርህ አለው፤ ከዚያም ለወላጆቹ ታዛዥ መሆን እንዳለበት መከረው፡፡ ከማንኛውም ከሰው ልጆች በምትኖር ሰዓት ጀርባህን አትስጥ፣ ጎርባጣ አትሁን አለው። ልጁም የአባቱን ምክርና ትዕዛዝ ያከብር ስለነበር መልካም ሥነ ምግባር ያለው፣ ሰዎችን የሚያከብርና በሰዎች ዘንድም የተወደደ ነበር፡፡ ስለዚህ ልጆች እናንተም ወላጆቻችሁን እና ታላላቆቻችሁን የምታከብሩ ከምንም በላይ ደግሞ ፈጣሪያችሁን የምትፈሩ፣ ጥሩ ሥነ ምግባር ያላችሁ መሆን አለባችሁ፡፡

ልጆች አንድ ሰው ወደዚህች ምድር ተወልዶ ሲቀላቀል መጀመሪያ ሊፈራውም፣ ሊያከብረውም፣ ሊታዘዘውም የሚገባው ፈጣሪን ነው። ከዚያም ወላጆችን ይታዘዝ፡፡ ልጆች እምነት ማለት በተግባር መኖር ነው። ኢስማኤል ለአባቱ ሲል ህይወቱን መስዋዕት ሊያደርግ ፈቃደኛ ከሆነ እኛስ ወላጆቻችንን ማክበር፣ ስሜታችንን መግታት፣ እንዲህ አድርጉ የሚሉንን ማድረግ ለምን አቃተን ብላችሁ ራሳችሁን መጠየቅ ይገባችኋል፡፡ መጠየቅ ብቻም ሳይሆን በተግባር ማሳየት አለባችሁ፡፡

የአላህ መልዕክተኛ (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) ከእኛ መካከል ለትንሹ ያላዘነ ትልቁን ያላከበረ ከእኛ አይደለም ወይም አማኝ ነኝ ሊል አይችልም ብለዋል፡፡ ልጆች፤ ፈጣሪን ስታከብሩ ወላጆቻችሁን ታከብራላችሁ፣ ወላጆቻችሁን ስታከብሩ ደግሞ ጎረቤቶቻችሁንና ጓደኞቻችሁን ታከብራላችሁ፤ ታዛዥ ትሆናላችሁ። ይህም ማለት እምነታችሁን በተግባር አሳያችሁ ማለት ነው፡፡

ፈጣሪያችሁን ስትፈሩ፣ ወላጆቻችሁን ስትታዘዙ፣ ታላላቆቻችሁን ስታከብሩና ለታናናሾቻችሁ ስታዝኑ የምታገኟቸው ጥቅሞች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል የመጀመሪያው ጀነት ወይም ገነት መግባት ነው፡፡ የአምላክ በረከትና ጥበቃም ይደረግላችኋል፡፡ ከጥፋት እንድትድኑም ይረዳችኋል፡፡ ለአምላክ ቃል መታዘዝ በአምላክና በሰዎች ዘንድ የተወደዳችሁ ያደርጋችኋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ በመታዘዛችሁ የምታገኙት ጥቅም በዚህች ምድር ስትኖሩ ያማረ ደስ የሚል ህይወት እንድትኖሩ፣ በሰዎቻ ዘንድ እንድትወደሱ፣ እናንተንም ስታድጉ ሰው እንዲያከብራችሁና እንዲታዘዛችሁ፣ ራሳችሁም እንድትከበሩ ያደርጋችኋል፡፡

ልጆች ታዛዥነት የተባረከ፣ ጤናማ እና ረጅም እድሜ ያለው ህይወት ያስገኛል። መታዘዝ የቤተሰብ፣ የማህበረሰብ እና ከአምላካችሁ ጋር ያለውን ግንኙነት ያጠናክራል። በአጠቃላይ መታዘዝ ራስን መግዛት፣ ሰላም እና ደስታን የሚያስገኝ የህይወት መርህ በመሆኑ በተግባር ልታሳዩት ይገባል፡፡

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ





## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**እህል በልቶ የማይጠጣ ምንድን ነው?**

**መልስ፡-** *ሀ. ነቀዝ*

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**ሆዷን ሞልታ ሌላውን በሆዷ ሰክታ**

ሀ. አይጥ
ለ. ጃርት
ሐ. እንቁራሪት

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ፡፡**

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል የመንግስት አገልግሎት ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# በዲጂታል አገልግሎት የሴቶች መሪነት ሲቃኝ

**“የአዲስ መሶብ ተተኪ አመራር የሚወጣው ከአዲስ መሶብ ሠራተኛ ነው”**

**በአዲስ መሶብ ዋና መሥሪያ ቤት የጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ ደመቁ ካሣሁን**

**በደረጀ ታደሰ**

የተቋቋመበትን ተልዕኮ ለመፈፀም እንደተቋም ተቋቁሞ ወደ ሥራ ከገባ አንድ ዓመት እንኳን አልሞላውም፤ የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ያከናወነውንና እያከናወነ ያለውን ስንመለከት፤ ለዓላማ ታምኖ በትጋት መሥራት የሚያስገኘውን ከፍ ያለ ውጤት እንረዳለን፡፡ አዲስ የሥራ ባህል፣ የሥራ ከባቢ፣ ዘመናዊና ዲጂታላይዝድ አሠራር ... በአዲስ ይዞ የመጣውና፣ በዚህም የተገልጋይን እርካታ ከፍ ማድረጉን ተገልጋዮች ራሳቸው የመሰከሩለት አዲስ መሶብ ለበለጠ ስኬት መትጋቱን ቀጥሏል።



ፎቶ- ከፋይል

የአዲስ ሞሰብ አንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ወ/ሮ ደመቁ ካሣሁን ስልጠና ሲሰጡ

ጷጉሜ 5 ቀን 2017 ዓ.ም. አንድ ብሎ ሥራውን የጀመረው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት ዛሬ ላይ፤ የማዕከላቱን ቁጥር ወደ ስድስት አድርሷል፡፡ እንደ ከተማ ብሎም እንደ አገር አዲስ የሆነውን የአዲስ መሶብ ተንቀሳቃሽ አገልግሎትን አስተዋውቋል።

ገና በማለዳው፣ በተጨባጭ ውጤቱ፣ ብዙ እንዲነገርለት እያስገደደ ስላለው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት ተቋም፤ ከስኬት ነዶው ውስጥ አንዷቷን ዘለላ መዘን በዚህ ጽሑፍ እንቃኛለን፡፡ ይህም፤ “በተቋሙ ያለውን የሴት አመራሮች ሚናን” የሚመለከት ሲሆን፤ ለዚህ ጉዳይ መነሻ ሆነን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለአገልግሎት ከበቁ አምስት የአዲስ መሶብ ማዕከላት(አራዳ የሚገኘውን ዋና መሥሪያ ቤቱን ሳይጨምር) ፡- የአራቱ ሥራ አስኪያጆች(አመራሮች) ሴቶች መሆናቸው ነው፡፡ ከተቋሙ ባገኘነው መረጃ መሰረት፤ በሴት ሥራ አስኪያጆች እየተመሩ ያሉት የአዲስ መሶብ ማዕከላት (የቦሌ፣ የአዲስ ከተማ፣ የቂርቆስ እና የልደታ ማዕከላት) ናቸው፡፡

ወይዘሮ ዓለም ሰዒድ፣ የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት ልደታ ማዕከል ሥራ አስኪያጅ ናቸው፡፡

በመንግሥት ተቋማት ላይ ከባለሙያነት እስከ አመራርነት የዘለቀ፣ የአስር ዓመት ዕድሜን ያስቆጠረ የሥራ ልምድ እንዳላቸው ያስታወሱት የአዲስ መሶብ የልደታ ማዕከል ሥራ አስኪያጇ፤ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ በተለያዩ ተቋማት ራሳቸውን በዕውቀት፣ በክህሎት፣ በአመራር ጥበብና ተያያዥ ጉዳዮች ሲያበቁ መቆየታቸውን ይናገራሉ። እስከ ቡድን መሪ የደረሰ የአመራርነት ኃላፊነት ላይም መቆየታቸውን ይጠቅሳሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት ላሉበት የአዲስ መሶብ የልደታ ማዕከል ሥራ አስኪያጅነት የበቁበትን አጋጣሚም ሲያስታውሱ፤ “ጷጉሜ 5 ቀን 2017 ዓ.ም. በይፋ አገልግሎት በጀመረው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት ዋና መሥሪያ ቤት ከተካተቱ አመራሮች እና ባለሙያዎች መካከል አንዷ ነኝ፡፡ ወደ ተቋሙ የተቀላቀልኩት፣ እንደሌሎቹ የሥራ ባልደረቦቼ ሁሉ ተወዳድሬና መመዘኛውን አልፌ ሲሆን፤ የትራፊክ ማኔጅመንት ቡድን መሪነትን ስወጣ ቆይቻለሁ፡፡ በቆይታዬም ያለኝን ዕውቀት፣ ክህሎት፣ ልምድ፣ ጊዜ ... ሳልሰስት በመስጠት ተቋሙ ውጤታማ እንዲሆን የበኩሌን አድርጌያለሁ፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ባሳየሁት አፈፃፀም፣ የቅርብ ኃላፊዎቼ እና ከፍተኛ አመራሮቼ፣ ‘ከፍ ወዳለ የኃላፊነት ቦታ ብትመጣ ውጤታማ ሥራን ማከናወን ትችላለች’ በማለት የልደታ ማዕከልን በሥራ አስኪያጅነት እንድመራ ተደርጌያለሁ፡፡” በማለት ነው፡፡

“ከበላይ የሥራ ኃላፊ የተሰጠንን ወይም በሥራ መዘርዝር ላይ የተቀመጠልንን ተልዕኮ በጊዜ፣ በጥራትና በፍጥነት ማሳካትን፣ ሥራን በባለቤትነት ይዞ፣ ተባብሮና ተጋግዞ መሥራትን ... የመሳሰሉ ወሳኝ የሥራ ላይ እሴቶችን ከአዲስ መሶብ ዋና መሥሪያ ቤት ተምሬበታለሁ፡፡” የሚሉት ወይዘሮ ዓለም፤ የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት ልደታ ማዕከል ሥራ አስኪያጅ ሆነው እንዲያገለግሉ ኃላፊነት በተሰጣቸው ወቅት ሁለት ተቃራኒ ስሜት (የደስታ እና የፍርሃት) እንደተሰማቸው ይገልፃሉ፡፡ ደስታው፤ በዚህ ለትልቅ ዓላማ በተቋቋመ እና ከማለዳው ስኬታማ ጉዞን በጀመረው ተቋም ውስጥ ታሪካዊ የሆነ የኃላፊነት ቦታን መያዝ በራሱ የማይገኝ ዕድል መሆኑን በመገንዘብ የመነጨ ሲሆን፣ ፍርሃቱ ደግሞ የተልዕኮውን ክብደት ከማየት የመጣ እንደሆነ ያብራራሉ፡፡ ይህም ሆኖ፤ በተመደቡበት ቦታ ላይ ያላቸውን ዕውቀት፣ ክህሎት፣ ጊዜ ... በመስጠት ለስኬታማነት ጥረት እያደረጉ መሆናቸውን አልሸሸጉም፡፡

በመንግሥት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታዩ ችግሮችን በመቅረፍ፣ የተገልጋይ ቅሬታ እና የመልካም አስተዳደር ጉድለት መነሻነቱን በማቃለል፣ የተገልጋዮችን እርካታ በከፍተኛ ደረጃ የሚያሻሽል ፈጣን፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ፍትሐዊ የመንግሥት አገልግሎት ለማቅረብ ጥረት እያደረገ በሚገኘው የአዲስ መሶብ ተቋም ውስጥ ያለው የሥራ ባህልና ልምድ ትልቁን ሚና እንደሚጫወት የገለጹት በአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግሥት አገልግሎት ዋና መሥሪያ ቤት የፅሕፈት ቤት ኃላፊዋ ወይዘሮ ደመቁ ካሣሁን ናቸው፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ ተቋሙ የተጣለበትን ወሳኝ ተልዕኮ ለማሳካት ተቋማዊ ግንባታ ላይ አተኩሮ ይሠራል። ለስኬቱ አጋዥ ከሆኑ ቁልፍ አቅሞች መካከል ደግሞ በዕውቀት፣ በክህሎት፣ በሥነ ምግባር የበቃ የሠው ኃይል ማሟላት አንዱ ነው፡፡ ይህንን መነሻ በማድረግም ከዋና መሥሪያ ቤት ጀምሮ በሂደት ለአገልግሎት በበቁ ማዕከላት ላይ ተልዕኮውን ማስፈጸም የሚችሉ ነባርና አዳዲስ ባለሙያዎችን በማወዳደር ወደ ሥራ ማስገባት ተችሏል፡፡

የአዲስ መሶብን የሰው ኃይል ስብጥር ከጾታ አንጻር ምን እንደሚመስል የጽሕፈት ቤት ኃላፊዋ ሲገልፁ፤ “ከዋና መሥሪያ ቤት ጀምሮ እስከ ማዕከላት ያለው የሰው ኃይል የጾታ ስብጥር እኩል የሚባል ደረጃ ላይ ይገኛል። በአንዳንድ ዘርፎች ላይ (ለአብነት በተቋሙ ወሳኝና ፊት ለፊት ወንበር ላይ በሚገኙት የመረጃ መስጫ(ካውንተር) ስፍራዎች፣ በአይቲ ሲስተም ዘርፍ፣ በአስተዳደር እና ፋይናንስ ዘርፍ ...) የሴቶች ተሳትፎ ከወንዶች በልጦ ወይም ተሽሎ እናገኘዋለን፡፡ ከዚህ አለፍ ሲልም፤ የአመራርነት ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ የሴቶች ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ይህ የሆነው እንደተቋም ለሴቶች የተለየ ድጋፍ ወይም ዕድል በመሰጠቱ አይደለም፡፡ ይልቁንም ለቦታው ብቁ የሚያደርጋቸውን ዕውቀት፣ ልምድ፣ አፈጻጸም ... በማሟላታቸውና ከተፎካካሪዎቻቸው ተሽለው በመገኘታቸው ነው” በማለት ነው፡፡

የአንድ ተቋም ስኬታማነትን ከሚበይኑ ወሳኝ አቅሞች መካከል አንዱ የሆነውን የሰው ኃይል በብቃት፣ በብዛትና በጥራት ለማፍራት እንዲሁም ወደ ሥራ ለማሰማራት በሚደረገው ሂደት ውስጥ የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት ጠንካራ የአሠራር ስርዓት መዘርጋቱን የጽሕፈት ቤት ኃላፊዋ ወይዘሮ ደመቁ ጠቅሰዋል፡፡ ብቁ ሠራተኞች እና የሥራ አመራሮች ወደ ተቋሙ እንዲቀላቀሉ ከቅጥር ጀምሮ እስከ ሥራ ሂደት ድረስ የዘለቀ ጥብቅ የአሠራር ሥርዓት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ ወደ ተቋሙ እንዲገቡ የተመረጡ ሠራተኞች ወደ ሥራ ከመግባታቸው በፊት በኢትዮጵያ አቪዬሽን አካዳሚ መሰረታዊ ስልጠና ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህም ሥራን መውደድ፣ ተገልጋይን ማክበር፣ ለጊዜና ለጥራት ትኩረት መስጠት፣ ከኔነት ወጥቶ በጋራና በትብብር መሥራት ... የመሳሰሉ ወሳኝ ተቋማዊ እሴቶች በአዲስ መሶብ መዳበር መቻሉን አብራርተዋል፡፡

እዚህ ላይ አንድ ነጥብ እናንሳ፡- ሴቶችን ወደ አመራርነት እና ኃላፊነት የማምጣት ተግባር፤ ከ2010 ለውጥ በኋላ ጉልህ መሻሻል ማሳየቱ ይታወቃል፡፡ በታሪክ የመጀመሪያዋ የአዲስ አበባ ከተማ ሴት ከንቲባ የሆኑትን ወይዘሮ አዳነች አቤቤን ጨምሮ፣ በርካታ ሴቶች በሚኒስቴር እና በሌሎች ቁልፍ የአመራርነት ሥፍራ ላይ ተቀምጠዋል፡፡ ቦታውን መያዛቸው ብቻ ሳይሆን በሥራቸውም ውጤታማ መሆናቸውን እያሳዩ ይገኛሉ፡፡ ለአብነት መዲናችን አዲስ አበባ እያሳየች ላለችው እንደስሟ አበባ የመሆን ተግባር፤ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ዕውን እንዲሆኑ፣ የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት በአስደናቂ ሁኔታ እንዲከናወን፣ ተቋማት እንዲገነቡ፣ ምቹ፣ ዘመናዊ፣ ጽዱና የጎብኚዎችን ቀልብ የምትስብ መዲና የመፍጠሩ ዓላማ በአጭር ጊዜ ውስጥ ፍሬ እንዲያፈራ፤ የከንቲባ አዳነች አቤቤ ከፍ ያለ የአመራርነት ብቃት ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ግልጽ ነው።

ከዚህ በተጨማሪም፤ የጽሑፋችን ዋና ማጠንጠኛ የሆነው የአዲስ መሶብ የአንድ ማዕከል ዲጂታል የመንግስት አገልግሎት እንደተቋም እንዲቋቋም ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ቀጥሎ በፈጣን ዕድገት እንዲጓዝ እና ተስፋ እንዲጣልበት የከንቲባዋ የአመራርነት ሚና በታሪክ የሚወሳና ለብዙዎች ምሳሌ የሚሆን ነው፡፡

“የአዲስ መሶብ ተተኪ አመራር የሚወጣው ከአዲስ መሶብ ሠራተኛ ነው” የሚል ተቋማዊ መርህ እንዳለ ያነሱት የጽሕፈት ቤት ኃላፊዋ፤ ይህንን እሳቤ ለማስረጽ ዘወትር ሰኞ በሚከናወነው የሠራተኞች የእውቀት ሽግግርና የአብሮነት መርሃ ግብር ላይ በስፋትና በጥልቀት እንደሚነሳ ውይይትም እንደሚደረግበት ገልጸዋል፡፡ ከዚህ አለፍ ሲልም፤ ሴት ሠራተኞች የተሻለ አቅም እንዲገነቡ የተለያዩ ስልጠናዎች መሰጠታቸውን ጠቅሰው፤ የተሠራው ሥራ ከሚጠበቀው አንጻር ሲመዘን የሚቀረው ነገር እንዳለ አልሸሸጉም፡፡ ይህንንም ታሳቢ በማድረግ፤ አሁን በማዕከላት ሥራ አስኪያጅነት ላይ ያሉትን አመራሮችና ሌሎች የተቋሙ ሴት ሠራተኞችን በተለየ ሁኔታ የአመራርነት አቅም እንዲገነቡ በአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ስልጠና ለመስጠት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የጽሕፈት ቤት ኃላፊዋ ወደ ተቋሙ እንዴት እንደተቀላቀሉ እንደገለጹት፤ “በሥራ ሕይወቴ ውስጥ በአብዛኛው ያሳለፍኩት ከተቋማት ሪፎርም ጥናት እና ትግበራ ጋር የተያያዘ ነው። በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሠው ሀብት ልማት ቢሮ የሪፎርም የቴክኒክ አማካሪ ሆኜ ሠርቻለሁ። በተመሳሳይ በአዲስ አበባ ሥራ አመራር አካዳሚ የአመራር ማብቃት በተያያዘ ከፍተኛ አማካሪ ነበርኩ፡፡ ብዙ ተቋማት ሪፎርም ሲሰሩ እና ሲተገብሩ አማክሬያለሁ፡፡ ከተቋም ለውጥና ግንባታ(ሪፎርም) እንዲሁም ከአመራር ጋር በተያያዘ የተለያዩ ጥናትና ምርምሮች ላይ ተሳትፌያለሁ፡”

አያይዘውም፤ ይህንን የካበተ ዕውቀትና ልምዴን በአዲስ መሶብ ተቋም ውስጥ በሥራ ለመግለጥ ጥረት እያደረግሁ እገኛለሁ፡፡ በቀጣይም የተሰጠኝን ኃላፊነት በብቃትና በውጤት ከመወጣት ባሻገር ተተኪ አመራሮች እንዲወጡና በቅርቡ ለአገልግሎት በሚበቁ ማዕከላት ላይ የተቋሙን ተልዕኮ ለማሳካት የመሪነት ሚናን የሚወጡ ወጣት አመራሮች ወደ ቦታው እንዲመጡ በትኩረት እሠራለሁ። ይህ ሥራ ከግለሰብ ያለፈ እና ተቋማዊ ሆኖ የተገነባ በመሆኑ በቀጣይነትም ለከተማዋ ብሎም ለአገር ምሳሌ መሆን የሚችል ስኬት የሚያስመዘግብ እንደሆነ ያላቸውን እምነት በመግለፅ፤ ለስኬቱ ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ አሳስበዋል፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና ከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# 50 ዶሮዎች የፈቱት የኑሮ ቋጠሮ

- **በአዲስ አበባ ከተማ በቤተሰብ ደረጃ በሚሰራ የዶሮ እርባታ ስራ 20 ሺህ ግለሰቦች በዘርፉ ተሰማርተው ኑሮአቸውን እንዳሻሻሉ ተገልጿል**

**በይግለጡ ጓዴ**

የአራዳ ክፍለ ከተማ የወረዳ 6 ነዋሪ የሆነው ወጣት ዮሴፍ የሃሳብፍሬ፣ ዛሬ ላይ ፊቱ በፈገግታና በተስፋ ተሞልቶ ስለ ስኬት ሲያወራ ትናንት የነበረውን አድካሚ የስራ አጥነት ህይወት በማስታወስ ነው። ነገሮች ሁሉ የተቀየሩት በ2018 ዓ.ም መስከረም ወር ላይ እንደነበር ፈፅሞ አይዘነጋውም፡፡ ወጣት ዮሴፍና ሁለት የቤተሰቡ አባላት በአጠቃላይ ሶስት ሆነው በመንግስት በተመቻቸላቸው በቤተሰብ ደረጃ በሚሰራ የዶሮ እርባታ ስራ (ፋሚሊ ቢዝነስ) ዘርፍ ተደራጁ፤ በወቅቱ የተሰጣቸው ድጋፍ መጠነኛ የሚባል ነበር፤ 50 የዶሮ ጫጩቶች፣ የአንድ ወር የዶሮ መኖ እና የዶሮ መኖሪያ ቤት (ኬጂ)፤ አሁን ግን ስራቸውን አስፋፍተው የኑሮ ውድነትን አቀበት ስለመሻገራቸው ወጣቱ ይናገራል፡፡

ለብዙዎች ይህ አነስተኛ እርዳታ ሊመስል ይችላል፤ ለዮሴፍና ለቤተሰቡ ግን የህይወት መቀየሪያ ትልቅ የሞራል ስንቅ ነበር። ስራውን በቁርጠኝነትና በእንክብካቤ የጀመሩት እነዚህ ወጣቶች፣ ገና በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ ውጤት ማየት ጀመሩ። ዶሮዎቹ እንቁላል መጣል ሲጀምሩ ምርቱን ቀጥታ ወደ ገበያ ማቅረብ ያዙ፤ አሁን ኑሮአቸው በእጅጉ ተሻሽሏል፡፡

“የመኖ ዋጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ መጨመሩ በስራችን ላይ የራሱ የሆነ ጫና ማሳደሩ አልቀረም፤ ነገር ግን ጠንክረንና እየተረዳዳን በዓላማ መስራታችን ለስኬት አብቅቶናል፤ የዶሮ እርባታው ዘርፍ የኛንና የቤተሰባችንን ህይወት ሙሉ በሙሉ ቀይሮታል” ይላል ወጣት ዮሴፍ።

ዛሬ ዮሴፍና ቤተሰቡ የምግብ ፍጆታቸውን ከመሸፈን አልፈው እንቁላል ለገበያ በማቅረብ ተጨማሪ ገቢ እያገኙ ነው። የወረዳው የከተማ ግብርና ባለሙያዎች የሚያደርጉላቸው የህክምናና ሙያዊ ድጋፎች ጥንካሬ እንደሆናቸው የሚናገረው ወጣቱ፣ በቀጣይም ባላቸው ክፍት ቦታ ላይ ስራቸውን ይበልጥ ለማስፋፋት ትልቅ እቅድ ሰንቋል።

የዚሁ ወረዳ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ ፅዮን ጀማል ሌላኛዋ በቤተሰብ ደረጃ በሚሰራ የዶሮ እርባታ ስራ ስኬታማ የሆኑ ህያው ምስክር ናቸው። ቀደም ሲል ሙሉ ጊዜያቸውን በቤት እመቤትነት የሚያሳልፉና ምንም አይነት ገቢ የሌላቸው እንደነበሩ ያስታውሳሉ። አሁን ግን ቀናቸው የሚጀምረው በዶሮዎቻቸው ጩኸትና በደስታ በተሞላ እንክብካቤ ነው። ወይዘሮ ፅዮን ዘጠኝ የቤተሰብ አባላትን በማስተባበርና በመደራጀት ከወረዳው ያገኙትን ሶስት የዶሮ ኬጂዎች፣ 150 ዶሮዎች እና የመኖ ድጋፍ ተረክበው ወደ ስራ ገቡ።



ፎቶ- ከገፀ ድር

በቤተሰብ ደረጃ በሚሰራ የዶሮ እርባታ ስራ የተሰማሩ የከተማዋ ነዋሪዎች የምግብ ፍጆታቸውን ከማሟላት አልፈው ተጨማሪ ገቢ እያገኙ ነው

በወረዳው አርሶ አደር እና የከተማ ግብርና ልማት ፅሕፈት ቤት አማካኝነት የተደረገላቸው ይህ የመጀመሪያ ደረጃ ድጋፍ ትልቅ ብርታትና መሠረት እንደሆናቸው የገለፁት ወይዘሮ ፅዮን፣ ይህም አሁን ለደረሱበት የስኬት ደረጃ እንዳበቃቸው ተናግረዋል፡፡ ወይዘሮ ፅዮን፣ ዶሮዎችን መንከባከብ፣ መኖና ውሃ በሰዓቱ መስጠት አሁን ላይ የዕለት ተዕለት አስደሳች ተግባራቸው ሆኗል። ልክ እንደ ዮሴፍ ሁሉ እርሳቸውም የመኖ ዋጋ መናር ዋነኛ እንቅፋት እንደሆነባቸው አልሸሸጉም፡፡ ሆኖም ግን፣ በትጋት መስራት ከተቻለ የከተማ ግብርና የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ አቅም ለመገንባትና ከቤት እመቤትነት ወደ ማህበረሰብ መጋቢነት ለመሸጋገር ትልቅ ድልድይ መሆኑን በተግባር አሳይተዋል።

የአራዳ ክፍለ ከተማ የወረዳ 6 የከተማ ግብርና ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ አሸናፊ ትግስቱ እንደሚገልፁት፣ የቤተሰብ ቢዝነስ በከተማዋ ውስጥ ሰርክ የሚሰማውን “በከተማ የግብርና ስራን መከወን አይቻልም” የሚለውን የተሳሳተ አመለካከት በተግባር የሰበረ ትልቅ ንቅናቄ ነው።

እንደ አቶ አሸናፊ ማብራሪያ፣ በወረዳው ውስጥ የከተማ ግብርና በሁለት መልኩ ይተገበራል፡፡ አንደኛው ለቤተሰብ ፍጆታ ሲሆን በዚህ ስራ ለሚሰማሩ እስከ 5 የሚደርሱ ዶሮዎች የሚሰጡበት። ሁለተኛው በቤተሰብ ደረጃ የሚሰራ የዶሮ እርባታ ስራ ነው፡፡ ይህ ደግሞ 50 ዶሮዎች፣ የዶሮ ኬጂ፣ መኖና ሙያዊ ድጋፍ ተሟልቶ የሚሰጥበት መስክ ነው።

በዚህ በጀት ዓመት ብቻ በወረዳው በሶስት ዙር ለ48 ተጠቃሚዎች ለእያንዳንዳቸው 50 ዶሮዎች መሰራጨታቸውን አቶ አሸናፊ ገልጸዋል።

የዚህ ስራ ትልቁ ስኬት ተጠቃሚዎች ዛሬ ላይ እንቁላል ለመግዛት ወደ ገበያ አለመውጣታቸው ነው፤ ይልቁኑ ምርታቸውን ወደ ውጭ በማውጣት የከተማዋን የኑሮ ውድነት እያረጋጉ ይገኛሉ። ከዚህም ባለፈ፣ በርካታ አባወራዎችና እማወራዎች ከእንቁላል ሽያጭ በሚያገኙት ገቢ የወርሃዊ የልጆች የትምህርት ቤት ክፍያን በአግባቡ መሸፈን መጀመራቸውን በደስታ ይናገራሉ።

በአራዳ ክፍለ ከተማ የአርሶ አደርና የከተማ ግብርና ልማት ጽህፈት ቤት የበሽታ መከላከልና ቁጥጥር ረዳት የእንስሳት ሃኪም አቶ ዳንኤል እውነቴ በበኩላቸው፣ መንግስት ለዚህ ዘርፍ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ያረጋግጣሉ። በክፍለ ከተማው በሚገኙ ስምንት ወረዳዎች ውስጥ በአጠቃላይ 1 ሺህ 274 ነዋሪዎች በቤተሰብ ደረጃ የሚሰራ የዶሮ እርባታ ስራ ተጠቃሚ መሆን ችለዋል።

ስራው ዝም ብሎ የተሰጠ ሳይሆን ባለሙያዎች ቤት ለቤት በመዞርና በኢኮኖሚ ዝቅተኛ የሆኑ ነዋሪዎችን በጥንቃቄ በመለየት የተተገበረ ነው። ተጠቃሚዎቹ ያመረቱትን ምርት በቀላሉ እንዲሸጡ በእሁድ እና በቅዳሜ ገበያና በተለያዩ ባዛሮች ላይ የገበያ ትስስር ተፈጥሮላቸዋል። አልፎ አልፎ በመኖ እጥረትና በአያያዝ ጉድለት ከተስፋ መቁረጥ የተነሳ ከስራው የወጡ ሰዎችን ጭምር ባለሙያዎቹ በማማከርና በመምከር ተስፋ ሰጥተው መልሰው ወደ ማምረቱ መስመር እንዲገቡ እያደረጉ ይገኛሉ።

ይህ በዶሮ እርባታ ላይ የተመሰረተው በቤተሰብ ደረጃ የሚሰራ የዶሮ እርባታ ስራ (የቤተሰብ ቢዝነስ) ስኬት በአንድ ወረዳ ብቻ የተወሰነ አይደለም። የከተማዋን የተለያዩ ክፍለ ከተሞች ስንቃኝ የተመዘገቡት ስኬቶች እጅግ አበረታች ናቸው፡፡ በጉለሌ ክፍለ ከተማ የእንስሳት ሃብት ልማት ቡድን አስተባባሪ አቶ ሞገስ አባይነህ እንደገለጹት፣ በ2017 በጀት ዓመት 1 ሺህ 950 ማህበራት በቤተሰብ ደረጃ የሚሰራ የዶሮ እርባታ ስራ (በቤተሰብ ቢዝነስ) ተሳታፊ ሆነዋል። በ2018 በጀት ዓመት ደግሞ እስካሁን ድረስ እያንዳንዳቸው አምስት አባላት ያሏቸው 300 ማህበራት ወደ ስራ ገብተዋል።

ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ የእንስሳት ሃብት ቡድን መሪ አቶ ሀብታሙ ቃበታ በበኩላቸው፣ በ2018 በጀት ዓመት እስካሁን 342 ነዋሪዎች የ50 ዶሮዎች፣ የ1 ኩንታል መኖና የኬጂ ድጋፍ ተደርጎላቸው ውጤታማ መሆናቸውን ይናገራሉ።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርሶ አደር እና የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የእንስሳት ሃብት ልማት ዳይሬክተር ደጀኔ ጌታቸው (ዶ/ር) እንዳረጋገጡት፣ በዚህ በጀት ዓመት ባለፉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ ብቻ 4 ሺህ 101 አባወራዎችና እማወራዎች በቤተሰብ ደረጃ ወደሚሰራ የዶሮ እርባታ ስራ ገብተዋል። በእያንዳንዱ ውስጥ አምስት የቤተሰብ አባላትን በማካተት በአጠቃላይ 20 ሺህ ግለሰቦች የዘርፉ ተጠቃሚ መሆን ችለዋል።

በቤተሰብ ደረጃ የሚሰራ የዶሮ እርባታ ስራ (የቤተሰብ ቢዝነስ) ከአንድ ተራ የስራ እድል ፈጠራ የዘለለ ጥልቅ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ አለው። የቤተሰብ አባላት በአንድ የጋራ ራዕይና መተማመን ላይ ተመስርተው ሲሰሩ በመካከላቸው ያለው አንድነትና ፍቅር ይበልጥ ይጠነክራል። ደጀኔ ጌታቸው (ዶ/ር) እንደሚገልፁት፣ ብዙዎች መጀመሪያ ከተሰጧቸው 50 ዶሮዎች ተነስተው፣ ውጤታማነቱን እያዩ በራሳቸው አቅም የዶሮ ቁጥራቸውን ከ100 እስከ 600 በማድረስ የኬጂ ቤቶችን አስፋፍተው ሰርተዋል። ይህ የሚያሳየው ስራው ራሱን የመመገብ ብቻ ሳይሆን የካፒታል አቅምን የማሳደግ ትልቅ አቅም እንዳለው ነው።

በቤተሰብ ደረጃ የሚሰራ የዶሮ እርባታ ስራ (የቤተሰብ ቢዝነስ) ስኬታማና ለትውልድ የሚሻገር ይሆን ዘንድ ግን በጥንካሬ መስራት ግድ ይሆናል። እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የስራ ድርሻው በግልጽ ሊታወቅ ይገባል። የገቢና የወጪ ሂሳብ በትክክል መመዝገብ አለበት፤ የቢዝነስ ገንዘብና የቤተሰብ የግል ወጪ መደበላለቅ የለበትም። ጊዜያዊ ጥቅማጥቅም ላይ ከማተኮር ይልቅ ስራውን አሳድጎ ለቀጣይ ትውልድ የማስተላለፍ ግብ መያዝ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

የዮሴፍ፣ የወይዘሮ ፅዮንና የሺዎች አዲስ አበባውያን ስኬት የሚያሳየን አንድ ትልቅ እውነት አለ፡፡ ለመለወጥ ሰፊ መሬትና በሚሊዮኖች የሚቆጠር ካፒታል አይጠይቅም። በጓሯችን ባለው ጠባብ ቦታ፣ በመንግስትና በባለሙያዎች የሚሰጡትን ድጋፎች በአግባቡ ተጠቅሞ በቁርጠኝነት መነሳት ብቻ ነው የሚፈለገው።

የመኖ ዋጋ መጨመርና መሰናክሎች መኖራቸው ባይካድም፣ በጋራ የመስራት ጥንካሬና የከተማ ግብርናው ያለው ከፍተኛ ፍላጎት ማንኛውንም ተግዳሮት ለማሸነፍ ያስችላል። ታዲያ እርስዎና ቤተሰብዎ ምን እየጠበቃችሁ ነው? እጅ ለእጅ ተያይዛችሁ፣ ያላችሁን ውስን ቦታ ወደ ልማት ቀይራችሁ የኑሮ ውድነቱን የምትቋቋሙበትና የቤተሰባችሁን የኢኮኖሚ ሉዓላዊነት የምታረጋግጡበት ጊዜው አሁን አይመስላችሁም?

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# ተፈጥሮን በምርምር የመታደግ ጥረት

**በለይላ መሀመድ**

የምንኖርባት ምድር የሰው ልጆችን ጨምሮ በውስጧ ያሉ ፍጡራን ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ በመጨመሩ ምክንያት ፍላጎትን ለማሟላት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ጫና ውስጥ እየገባች ትገኛለች፡፡ ከጫናዎችም መካከል የብዝሀ ሕይወት መመናመን፣ የካርቦን ልቀት መጨመር፣ ብክለትና ሌሎች አካባቢያዊ ችግሮች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

አዲስ አበባ ከተማ ፈጣን የህዝብ ቁጥር ከሚታይባቸው ከተሞች መካከል አንዷ ናት፡፡ ይህም ለብዝሀ ህይወትና የሥርዓተ ምህዳር መመናመንና መጎሳቆል ተጋላጭ ሆናለች፡፡ የሥርዓተ ምህዳር መመናመንና የብዝሀ ሕይወት መጥፋትን ለመቀነስ የተጎዳውን ሥርዓተ ምህዳር ወደነበረበት መመለስ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡



ፎቶ -ከፋይል

ያጋጠመውን የብዝሃ ህይወት መመናመን በጥናት በማሳየት ከለሙ መካከል የቀበና ወንዝ ዳርቻ አንዱ ነው

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ትኩረት ሰጥቶ ከሚሰራቸው ተግባራት መካከል ሥርዓተ ምህዳርና ብዝሀ ሕይወት እንዲጠበቁ ማድረግ አንዱ ነው፡፡ ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ጋር ቆይታ ያደረጉት በባለስልጣኑ መስሪያ ቤት የሥርዓተ ምህዳርና ብዝሀ ህይወት ዳይሬክቶሬት የጥናትና ምርምር ቡድን መሪ አቶ ሳሙኤል ተስፋዬ እንደተናገሩት፤ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የሥርዓተ ምህዳርና ብዝሀ ሕይወት የስራ ክፍል በማቋቋም በሥነ ምህዳርና ብዝሀ ህይወት መመናመን ላይ ከባለፉት ሶስትና አራት ዓመታት ጀምሮ ጥናትና ምርምር በመስራት መፍትሄ እንዲመጣ እየሠራ ይገኛል፡፡

ክፍሉ ከጥናትና ምርምር በተጨማሪ ጋይድላይን (የአሰራር ስርዓት) ያዘጋጃል። በአዲስ አበባ ከአካባቢ ጋር በተያያዘ የተለያዩ ጉዳቶች አሉ፡፡ በተለያየ ጊዜ የአካባቢ መሸርሸርና የጎርፍ አደጋዎች ይከሰታሉ፡፡ ችግሮቹ እንደ ሀገርም በብዛት ይከሰታሉ፡፡ እነዚህም በሥነ ምህዳር አለፍ ሲልም ለብዝሀ ህይወት መመናመን ምክንያት በመሆናቸው የጥናትና ምርምር ክፍሉ ጥናቶችን በማካሄድ የመፍትሄ ሀሳብ ያስቀምጣል፡፡

የብዝሀ ህይወት እና የሥርዓተ ምህዳር የጥናትና ምርምር ክፍል አምስት የጥናትና ምርምር ተመራማሪዎች ያሉት ሲሆን፤ ባለፉት አራት ዓመታት ስምንት የሚሆኑ ጥናቶችን አካሂዷል፡፡ ለአብነት ያህልም የመዝናኛ ስፍራዎች አያያዝ ዙሪያ፣ የአረንጓዴ አሻራ ምን ውጤት እንዳመጣ እና መንገድ ዳር የሚተከሉ ችግኞች ምን ዓይነት መሆን አለባቸው፣ እንዲሁም የአዲስ አበባ የወንዝ ብክለት መንስኤና እንዴት መስተካከል እንደሚችሉና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ ከአፈር፣ እጽዋትና ከውሀ ናሙናዎችን በመውሰድ በ2017 ዓ.ም ጥናት ተደርጓል።

በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በምርምር ዘርፍ ላይ ከፍተኛ ተመራማሪ የሆኑት መህሪ ማርዬ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በምርምር ዘርፉ ላይ በርካታ ስራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን ይናገራሉ፡፡ ምርምሮቹ ሳይንሳዊ ጥናቶችን የሚከተሉ በመሆኑ አዳዲስ እውቀቶችን ለማግኘት እና ሁለተኛ እውነታዎችን በማረጋገጥና ለችግሮች መፍትሄዎችን ለማስቀመጥ ጠቀሜታቸው ከፍተኛ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

መህሪ ማርዬ (ዶ/ር) ገለጻ፤ የተሰሩት የጥናትና ምርምር ስራዎች ለሚመለከታቸው አካላት ተሰራጭተዋል። ጥናቱም የሥርዓተ ምህዳር ጉዳቱን ስለሚያሳይ “የጉዳቱ መጠን ምን ይመስላል?” ለሚለው ተመራማሪው መህሪ (ዶ/ር) በሰጡት ምላሽ፤ ሥርዓተ ምህዳር ላይ እየደረሰ ያለው፤ በተለይም ከብክለት ጋር ተያይዞ በአዲስ አበባ ወንዞች ላይ በ2017 ዓ.ም የተሰራው ጥናት እንደሚያሳየው በወንዞች ውስጥ የሚገኝ ብዝሀ ህይወት አለ፡፡ ጥናቱ የሚያሳየው አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ 76 ወንዞች ያሉ ሲሆን በተለይም በስድስቱ ዋና ዋና ወንዞች ላይ በደንብ ለማየት ተሞክሯል፡፡

ለምሳሌ ቀጨኔ፣ ቀበና፣ ትንሹና ትልቁ አቃቂ፣ ቡልቡላ፣ ቁርጥሜ ወንዞች ላይ ጥናቱ የተካሄደ ሲሆን ናሙናዎቹን በታችኛው፣ በመካከለኛውና በላይኛው ተፋሰስ በመውሰድ የብክለት መጠኑ ምን ይመስላል? የሚለውን የመለየት ስራ ተሰርቷል፡፡ በውሀና በአፈር ውስጥ ያለውን ብዝሀ ሕይወት በላቦራቶሪ መታየታቸውንና ወንዞች ከብክለት አልፈው በጣም የተበከሉ እንደሆኑና ቀደም ሲል ወንዞቹ ከመበከላቸው በፊት ወንዞቹ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ አሳዎችና እንቁራሪት ውሀው በመበከሉ ምክንያት መጥፋታቸውን እንደሚያሳይ መህሪ (ዶ/ር) ያስረዳሉ፡፡

ቡድን መሪው አቶ ሳሙኤል እንደሚገልፁት ብዝሀ ህይወት ሲባል የተለያዩ ህይወት ያላቸው ነገሮች ያላቸው ትስስር ነው፡፡ ስለሆነም ብዝሀ ሕይወት ሲጠበቅ ወይም እንዲያገግም ሲደረግ ለምሳሌ የወንዞች መጠበቅ ወንዝ ውስጥ የሚኖሩ እንደ አሳና መሰል ህይወት ያላቸው ነገሮች ይጠበቃሉ፡፡ ንጽህናው በተጠበቀ ወንዝ የሚመረቱ የጓሮ አትክልቶችን ማህበረሰቡ ሲመገብ የህብረተሰቡ ጤና የተጠበቀ ይሆናል፡፡

## ጥናቶችን ወደ መሬት ለማውረድ ምን እየተሰራ ነው?

ተመራማሪው መህሪ (ዶ/ር) እንደሚገለፁት በጥናት ቡድኑ ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ በየጊዜው የተዘጋጁት ጋይድላይኖችና ጥናቶች በ11ዱ ክፍለ ከተሞች በሚገኙ የአካባቢ ጥበቃ ጽህፈት ቤቶች እና የሚመለከታቸው ቢሮዎች እንደ ከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ ፓርኮች ኮርፖሬሽን ተግባራዊ እንዲሆኑ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ በአዲስ አበባ የፓርኮች አያያዝ ላይ ጥናት የተደረገ ሲሆን ጥናቱም ተግባር ላይ እንዲውል የፓርክ ኃላፊዎች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በተገኙበት የጥናቱን ውጤት የአዲስ አበባ የህዝብ መዝናኛ ቦታዎች አስተዳደር ኮርፖሬሽን እንዲሰጥ በ2015 ዓ.ም ተደርጓል፡፡

በገባር ወንዞች ላይ በዋናነት በቀበናና ቀጨኔ የተሰራው ጥናትም ተግባራዊ በመደረጉ በአሁኑ ወቅት ወንዞቹ እየለሙ ይገኛሉ፡፡ በተለይም ላይኛው ተፋሰስ ላይ የሚገኙ ወንዞችን በደንብ ማጽዳት ካልተቻለ የሚሰሩ ስራዎች ቀጣይነት ስለማይኖራቸው አሁን ላይ በትኩረት እየተሰራ ነው፡፡

> **ባለፉት አራት ዓመታት ስምንት የሚሆኑ ጥናቶችን አካሂዷል። ለአብነት ያህልም የመዝናኛ ስፍራዎች አያያዝ ዙሪያ፣ የአረንጓዴ አሻራ ምን ውጤት እንዳመጣ እና መንገድ ዳር የሚተከሉ ችግኞች ምን ዓይነት መሆን አለባቸው፣ እንዲሁም የአዲስ አበባ የወንዝ ብክለት መንስኤና እንዴት መስተካከል እንደሚችሉና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ ከአፈር፣ እጽዋትና ከውሀ ናሙናዎችን በመውሰድ በ2017 ዓ.ም ጥናት ተደርጓል**

ቡድን መሪው አቶ ሳሙኤል በበኩላቸው ጥናቶች ሲጠኑ በአንድ ጊዜ ለውጥ ያመጣሉ ብቻ ተብሎ ሳይሆን ለውሳኔ ሰጪዎች እና ለህግ አውጪዎች በግብዓትነት ይውላሉ ተብሎ ይታሰባል። በወንዞች ላይ የተደረገው ጥናት ግን ለውጥ እያሳየ ነው፡፡ ወንዞች በጣም ብክለት ሲያጋጥማቸው ሥነ ምህዳር እና ብዝሀ ሕይወት ላይ የሚፈጥረውን አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳየት በመቻሉ አሁን ላይ ወንዞች ላይ እየተካሄደ ባለው ልማት ለውጥ እየታየ ነው፡፡

### መውጫ

ጥናቶች ለውጥ ስለሚያመጡ አካባቢ ላይ የሚሰሩ ስራዎች ጥናት ላይ መሰረት ያደረጉ መሆን ይኖርባቸዋል ይላሉ ቡድን መሪው አቶ ሳሙኤል፡፡ ከባለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ በወንዝ ዳርቻ ልማት እና በኮሪደር ልማት የመጣው ለውጥ አንዱ የትንተና ውጤት በመሆኑ ማስቀጠል እንዲሁም የጥናትና ምርምር ውጤቶችን ወደ እቅድና ፖሊሲ መለወጥ ያስፈልጋል።

ተመራማሪው መህሪ (ዶ/ር) ጥናቶች ሲጠኑ ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ መሆን አለባቸው፡፡ ሌላው በከተማዋ ላይ የሚሰሩ ጥናቶች ለውጥ እንዲያመጡ ከተፈለገ በየተቋሙ የጥናት ባለሙያዎችንና ተመራማሪዎችን አቅም ማሳደግ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል። በጥናት ለውጥ እንዲመጣ አመራሩም መጣር አለበት፡፡ አሁን ላይ ለውጦች እየመጡ ያሉት ጥናቶች ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ በመሰራታቸው እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

የሰው ልጅም የሚኖርባት ምድር እንዳትራቆት በመጠበቅና በመንከባብ የተፈጥሮ ሀብት መመናመን እንዳያጋጥመው የድርሻውን መወጣት ይኖርበታል፡፡ ተፈጥሮ ሲጠበቅ የሰው ልጅ ሰላምና ጤናው ይጠበቃል፡፡ የሰው ልጅ አካባቢውን ሲንከባከብ አካባቢዋ ራሷ ትንከባከበዋለች፡፡ አካባቢን መጠብቅ የመንግስት ወይም የአንድ አካል ሳይሆን የሁሉም ድርሻና ኃላፊነት መሆኑን መረዳት እንደሚገባ መህሪ (ዶ/ር) ይመክራሉ፡፡

ስለሆነም ዛፍ ሲቆረጥ መልሶ በመትከል፣ ወንዝ እንዳይበከል፣ የውሃ ውስጥ ሥነ ምህዳር እንዲጠበቅ ሁሉም የበኩሉን ሚና መወጣት ይኖርበታል፡፡ ፋብሪካዎችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ወንዝን እንደቆሻሻ ማስወገጃ ሳይሆን እንደ ሀብት መጠበቅ አለባቸው፡፡

## የከተማዋ ... ከገጽ 4 የዞረ

ይህ የመዝናኛ አማራጮችን የማስፋፋት ስራ በአዳዲስ ግንባታዎች ላይ ብቻ የተገደበ አይደለም፤ ይልቁንም በነዋሪዎቿ ልብ ውስጥ ትልቅ ቦታ ያላቸውን ቀደምት ታሪካዊ ስፍራዎችም ያካተተ ነው። በዚህ መሰረትም እንደ ብሔረ ፅጌ፣ ሐምሌ 19፣ አምባሳደር እና የጉለሌ እፅዋት ማዕከል ያሉ አንጋፋ የመዝናኛ ስፍራዎች የነበራቸውን ታሪካዊ ገፅታ ሳይለቁ፣ በዘመናዊ መልክና በላቀ ውበት ታድሰው ለአገልግሎት ክፍት መደረጋቸው የከተማዋን ውበት በእጥፍ አሳድጎታል። ይህም የቀደመውን አዲሱን ትውልድ የሚያገናኝ ውብ ድልድይ ፈጥሯል።

የባህል፣ የሰላምና ኪነ ጥበብ ተመራማሪው ወሰን ባዩ (ዶ/ር) በመዲናዋ እየተገነቡ ያሉ የመዝናኛ ሥፍራዎች፣ ውብ የመኖሪያ መንደሮች፣ ቴአትርና ሲኒማ ቤቶች ትልቅ ሃገራዊ ፋይዳ እንዳላቸው ከዚህ ቀደም ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት ተናግረዋል። የአንድ ሃገር ኪነ ጥበባዊ ሥራዎች እንዲያድጉ ሲኒማ ቤቶችና የጥበብ መከወኛ ሥፍራዎች ቁልፍ ናቸው ያሉት ተመራማሪው፣ የኪነ ጥበብ ዕድገት ደግሞ በተዘዋዋሪ መንገድ የእሴት መጎልበትን ይፈጥራል ብለዋል። የጥበብ ሥራዎችና ባህል ተያያዥ መሆናቸውን ያብራሩት ወሰን ባዩ (ዶ/ር)፣ የትውልዱን ሰብዕና በመቅረጽና በባህሉ የሚኮራ ዜጋ ለማፍራት መሰል የጥበብና የመዝናኛ ሥፍራዎች ግንባታ ጉልህ ሚና እንደሚጫወቱ አንስተዋል። እንዲሁም አዲሱ ትውልድ ጥበባዊ ሥራዎች እንዲወድድ፣ የፈጠራ ሥራዎችን እንዲያደንቅና ሃገራዊ እሴቶቹን እንዲገነዘብ የተገነቡት ቴአትር ቤቶችና የጥበብ ስፍራዎች አስፈላጊ እንደሆኑም ተናግረዋል፡፡

ለበርካታ ዓመታት የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ከስራና ከውጥረት በኋላ ዘና የሚሉባቸው፣ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ጥራት ያለው ጊዜ የሚያሳልፉባቸው ክፍትና ሰፊ የህዝብ መዝናኛ ስፍራዎች (Open-air spaces) እጥረት በከፍተኛ ደረጃ ነበረባቸው። አብዛኛው የማህበራዊ መስተጋብር በተዘጋጁ ካፌዎች፣ ሬስቶራንቶች ወይም ሲኒማ ቤቶች ላይ ብቻ የተገደበ በመሆኑ፣ ነዋሪው ከተፈጥሮ ጋር የሚገናኝበት አካላዊና አዕምሯዊ እረፍት የሚያገኝበት እድል ጠቦ ቆይቷል። አሁን ግን የተገነቡት ዘመናዊ ፓርኮች ይህንን ክፍተት በሰፊው በመሙላት የሰዎችን የእለት ተእለት የህይወት ዘይቤ ሙሉ በሙሉ እየቀየሩት ይገኛሉ።

በተጨማሪም እነዚህ ስፍራዎች የተለያየ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዳራ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ያለምንም ልዩነት የሚገናኙባቸውና እርስ በርስ የሚቀራረቡባቸው ጠንካራ የማህበራዊ ድልድይ ሆነው እያገለገሉ ነው። ሰዎች በፓርኮች ውስጥ እየተገናኙ ሐሳብ ይለዋወጣሉ፣ አዳዲስ ጓደኝነቶችን ይመሰርታሉ፣ እንዲሁም የጋራ ሰላምና አንድነትን ያጠናክራሉ። በመሆኑም ፓርኮቹ የውበት ምንጭ ብቻ ሳይሆኑ፣ ጤናማ ማህበረሰብን ለመገንባትና የከተማ ነዋሪውን የሥነ-ልቦና ደህንነት ለመጠበቅ የሚጫወቱት ሚና የማይተካ ነው።

እነዚህ ፓርኮች የአገሪቱን ባህል፣ ታሪክና ጥበብ በሚያንጸባርቅ መልኩ የተቀረጹ በመሆናቸው ለቱሪስቶች ልዩ መስህብ መሆን ችለዋል። ጎብኚዎች በፓርኮቹ ውስጥ በሚንሸራሸሩበት ወቅት የከተማዋን ዘመናዊነት እያደነቁ፣ የአካባቢውን ሰላማዊ ድባብ የመለማመድ እድል ያገኛሉ። ይህ የቱሪስቶች ፍሰት መጨመር ደግሞ ለአገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ግኝትና ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው እድገት አዲስ ብርሃን ፈጥሯል።

ከመሰል የሕዝብ መዝናኛ ፓርኮች በተጨማሪ የኑሮ ውድነትን ለማቃለል፣ ምርት በብዛት ማቅረቢያ እና የግብይት ማዕከላት አካል የሆነውን ሰባተኛውን የለሚ ሁለገብ የገበያ ማዕከል ከሰሞኑ ለአገልግሎት ክፍት ተደርጓል፡፡ ገበያ ማዕከሉ የኑሮ ውድነትን የሚያቃልሉ ዘመናዊ ማሞቂያ እና ማቀዝቀዣ ያላቸው 221 መጋዘኖች፣ የችርቻሮ ሱቆች፣ ሱፐር ማርኬቶች፣ ወፍጮ ቤቶች፣ በአንድ ጊዜ 250 ተሽከርካሪዎችን ማቆም የሚችል ፓርኪንግ፤ ለለሚ ኩራ፣ ለቦሌ እና የካ ክፍለ ከተሞች ውስጥ የሚገኙ ነዋሪዎች አማካይ ቦታ በሆነው ሰሚት ዋና መንገድ ላይ የሚገኝ ምቹ የሆነ ሁለገብ የገበያ ማዕከልን በውስጡ ይዟል።

በከተማዋ የተሰሩ አካታች የልማት ፕሮጀክቶች የሕዝቡን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት እያረጋገጡ ይገኛሉ ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ ተናገረዋል፡፡ በልማት ፕሮጀክቶቹ ከተሰሩት ስራዎችም በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ “ገብስ ተራ” ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በሚገኘው ቁጥር 3 የበጎነት መንደር የተገነባው 44 የመኖሪያ ቤቶች እና ሱቆች ያሉት ባለ አምስት ወለል ህንጻም ባሳለፍነው ሳምንት ለተጠቃሚዎች የተላለፈ ሲሆን ይህም ትልቅ ሰው ተኮር ተግባር ነው፡፡ ገብስ ተራ ቀደም ብሎ እጅግ የተጎሳቆለ፣ ለመኖር ምቹ ያልሆነ፣ ባረጁ እና በደቀቁ ቤቶች የተሞላ፣ በተደጋጋሚ በእሳት አደጋ የሚጠቃ፣ ለአቅመ ደካማ እናቶች የማብሰያና የመጸዳጃ አገልግሎት አስቸጋሪ የነበረበት መንደር እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ። አሁን ላይ በአጠቃላይ 377 የመኖሪያ ቤቶች ያላቸው 5 ህንጻዎችን በመገንባት ነዋሪዎቹንም ከዛ አስከፊ አኗኗር ተላቅቀው፤ ክብራቸውን በሚመጥን ፅዱ፣ ዘመናዊ አኗኗር የሚፈጥር፣ ልጆች ቦርቀዉ የሚጫወቱበት እና ደረጃውን በጠበቀ መኖሪያ መንደር እንዲኖሩ መደረጉን ከንቲባ አዳነች አቤቤ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባጋሩት መልዕክት ገልጸዋል፡፡

## የአረፋ ... ከገጽ 8 የዞረ

እጅን መዘርጋትና ደግነትን ማሳየት ከፍላጎት በላይ የሆነ ኃይማኖታዊና ግብረገባዊ ግዴታ መሆኑን በአጽንኦት ይገልጻሉ። ይህ የመረዳዳት እሴት ከግለሰብ አልፎ ማህበረሰባዊ ትስስርን የሚያጠናክር በመሆኑ፣ በዓሉን ስናከብር የተቸገሩትን በማሰብና ለጋራ ሰላምና አንድነት በጋራ በመቆም ሊሆን እንደሚገባ ምሁራዊ ምክራቸውን ይለግሳሉ።

ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል ከበዓሉ ጋር በማስተሳሰር ከገለጹት አንዱ ጉዳይ፣ እንደ ወደብና ቀይ ባህር ያሉ ስትራቴጂካዊ የሀገር ጥቅሞችን በዘላቂነት ለማስከበር በሚደረጉ ሰላማዊ እንቅስቃሴዎች ላይ በጋራ መቆም ከህልውና ጋር የተያያዘ ነው የሚለው ሃሳብ ነው፡፡ ግብጾች በናይል ጉዳይ ያላቸውን የማይናወጥ አንድነት እንደ ምሳሌ በመጥቀስ፣ “እኛም እንደ ሀገር በባህር በር ጥያቄ ላይ ተመሳሳይ የጋራ አቋም ሊኖረን ይገባል” በማለት አስገንዝበዋል፡፡ ይህን ብሔራዊ ግብ ለማሳካት ደግሞ በአረፋ በዓል ወቅት የሚታየውን የግል ፍላጎትን ለላቀ ዓላማ የመሰዋት እሴት በተግባር ማዋል አስፈላጊ መሆኑን አክለዋል።

ዜጎች በፖለቲካዊ አመለካከታቸው የመለያየት መብት ቢኖራቸውም፣ እንደ ወደብ ባሉ የትውልድ ዕጣ ፈንታን በሚወስኑ ጉዳዮች ላይ ግን አንድ ልብ ሆነው ሊደማመጡ እንደሚገባ ነው ምሁሩ የሚገልጹት፡፡ በኃይማኖታዊ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ የሚታየው የአንድነትና የጋራ መደማመጥ፣ ወደ ሀገራዊ ስትራቴጂካዊ ጥያቄዎች ሲመጣም የማይታለፉ የሚመስሉ መሰናክሎችን ለማለፍና የሀገርን ጥቅም ለማስከበር ትልቁ መሣሪያ ነው ብለዋል።

በአጠቃላይ፣ ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል ያጋሩን ሃሳብ እንደሚያመለክተው፣ የአረፋ በዓል ከመንፈሳዊ ይዘቱ ባለፈ ለሀገር ግንባታና ለብሔራዊ አንድነት የሚረዱ ስንቅ የሆኑ እሴቶችን በውስጡ መያዙን ነው። በበዓሉ ላይ የሚታየው እኩልነት፣ የግል ጥቅምን ለላቀ ዓላማ የመሠዋት ልምድና የይቅርታ ባህል፣ እንደ ሀገርም ልንጠቀማቸው እንደሚገባ ነው ምሁሩ በአጽንኦት የገለጹት። በተለይም እንደ ባህር በር ያሉ ስትራቴጂካዊ ጥቅሞችን ለማስከበር በዓሉ የሚያስተምረውን በጋራ ሀገራዊ ጉዳይ ላይ አንድነት መፍጠር እና የመደማመጥ እሴት ወደ ብሔራዊ አንድነት ማምጣት ይገባል። በመሆኑም፣ የአረፋን በዓል ስናከብር እነዚህን የቆዩ የሰላም፣ የርህራሄና የጽናት እሴቶች ከተግባራዊ ሀገራዊ ፍላጎቶቻችን ጋር በማስተሳሰር ለተሻለችና አንድነቷ ለጸና ኢትዮጵያ መሠረት ልናደርጋቸው እንደሚገባ ነው ምሁሩ ያስገነዘቡት።

## ለትውልድ... ከገጽ 10 የዞረ

አገልግሎት ማሻሻያዎች አሁን ላሉበት ደረጃ የደረሱት የጊዜን አጠቃቀም ቀመር በመቀየር ነው። ቀደም ሲል በአምስት እና በስድስት ዓመታት ይከናወኑ የነበሩ ግዙፍ የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች አሁን ላይ በሰባት እና ስምንት ወራት ውስጥ ተጠናቀው ለአገልግሎት እየበቁ ነው። ይህ ሊሆን የቻለው የጊዜ ብክነትን በማስቀረት፣ በፈረቃ (Shift system) ሳምንቱን ሙሉ 24 ሰዓት የሰው ኃይልና ማሽነሪዎች በተቀናጀ ሁኔታ በመሰማራታቸው ነው።

ሥራን በጊዜ አለመወሰን ወይም ሥራን ቀን በጸሐይ ብቻ የማይከናወን “ኋላቀር ልማድ” በእንቅልፍ አልባዋ አዲስ አበባ ተሸንፏል ማለት ይቻላል። ቀንና ሌሊትን ለሥራ የማዋልን ባህል ቀድሞ በመተግበር የመዲናዋን ጎዳናዎች፣ ዓደባባዮች፣ ፓርኮችና ግዙፍ የልማት ፕሮጀክቶች በማጽዳት ሥራ ላይ የተሰማሩ ሙያተኞች ይጠቀሳሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ አስተያየት የሰጠችን የጽዳት ሠራተኛዋ ወይዘሮ አልማዝ በቀለ፤ “አዲስ አበባን ለመቀየር ሁሉም ሰው የድርሻውን መክፈል አለበት። እኛ ሌሊት የምናጸዳው ከተማዋ ጠዋት ለዕለታዊ ኑሮ ዝግጁ እንድትሆን ነው። ሰዓታችንን ሰጥተን ከተማችንን ማሳመር ትልቅ እርካታ አለው” ትላለች።

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሃብት ምሁር የሆኑት ተስፋዬ ጮፋና (ዶ/ር)፣ አዲስ አበባ የጀመረችውን የ24 ሰዓት የሥራ ባህል ከዓለም አቀፍ ተሞክሮ ጋር አያይዘው እንዲህ ሲሉ ይተነትኑታል፡-“እንደ ለንደን፣ ኒውዮርክ እና ሲንጋፖር ያሉ የዓለም ታላላቅ ከተሞች የኢኮኖሚ መዋቅራቸው የተገነባው ‘Night-time Economy’ ወይም በሌሊት ኢኮኖሚ ላይ ነው። አዲስ አበባ አሁን ወደዚህ ሥርዓት እየገባች ነው። 24 ሰዓት መሥራት ማለት የከተማዋን ምርታማነት በሦስት እጥፍ ማሳደግ ማለት ነው። ይህ ደግሞ በባዶ ሜዳ የመጣ ሳይሆን፣ የሠራተኛው፣ የአመራሩና የባለሙያው ‘የጊዜና የጉልበት’ መስዋዕትነት ውጤት ነው።”

ምሁሩ አክለውም፣ ይህ ዓይነቱ የሥራ ባህል ከተማዋን ለነዋሪዎቿ ምቹ ከማድረግ ባለፈ፣ የቱሪስትና የኢንቨስትመንት ፍሰቱን በማሳደግ ረገድ የላቀ ሚና እንዳለው ያስረዳሉ።

ለሰው ልጅ ከተሰጡ ውድ ጸጋዎች መካከል አንዱ የሆነው “ጊዜን” በአግባቡ መጠቀምን ይህ ትውልድ ለአገር እና ለትውልድ የሚያቀርበው መስዋዕት ሊሆን እንደሚገባ ዑስታዝ ሙሐመድ ፈረጅ ባስተላለፉት መልዕክት ፅሑፋችን እንቋጭ። “የጊዜ ባለቤት የሆነው አላህ(ፈጣሪ) ጊዜን ለበጎ ተግባር እንድንጠቀመው ነውና የሰጠን፤ ይህንን ስናደርግ ከእርሱ ዘንድ ዋጋ ያስገኝልናል፡፡ ለአገር እና ለትውልድ ዕድገት የምንችለውን ሁሉ በተሰጠን ጊዜ ውስጥ ማድረግ ግዴታ ነው፡፡ መለወጥ በማንችለው ሁኔታ ምክንያት ማድረግ የምንችለውን አለማድረግ ተገቢነትም ተቀባይነትም የለውም። ልማትን የምናለማው ራሳችንን ብቻ በማሰብ መሆን የለበትም፡፡ በልማቱ እኛ ልንጠቀም እንችላለን፣ እኛ ባንጠቀም እንኳን ልጆቻችን፣ የልጅ ልጆቻችን፣ የሰው ዘር እንዲሁም እንስሳትና አራዊት ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ዛሬ ያለንን ጊዜ ተጠቅመን የምናለማው ልማት ለሰፊ ጥቅም እንደሚውል በማመን መሆን አለበት፡፡”

## ነብዩ ... ከገጽ 14 የዞረ

ከእነዚህ ቀለማት መካከል ጥቁር ቀለም አንዱ ሲሆን፣ በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ ሰፊ ስፍራና የተለየ ትርጓሜ የሚሰጠው ቀለም ነው። በአንዳንድ ባህሎች ውስጥ ጥቁር ቀለም ከሀዘን ወይም ከክፉ ነገር ጋር ብቻ ተያይዞ ቢታይም፣ በእስልምና አስተምህሮ ግን ከፍ ያለ ክብርና ውበትን የሚወክልበት በርካታ አውዶች አሉ።

ነብዩ መሐመድ በተለያዩ ሁኔታዎች ጥቁር ቀለማት ያላቸውን አልባሳት ለብሰዋል፡፡ ለአብነትም ጥቁር ጥምጣም ይለብሱ እንደነበር በሐዲስ ተዘግቧል። ጥቁር ሰንደቅ ዓላማ (መለያ ምልክትም) ተጠቅመዋል፡፡ ምክንያቱም ጥቁር የክብር፣ የቁም ነገርና የልግስና ምልክት ነው ይላሉ ኡስታዝ ፉአድ።

በአጠቃላይ በእስልምና ከፍ ያለ ቦታ የተሰጣቸው ቀለማት ከላይ የተጠቀሱት ናቸው፡፡ በእስልምና ኃይማኖት ውስጥ በተለየ ሁኔታ የሚወደዱ ቀለማት ቢኖሩም “የማይፈቀድ” ተብሎ የተበየነ ወይም የተፈረጀ ቀለም የለም፡፡ ምክንያቱም ቀለማት በሙሉ የአላህ (ፈጣሪ) የፍጥረት ውበት መገለጫዎች ናቸው ተብሎ ስለሚታመን ነው።

# የቅጥር ማስታወቂያ

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከዚህ በታች በተገለፁት ክፍት የስራ መደቦች ላይ አመልካቾችን አወዳድሮ ለመቅጠር ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ደረጃ | ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ | አግባብ ያለው የሥራ ልምድ | የሙያ ዓይነት | መደብ መታወቂያ ቁጥር | ብዛት | የቅጥር ሁኔት | ደመወዝ | የሥራ ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **የዲጂታል ሚዲያና ህትመት ዘርፍ** | | | | | | | | | | |
| 1 | ኤክስክዩቲቭ ሴክሬታሪ | VI | ኮሌጅ ዲፕሎማ/ ቢ.ኤ ዲግሪ | 4/2 ዓመት | በሴክሬታሪያል ሳይንስ እና ኦፊስ ማናጅመንት ወይም በተዛማጅ የትምህርት መስክ | ከ/18.249 | 1 | በቋሚነት | በተቋሙ ስኬል መሰረት | አ/አ |

1. አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10/አስር/ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የትምህርት ማስረጃችሁን ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ በመያዝ በተቋሙ የሰው ኃብት ስራ አመራር እና ልማት ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 05 ድረስ በመምጣት እንድትመዘገቡ እናሳስባለን፡፡
2. ከግል ድርጅቶች የሚቀርብ የስራ ልምድ ማስረጃ የስራ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ማስረጃ ማምጣት ይኖርባቸዋል፡፡
3. የስራ ልምድ የሚጠይቀው ከወጣው ክፍት መደብ ጋር ቀጥተኛ መሆን አለበት፡፡
4. በቴክኒክና ሙያ/ሌቬል የሚወዳደሩ የብቃት ማረጋገጫ/COC ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. የምዝገባው ቀን ከግንቦት 17 ቀን 2018 ዓ.ም እስከ ግንቦት 30 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ
6. የፈተና ቀን በውስጥ ማስታወቂያ ይገለፃል፡፡
7. ለበለጠ መረጃ አድራሻ አምስት /5/ ኪሎ ቅድስት ማርያም ፊት ለፊት ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጐን ስልክ 0111551848

**አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ**

---

**የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ**

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ወረዳ 09 በሜማ ኢንጅነሪንግ ሶሉዩሽን ኃ/የተ/የግ/ማ ስም የተመዘገበ ይዞታ የይዞታው ልዩ መለያ ቁጥር AA000050903015 የተሰጠበት ቀን 02/07/2011 ዓ.ም የሆነ የመብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደጠፋባቸው በቁጥር የካፓ/ለ/ቁ/15/12719 በቀን 20/08/2018 ዓ.ም የሚገልፅ መረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡ ይህም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም መብት አለኝ የሚል በ90 ቀናት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ምትክ ሰርተፍኬት የሚሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ/ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ቢኒያም ረጋሳ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 08 የይዞታ ልዩ መለያ ኮዱ AA000060804612 ሴሪ ቁጥር 049183 የሆነው ይዞታ እና በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 01 በዋህደ በላይ አብተው የተመዘገበ ቤት -- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ክልል ውስጥ በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000070109626 በሴሪ ቁጥር L -094132 የተመዘገበው የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጁ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በእነ 1.አረዳ ነሜ ቀሬ 2.ታሪኳ አረዳ ነሜ 3.አመለወርቅ አረዳ ነሜ ስም የተመዘገበ ይዞታ ወረዳ 07 የይዞታ መለያ AA000090712118 የሆነ ካርታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) በቃጠሎ ወቅት ቤቱ ውስጥ የነበረው ዲጂታል ካርታ የተቃጠለ መሆኑን 28/8/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በፓየስ ኢንተርናሽናል ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ስም በአ/አ ከተማ አስተዳደር ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 4 ሳይት አያት 2 ሳይት 4 ብሎክ 40 የቤት ቁጥር BA2S4/8-040/SN/103 የሚገኘው ኮንደሚኒየም የይዞታ መለያ ቁጥር AA000061007507400103 የሴሪ ቁጥር C 0303820 የሆነ ኮንደሚኒየም ማህደር በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30/ሰላሳ/ ቀን ድረስ ፅ/ቤታችን ቀርበው እንዲያሳውቁ ካላቀረቡ በምትኩ ሌላ ማህደር ተደራጅቶ ሰርተፍኬት የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ እየሱስ ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር የካ/217200/11 የሴሪ ቁጥር 0669765 ወረዳ 13 የቦታው ስፋት 502 ሜ.ካ በእኛ ተቋም የተሰጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ይሁንና የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ እየሱስ ስም የተመዘገበ የካርታ ቁጥር የካ/217200/11 የሴሪ ቁጥር 0669765 ወረዳ 13 የቦታው ስፋት 502 ሜ.ካ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የጠፋ ስለሆነ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፣ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ለሚመጣው ሀለፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አለሚቱ ወንድሙ ታችበሌ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000060103957 ሴሪ ቁጥር R 0186446 የሆነው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ /የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

# ማስታወቂያ

በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 በቤት ቁጥር 9999/1 በካርታ ቁጥር 5/4/390820/02 በወ/ሮ እመቤት አረጋ አደም ስም የተመዘገበው በእጃቸው መገኘት የነበረበት ዋና ካርታ የጠፋ በመሆኑ ይህንኑ አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም መቃወሚያ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በህይወት ተስፋዬ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ቦሌ4/50/1/1/10594/00 የተሰጠበት ቀን 05/06/2004 ዓ.ም የቦታው ስፋት 94 ሜ.ካ የቦታው አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነው ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ እንዲጻፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ወረዳ 10 የሆነው መኖሪያ ቤት በህይወት ተስፋዬ ስም የተመዘገበ በካርታ ቁጥር ቦሌ4/50/1/1/10594/00 የተሰጠበት ቀን 05/06/2004 ዓ.ም የቦታው ስፋት 94 ሜ.ካ የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ኦርጅናል የጠፋ ስለሆነ ይዞታውን (ቤቱን) በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኋላ ካርታውን የምናዘጋጅ መሆኑን እየገለፅን የማስታወቂያው ወጪ በባለጉዳይ የሚሸፈን መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

አመልካች ሜስሮብ ኬቮርክ ሣርኪሲያን በቀን 14/08/2018 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በራሳቸው ስም የተመዘገበ በበሻሌ 40/60 የጋራ መኖሪያ ቤት የካርታ ቁጥር ቦሌ15/54/6/6/43446/00 የሴሪ ቁጥር 1492052 የቤት ቁጥር BESH-B46HN/702 የቤቱ ስፋት 104.65 የቤቱ አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነ ኦርጅናል ካርታ የጠፋብኝ በመሆኑ ይሄው ተገልፆ ለሚመለከተው አካል ምትክ እንዳገኝ ደብዳቤ ይፃፍልኝ በማለት በማመልከቻ ያሳወቁን ስለሆነ ይዞታን ወይም ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለቅ/ጽ/ቤታችን እንዲያሳውቁን እያልን በጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኃላ ኃላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ቦሌ8/73/2/4/24174/00 ሴሪ ቁጥር 066727 በአቶ ደምሴ ምርደቶ ሐሚድ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ይዞታ እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 25 ቀበሌ 03 በአሁኑ ወረዳ 12 ቤት ቁጥር -- ለሆነው ቤት በካርታ ቁጥር ወ13/ውዝ01/321/10749 በሴሪ ቁጥር 0642789 በቀን 24/04/2010 በወ/ሮ ዘውድነሽ ሀይሉ ወርቁ ስም የተመዘገበ የነባር ይዞታ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ካርታው በመጥፋቱ ምክንያት የካርታ ኮፒ አገልግሎት የተጠየቀ ሲሆን አገልግሎቱን ለመስጠት በሙብት ፈጠራ እና የይዞታ አገልግሎት አሰጣጥ ደንብ ቁጥር 163/2016 አንቀጽ 23 መሰረት የባለይዞታው የተነፃፃሪ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ወይም ሰነድ መጥፋቱ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ማስታወቂያ ወጥቶ በሰላሳ(30) ቀናት ውስጥ ተቃዋሚ ካልቀረበ አገልግሎቱን መስጠት እንደሚቻል ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ስለሆነም ካርታውን ይዤዋለው የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ መሬት ልማት እና አስተዳደር ቢሮ አ/ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት ይዞ እንዲቀርብ እያሳሰብን ይህ ካልሆነ ግን በደንቡ እና በአሰራሩ መሰረት የጠፋውን ካርታ አምክነን በምትኩ ሌላ የተነፃፃሪ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአዲስ ከተማ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የካርታ ቁጥር 003/10493/00/10512 በሴሪ ቁጥር 010115 በመኮንን አስፋሃ ገ/ስላሴ ስም ያለውን ይዞታ አስመልክቶ ይህን ይዞታ በእዳ፣ በዋስትና ወይም በሌላ ይዤዋለሁ የሚል ተቋምም ሆነ ግለሰብ ወይም ይዞታው ላይ የይገባኛል ጥያቄ ያለው አካል ካለ በ30 (ሰላሳ) ቀን ውስጥ በየካ ክ/ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ቀርቦ ካርታቸውን እንዲያስረክበን እንጠይቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ደሣለኝ ኑርጋ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ካርታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 029052 ሴሪ ቁጥር 013796 የይዞታ ስፋት 1000 ካ.ሜ የሆነ ካርታ የጠፋባቸው መሆኑን ከፖሊስ ማስመዝገባቸውን በቁጥር ወማ/10/25185/18 በቀን 11/09/18 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ በተገለፀልን መሰረት ወጪውን ግለሰቡ በመቻል በጋዜጣ እንዲታወጅላቸው እየገለፅን በማንኛውም ምክንያት የጠፋው ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ እስከ 30 ተከታታይ የስራ ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ካላቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

## የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለመጠየቅ

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት በ እነ ገሊላ ንጉሴ ስም የተመዘገበ ይዞታ መለያ ቁጥሩ AA00005l103450 የሆነና የተሰጠበት ቀን 21/10/2011 የሆነ የመብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት በቁጥር የካፖ/ለ/ቀ/15/12184/18 በ 06/08/2018 ዓ.ም የሚገልጽ ማስረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡ ይህም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለሁ ወይም መብት አለኝ የሚል በ 90 ቀናት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅ/ጽ/ቤት ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቾች ምትክ ሰርተፍኬት የምንሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ/ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በወ/ሮ ሰብለወንጌል ፅጌ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ወረዳ 01 ክልል ውስጥ የሚገኝ ይዞታ ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር 015523 ሴሪ ቁጥር 000770 የቦታው ስፋት 94.64 ካሬ ሜትር የሆነ ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በጋዜጣ እንዲታወጅ እየገለጽን በማንኛውም ምክንያት የጠፋውን ካርታ ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከታወጀበት ዕለት ጀምሮ እስከ 30 ተከታታይ የሥራ ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ካላቀረቡ በምትኩ ሌላ ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት**

---

በእነ ኤርሚያስ ገብረስላሴ ስሻህ ስም የተመዘገበ ነባር ይዞታ ካርታ ቁጥር ወ2/ውዝ01/404/10997/01 የጠፋባቸው መሆኑን በ07/09/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ በነበረኝ አስታጥቄ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 4 የቤት ቁጥር 302 ካርታ ቁጥር 07/84/26352/00 ተመዝግቦ የተሰጣቸው በእጃቸው መገኘት የነበረበት ካርታ የጠፋ በመሆኑ ይህንኑ አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም መቃወሚያ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ በ30 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት እነ የማነ ጉርሙ ቡሊቻ (8 ሰዎች) በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ በቀድሞ ቀበሌ-- በአሁኑ ወረዳ 03 ቤት ቁጥር -- ነዋሪ ሲሆኑ ከይዞታ አስተዳደር የተሰጣቸው ካርታ ቁጥር ወ3/ውዝ01/1538/25145/01 በሴሪ ቁጥር 0246989 ኦርጂናሉ ካርታ ተፈልጎ ሊገኝ ስላልቻለ በምትኩ ሌላ ካርታ እንዲሰጣቸው ይህንን ካርታ በዕዳ፣ በዋስትና ወይም በሌላ በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ካለ በ30 ቀን ውስጥ ኮ/ቀ/ክ/ከተማ ቀርቦ እንዲያሳውቅ ካላሳወቀ ግን በምትኩ ሌላ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አሚር አብዱራዛቅ መሀመድ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 የይዞታ ልዩ መለያ ኮዱ AA000061208148 ሴሪ ቁጥር 0183225 የሆነው ይዞታ እና በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ወ/ሮ ወ/ት እነ ስንዱ ተክለማሪያም የተባሉት በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 11 ቀበሌ -- ወይም በቀድሞው ወረዳ -- ቀበሌ -- የቤት ቁጥር -- የካርታ ቁጥር የካ/2/0565/10 ሴሪ ቁጥር 0116599 ተመዝግቦ የተሰጣቸው ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለው የሚል ካለ እስከ 20 ቀን ድረስ አዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን በምትኩ ሌላ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የየካ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ከአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 11 የቤት ቁጥር አዲስ በወ/ሮ ረሂማ ደንድር ኬረታ እና በአቶ ዘይኑ መህመድ ዳውድ ስም የተመዘገበውና የይዞታው ልዩ መለያ ቁጥር AA00009l101682 ሴሪ ቁጥር R 0229383 የሆነው የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) እንደጠፋባቸው በቀን 11/09/2018 ዓ/ም ያመለከቱ ሲሆን ይህንኑን የይዞታ ካርታ ይዤዋለሁ(አግኝቼዋለሁ) የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቅ/ፅ/ቤት ማቅረብ የሚችል ሲሆን ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ምትክ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

# በፅናት የተገኘ ስኬት

**በሳህሉ ብርሃኑ**

ባለፉት ሀያ ሁለት ዓመታት፣ ዓለም በፖለቲካውም ሆነ በስፖርቱ መስክ ፈጣንና ግዙፍ ለውጦችን አስተናግዳለች። በዚህ ወቅት ባራክ ኦባማ የመጀመሪያው ጥቁር የአሜሪካ ፕሬዝዳንት በመሆን ታሪክ ሲሰሩ፣ በታላቋ ብሪታንያ የነገሱት ንግሥት ኤልሳቤጥም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ዓለምን ያናወጠውና የአኗኗር ዘይቤን የቀየረው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ተከስቶ አልፏል፤ የቴክኖሎጂው በብዙ እጥፍ ተራምዷል። ማህበራዊ ሚዲያዎች ዓለምን በአንድ መንደር አስተሳስረዋል፤ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ በርካታ መንግሥታት ተለዋውጠዋል፡፡

በስፖርቱ ዓለምም እንዲሁ የሊዮኔል ሜሲና የክርስቲያኖ ሮናልዶ አስደናቂ የፉክክር ዘመን ተጀምሮ አብቅቷል። የአርሴናል የከተማ ተቀናቃኝ ቼልሲ፣ ማንቸስተር ሲቲ እና ሌስተር ሲቲ ሳይቀሩ የፕሪሚየር ሊጉን ዋንጫ በተደጋጋሚ ሲያነሱ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንደ ዩሴይን ቦልት ያሉ አትሌቶች የስፖርቱን ዓለም አዲስ ታሪክ ፅፈው አልፈዋል። አልፎ ተርፎም የማንቸስተር ሲቲው አሰልጣኝ ፔፕ ጋርዲዮላ ተጫዋችነቱን አቁሞ፣ አሰልጣኝ ሆኖ፣ በርካታ ዋንጫዎችን መሰብሰብ ችሏል። ነገር ግን፣ ይህ ሁሉ የዓለም ግዙፍ የለውጥ ሂደት ሲከናወን አንድ ነገር ሳይሳካ ቆይቷል፡፡ በእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ ታሪካዊውና በዓለም ላይ ሚሊዮኖች የሚደግፉት የአርሴናል እግር ኳስ ክለብ ከዋንጫ አሸናፊነት ርቆ ቆይቷል፡፡

የአርሴናል እግር ኳስ ክለብ የመጨረሻውን የፕሪምየር ሊግ ዋንጫ በታሪካዊው የ"ማይሸነፉት" (The Invincibles) ስብስብ አማካኝነት ሲያነሳ ዘመኑ የዛሬ 22 ዓመት፤ የ2003/04 የውድድር ዓመት ነበር። የቡድኑ የልብ ትርታና የለንደኑ ተወዳጅ ኮከብ ቡካዮ ሳካ በ2004 ዓ.ም የሁለት ዓመት ከግማሽ የወተት ጥርስ ሕፃን ነበር። በፈረንሳዩ 'ሌኪፕ' ጋዜጣ የድሉ "እውነተኛ ልብ" ተብሎ የተወደሰው ተከላካይ ዊሊያም ሳሊባ ደግሞ ገና የሶስት ዓመት አዳጊ ነበር። ቡድኑን በአምበልነት መርቶ ለክብር ያበቃው ማርቲን ኦዴጋርድ እንደዚሁ፣ የ5 ዓመት አዳጊ ነበር። ይህ የጊዜ ንጽጽር እውነት፣ እግር ኳስ የማያቋርጥ የትውልድ ቅብብሎሽ መሆኑን ነው።

እ.ኤ.አ በ2004 በአርሴን ቬንገር መሪነት ዓመቱን ሙሉ ሳይሸነፍ 'The Invincibles' ተብሎ በታሪክ የወርቅ ቀለም ከጻፈበት ጊዜ በኋላ የሰሜን ለንደኑ ክለብ አርሴናል ያሳለፈው ጊዜ በፈተናዎች የተሞላ ነው። ከሃይበሪ ወደ ኤምሬትስ ስታዲየም የተደረገው ሽግግር ክለቡን ለዓመታት ለከፍተኛ ዕዳ በመዳረጉ አርሴናል ኮከብ ተጫዋቾችን ለመሸጥ ተገድዷል። በሊጉ ከታላላቆቹ አራት ውስጥ መግባት ባለመቻል የሻምፒዮንስ ሊግ ተሳትፎ ማጣት እና የደጋፊዎች ተስፋ መቁረጥ ክለቡን ክፉኛ ፈትነውት ቆይተዋል። ባለፉት ጥቂት የውድድር ዓመታት ደግሞ ዋንጫውን ለመጨበጥ ተቃርበው በመጨረሻዎቹ ሳምንታት በማንቸስተር ሲቲ ሲነጠቁ የነበረው የደጋፊዎች ስሜት እጅጉን ሲጎዳ ቆይቷል።

በለንደን ከተማ ብቻም ሳይሆን በዓለም ዙሪያ በሚገኙ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የክለቡ ደጋፊዎች ልብ ውስጥ የነበረውን የ22 ዓመታት የዋንጫ ጥም በ2026ቱ የውድድር ዓመት ምላሽ አግኝቷል፡፡ በ37ኛ ሳምንት የፕሪሚየር ሊጉ ጨዋታ ማንቸስተር ሲቲ በበርንማውዝ ሜዳ አንድ አቻ መለያየቱን ተከትሎ፣ የሰሜን ለንደኑ አርሴናል እ.ኤ.አ ከ2004 በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የሊጉን ዋንጫ ማንሳቱን አረጋግጧል። ይህ ድል ለ22 ዓመታት የዘለቀ የናፍቆት፣ የልብ ስብራት፣ የትዕግሥት እና የፅናት መገለጫ ነው ሲሉ ብዙዎች ይገልፁታል።

አሰልጣኝ ሚኬል አርቴታ የክለቡን መንበር ሲረከቡ ቡድኑ የማንነት ቀውስ ውስጥ ገብቶ ነበር። ወጣቱን ስብስብ በመገንባት፣ የክለቡን ባህል በመቀየር እና በደጋፊው እና በቡድኑ መካከል የነበረውን የሻከረ ግንኙነት በመጠገን ረጅም መንገድ ተጉዘዋል። ቡድኑ በተደጋጋሚ ሲወድቅ እና ሲነሳ፣ ትችቶች ሲበራከቱ፣ አርቴታ ግን "ሂደቱን እመኑ" (Trust the Process) በሚል መርሕ ተጓዙ። ይህ መርሐቸው በተፈለገው ፍጥነት ውጤት ባለማምጣቱ ብዙዎች እንዲያሾፉባቸውም አድርጓቸው ነበር።

ዛሬ ላይ "ሂደቱን እመኑ" የሚለው መርሐቸው ፍሬ አፍርቶ የአርሴናል የሊጉን ዋንጫ የመጠበቂያ ጊዜው አከተመ። አርቴታ የተማመኑባቸው ወጣቶች እምነታቸውን አልበሉም፤ የሳካ ድንቅ ብቃት፣ የኦዴጋርድ መሪነት እና የመላው ቡድን አንድነት ለአርሴናል አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ከፍቷል። በውጤቱ ከለንደን እስከ አዲስ አበባ፣ ከቶኪዮ እስከ ኒው ዮርክ በዓለም ዙሪያ ያሉ የአርሴናል ደጋፊዎች ወደር በሌለው በደስታ ባህር ውስጥ ኖኙ፤ የደስታ ዕንባ ያፈሰሱም በርካቶች ናቸው።

ላለፉት 22 ዓመታት በሌሎች ክለቦች ደጋፊዎች ይደርስባቸው የነበረውን ስላቅ እና ብሽሽቅ በትዕግሥት ያሳለፉት የአርሴናል ደጋፊዎች በኩራት አንገታቸውን ቀና ማድረግ ችለዋል። ጎልማሶች እና አባቶች ዕድሜያቸው ከ25 ዓመት በታች ላሉ ወጣቶቹ "አርሴናል ዋንጫ ሲያነሣ እንዲህ ነበር" እያሉ የሚተርኩበት ዘመን አብቅቶ፣ አዲሱ ትውልድ የራሱን ታሪክ በዓይኑ ያየበት ወቅት ሆኗል። በለንደን ጎዳናዎች ላይ የሚታዩት ቀይ እና ነጭ ማሊያ የለበሱ ደጋፊዎች በደስታ ሲጨፍሩ፣ አንዳንዶቹም ላለፉት 22 ዓመታት ያሳለፉትን ውጣ ውረድ እያሰቡ የደስታ እንባ ሲያፈሱ ተስተውለዋል ይላል የ ዘ አትሌቲክ ዘጋባ።

ገና በ8 ዓመቱ ወደ አርሴናል አካዳሚ በመግባት "እዚህ ክለብ ውስጥ ኮከብ መሆን እፈልጋለሁ" ያለው የ24 ዓመቱ የክለቡ ምክትል ካፒቴን ቡካዮ ሳካ፣ ከ16 ዓመታት የልጅነት ጥረትና በ311 ጨዋታዎች ላይ ላበረከተው አስደናቂ የ152 የጎልና የጎል አስተዋጽኦ የሊጉን ዋንጫ በመጨበጥ ትልቅ ምላሽ ሰጥቷል። ሳካ የሻምፒዮንነት ድል ማግስት ባስተላለፈው የቪዲዮ መልዕክት፣ "ለ22 ዓመታት ሲስቁብንና ሲቀልዱብን ነበር፤ ከዚህ በኋላ ግን አይስቁብንም!" በማለት ለዓመታት በክለቡና በደጋፊው ላይ ይወርድ የነበረውን ማሾፍና ስድብ ያበቃለት መሆኑን በኩራት ገልጧል፡፡

የቢቢሲ ስፖርት ተንታኝና የቀድሞ የማንቸስተር ሲቲ ተጫዋች ሚካ ሪቻርድስ፣ ቡድኑ ያሳየውን የስነ-ልቦና ሽግግር ሲያደንቅ፣ "አርሴናል በመጨረሻ ከመሸነፍ ፍርሃት ወጥቷል። ይህ ቡድን አሁን እውነተኛ የአሸናፊ አዕምሮ ገንብቷል" ብሏል። ሪቻርድስ አክሎም፣ ይህ ውጤት በአንድ ጀምበር የመጣ ሳይሆን አሰልጣኝ ሚኬል አርቴታ በተሰጠው ጊዜና ትዕግሥት ላለፉት ሶስት ዓመታት በጥንቃቄ የገነባው ድንቅ ፕሮጀክት ፍሬ መሆኑን መስክሯል።

የስካይ ስፖርቱ ተንታኝ ጋሪ ኔቪል በበኩሉ፣ ድሉ ለደጋፊው ማኅበረሰብ ያለውን ትርጉም በስሜት ገልጾታል። "ለአርሴናል ደጋፊዎች ለ22 ዓመት ሙሉ ተስፋ ሳይቆርጡ ቆይተዋል" ያለው ኔቪል፣ የሰሜን ለንደኑን ታማኝ ደጋፊዎች "በእግር ኳስ ታሪክ ውስጥ ካሉ በጣም ታጋሽና ጽኑ ደጋፊዎች" ሲል አወድሷቸዋል። በሌላ በኩል፣ የዘ አትሌትክ ታዋቂው የእግር ኳስ ጸሐፊ ዴቪድ ኦርንስቴን፣ የክለቡን ጉዞ ለየት ባለ እይታ አስቀምጦታል። ኦርንስቴን ይህንን ታሪክ "በአንድ ወቅት ሂደቱን እመኑ እየተባለ ከሚሳለቁበት መድረክ ተነሥቶ፣ ዛሬ ወደ እውነተኛ የእግር ኳስ ፕሮጀክት የተቀየረ ታላቅ ታሪክ" ሲል አክብሮታል።

የኬንያው ፕሬዝዳንት ዊሊያም ሩቶ የአርሴናልን የዓመታት ጉዞ "ከውድቀትና ከከባድ ፈተናዎች ተነስተው፣ ተስፋ ባለመቁረጥና በማይናወጥ ጥንካሬ ወደ እግር ኳስ ማማው ማደግ የቻሉበት ታላቅ ጀብዱ" ሲሉ አሞካሽተውታል። ክለቡ በየሳምንቱ ከተፎካካሪዎች ጋር ያደረገው ፍልሚያ የተስፋን፣ የፅናትን እና የጠንካራ ስራን ኃይል በተግባር ያሳየ መሆኑንም ገልጸዋል። ፕሬዝዳንቱ አክለውም፣ "በደማቁ ምሽት ያ ታላቅ ጥረት ፍሬ አፍርቷል፤ ቡድኑም የድሉ ባለቤት ሆኗል። ይህ ድል በጠንካራ ስራ፣ በዲሲፕሊን እና በቡድን መንፈስ ስኬትን ማምጣት እንደሚቻል ማረጋገጫ ነው" በማለት ገልፀውታል፡፡

ለዓመታት ይወርድባቸው የነበረውን ነቀፌታና የጥርጣሬ አጥር ሰብረው ለመውጣት መድፈኞቹ ያሳዩት ፍልሚያ የእግር ኳስን ጥበብ ወደ ላቀ የህይወት ፍልስፍና የቀየረ ነበር። እያንዳንዱ ተጫዋች በሜዳ ላይ ሲታገልና ለአንድ ዓላማ በጋራ ሲቆም የነበረው ትዕይንት፤ ተስፋ በውስጡ ለሌለው ሰው ብርሃን የሚሰጥ፣ ፅናት ደግሞ አቋራጭ መንገድ ለሚፈልጉ ሁሉ ከባድ ስራን የሚሰብክ ድንቅ ማስተማሪያ ሆኗል። በመጨረሻም፣ ይህ ስብስብ የሊጉን የክብር አክሊል ሲቀዳጅ ያሳየው ትልቁ እውነት፣ በፅናት ከቀጠሉና ጠንክሮ መስራት ከተቻለ የማይታለፍ ተራራና የማይሰበር የጥርጣሬ ግንብ በምድር ላይ እንደሌለ ነው።


ፎቶ፡- ከገፀ ድር
አርሴናል ከ22 የፅናት ዓመታት በኋላ የእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግ ዋንጫ አሸናፊ ሆኗል


እሁድ ምሽት ከ2፡00 ሰዓት ጀምሮ ይጠብቁን
ሸዊት ከበደ
ቴዎድሮስ ተሾመ
ተስፋዬ ቢማ
ውብ አደይስ
ተስፋዬ እሸቱ
AMN
Addis Media Network
TEDDY STUDIO